# ማውጫ

*እንግዳችን*

ኢህአዴግ የተለያዩ ቀውሶችን ያለፈ ድርጅት ባይሆን ኖሮ አገርን ጭምር አደጋ ላይ የሚጥል ጥቃት ነው የተፈጸመው ........................................3

*በጎ አድራጎት*

በጎ ፈቃደኝነት ከዘመቻ ወደ ባህል........................................13

*ዓብይ ርዕስ*

ስርዓት ሊበጅለት የሚገባው ህግ አልባው የጦር መሳሪያ ዝውውር ......................24

*ተሞክሮ*

ኪጋሊ እንደምን ጽዱ ሆነች ........................................31

*ዓውደ ሃሳብ ...*

የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ ለምን ታጠፈ?........................................39

*ጥንቅር*

የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂው የፖለቲካ ምህዳር ........................................52

*ዓለም ዓቀፍ*

ዓለማዊ፣ አከባቢያዊና አገራዊ ሁኔታችን........................................60

# ዓውደ ለውጥ

**በአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት በየሁለት ወሩ እየታተመች ልዩ ልዩ ጥንቅሮችን፣ትንታኔና፣ መዝናኛ ይዛ የምትወጣ ልዩ መፅሔት**

**አዘጋጅ፡- የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት ህዝብ ግንኙነት ዘርፍ**

**አሳታሚ፡- አዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት**

**አድራሻ፡- 0116 67 43 94**

**ኢ.ሜይል፡- awdelewt@gmail.com**

**1ኛ ዓመት ቅፅ1 ሐምሌ-ነሐሴ 2011**

ዋና አዘጋጅ፡- ዘሪሁን ገ/መድህን 011 6 67 43 94

አዘጋጆች፡-

ታደለ በቀለ 011 6 67 44 13

ዮሐንስ ለገሠ

ብርሃኑ አምኃ

ቴዎድሮስ ተሻለ

ዲዛይነር፡- ደኗ ግዛው

ፊ/ዲዛይነር፡- እሪታቸ ቀኑብህ

ሽፋን ገፅ፡- ያሬድ መርሻ

ካርቱኒስት፡- አወቀ ንጉሴ

ህትመት ክትትል፡- ቤተልሔም ገ/ስላሴ

ህትመት ስርጭት፡- ትዕግስት አለሙ



# የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት

ዓውድ ሸንጎ ነው፤ አደባባይም ነው፤ አገሩ አድባሩ የሚመክርበት መሰብሰቢያ ስፍራ ነው፡፡ የዓውድ ትርጓሜ እንዲህ ከሆነ የዓውደ ለውጥ ምንነት እዚያው በዚያው ተብራርቷልና አብዝተን አንሰልቀውም፡፡ በቃ በለውጥ አስተሳሰብ፣ አመራርና ስምሪት፣ ችግሮችና መፍትሄዎች ዙሪያ በዋነኛነት የሚያጠነጥኑ ጉዳዮች የሚበራዩበት ዙሪያ መለስ መፅሄት ነው- ዓውደ ለውጥ

በአዲስ አበባ ኢህአዴግ ደረጃ የዚህ መፅሄት አስፈላጊነቱ የምሁር አባሎቻችንን ደረጃ የሚመጥን ልሳን ማዘጋጀትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ለአለፉት 11 ዓመታት በህዳሴ ጋዜጣ ላይ በሳይንሳዊ ዕውቀትና ምርምር የላቀውንም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ትምህርት ገበታ ጎራ ያላሉ አባሎቻችንን ማዕከል ያደረጉ ጽሁፎችን በየአምዶቿ ይዛ በመውጣት እንደ አንድ የፖለቲካ አቅም መገንቢያነት ስታገለግል ቆይታለች፡፡ በአባላት መካከል የአለው የትምህርት ሁኔታ ክፍተቱ የሰፋ በመሆኑ አንዱ ይፋጃል ሲል ሌላው ይቆፈንናል የሚለው፣ በጥናት እንደ ተረጋገጠውም ከሁለት የአጣ መሆንን አስከትሏል፡፡ እናም ቢያንስ ምሁር አባላችን ለራሱ የሚዘጋጅለት የአስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ሁለገብ መፅሄት ተገቢነቱ ታምኖበት እነሆ የመጀመሪያ ዕትም ለንባብ በቅቷል፡፡

ዓውደ ለውጥ መፅሄት ይዘትዋም ሆነ ሙሌትዋ በዝግጅት ክፍሉ ብቻ የሚሸፈን አይደለም፡፡ እንዲያውም ምሁር የድርጅታችን አባላት ሊነበቡበት፣ በሙያቸው፣ በስራ ልምዳቸው፣ በዕውቀታቸው፣ በንባብ ሃብታቸው የአካበቱትን ሰናይ ነገር ሁሉ ለሌሎች የሚያካፍሉበት እንድትሆንም ነው የሚፈለገው:: በተለይም ለውጡ ቃለ አብዮቱን የሚያነበንቡለትን ሳይሆን በለውጡ ውስጥ የሚታይን ዝግመትም ሆነ ጉብጠት በተጨባጭ እየነቀሱ በማሳየት፣ በገንቢ ትችት ለውጡን የሚያጎለብቱ ሃሳቦች ይሻል፡፡ ከምሁራን አባላት እንዲህ አይነት መጣጥፎችን ዓውደ ለውጥ መፅሄታችን በናፍቆትና በጉጉት ትጠብቃለች፤ ታስተናግዳለችም፡፡

ከስብሰባ እውቀት በዘለለ ምሁራን አባላት በማንበብና በመነበብ እንዲገነቡ ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን እንዲያበለፅጉ፣ አስተሳሰብ ከአስተሳሰብ እንዲፋለሙ፣ እንዲዋሃዱ ዓውደ ለውጥ ተጀምራለች፡፡ ጅምሩን በነቃ ምሁራዊ ተሳትፎ ማዝለቅ የምሁር አባላት ጉዳይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በዚህ የመጀመሪያ ዕትማችንም ሁለት አመራሮች ዘመን ጆነዲ በጐ ፈቃደኝነትን ፣ ፀጋዬ በየነ ደግሞ ዓለማዊና አገራዊ ሁኔታችንን በተመለከተ የላኩልንን ፅሁፍ ለንባብ አብቅተናል፡፡ ለተሳትፏቸውም ምስጋናችን ይድረሳቸው፡፡ ይህች የመጀመሪያ ዕትም አንባቢያን ዘንድ ደርሳ የምትቀር ሳይሆን አስተያየት፣ ትችትም ሆነ መጣጥፎች ወደ ዝግጅት ክፍላችን እንዲላኩ እንጠብቃለን፡፡ ሰናይ ንባብ!!

# “ኢህአዴግ ልምድ ያለው ድርጅት በመሆኑ እና ለበርካታ ጊዜያት የተለያዩ ቀውሶችን ያለፈ ድርጅት ባይሆን ኖሮ አገርን ጭምር አደጋ ላይ የሚጥል ጥቃት ነው የተፈጸመው”



***ጓድ ተስፋዬ በልጅጌ የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ ናቸው፡፡ የአዲስ አበባ ኢህአዴግ በበጀት ዓመቱ የድርጅት፣ የፓለቲካ ስራዎችን፣ አፈፃፀምና ለውጡን በተመለከተ ከልሳናችን ጋር የአደረጉት ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡***

*ዓውደ ለውጥ፡- የአመቱን የድርጅትና የፖለቲካ ተግባራት እንዴት ይገመግሙታል?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* በተጠናቀቀው የበጀት አመት የለውጥ ስራዎችን እየሰራን የቆየንበት ነው፡፡ የለውጥ ስራዎችን ስንጀምር ስድስት ዋና ዋና የለውጥ ማዕከል ናቸው ተብለው የተለዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንደኛው እና የመጀመሪያው ዴሞክራሲን እያሰፋን ዴሞክራሲያዊ ባህልን እያሳደግን እንሂድ ብለን ነው የወሰድነው፡፡ በድርጅት ውስጥ ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን ማስፋት ነው፡፡ በህዝብ ውስጥ ደግሞ ከህዝብ ጋር የምንሰራውን ስራ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የዴሞክራሲ ባህልን እያሳደግን መሄድ ነው፡፡

ሁለተኛው የለውጡ እንቅስቃሴ መሆን አለበት ብለን የለየነው አገራዊ አንድነታችንን ማጠናከርና መገንባት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ማንነት ግንባታ ላይ ይበልጥ ትኩረት መስጠት ነው፡፡ ኢትዮጵያ የብዝሀነት አገር ናት፡፡ ብዝሀነትን ማዕከል ያደረገ ብዙ ቋንቋዎች፣ ብዙ ታሪኮች፣ ብዙ ባህሎች ቢኖሩንም አንዲት አገር ናት ያለችን፡፡ የአንዲት አገር ዜጎች እንደመሆናችን መጠን በኢትዮጵያዊ ማንነትና በብሄራዊ ማንነት መካከል

***ኢህአዴግ ምንጊዜም የህብረተሰቡ ንቃተ ህሊናና የእድገት ደረጃ በደረሰበት ራሱን እያረመ፣ እያስተካከለና እያደሰ የመጣ ተራማጅ ድርጅት ነው፡፡ ይህንን ተራማጅ ባህሪውን ይዞ ለውጡን ለመምራት ቆርጦ የተነሳ ድርጅት ነው፡፡***

የነበረውንና በጥልቅ ተሀድሶ የገመገምነውን የተዛባውን ነገር በማስተካከል አገራዊ አንድነታችንን ማጠናከርና መገንባት፣ ለዚህ ደግሞ የድርጅት አመራሩ ተምሳሌት እየሆነ እንዲሄድ ማድረግ ነው ሁለተኛው የለውጥ እንቅስቃሴ ማዕከል ተደርጎ የተወሰደው፡፡

ሌላው ብልፅግና፣ ልማትን ማፋጠን፣ ድህነትን እየታገልን መሄድ ነው፡፡ በዚህም የከተማውን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ እያሻሻልን መሄድ ነው፡፡ ይሄ በውስጡ ብዙ ትርጉሞች አሉት፡፡ የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የምንሰራው ስራ፣ ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ ላይ የምንሰራው ስራ በአጠቃላይ ከተማችንን ማልማትና፣ የከተማችን ነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል ስራ ሶስተኛው የለውጡ ማዕከል ነው፡፡

አራተኛው ሙስናን፣ ሌብነትን መታገል እና መልካም አስተዳደርን እያሰፈኑ መሄድ ነው፡፡ አምስተኛው አገራዊ ኩራት የመገንባት ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ዜጎች የሚኮሩባት አገር እንድትሆን ማድረግ ነው፡፡ ከዛ ውጭ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ የለውጡ ማዕከላዊ ነጥብ ውስጥ የሚታይ ነው፡፡ ዘላቂ ሰላምን፣ የህግ የበላይነትን እያረጋገጥን መሄድ ነው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና የለውጡ እንቅስቃሴ ማዕከላዊ ነጥቦች ናቸው፡፡

የሁሉም እንቅስቃሴያችን ማዕከላዊ ነጥቦች እነዚህ ናቸው፡፡ በእነዚህ ዙሪያ ነው የለውጥ እንቅስቃሴያችን ማዕከል የሚያደርገው፡፡ ከእነዚህ አኳያ ነው የአመቱ የድርጅት እና የፖለቲካ ስራዎች አፈፃፀም የሚለካው፡፡

ይህንን ታሳቢ አድርገን በመጀመሪያ አዲስ አበባ ላይ ያለው የድርጅት መዋቅር ይህንን የለውጥ ስራ መምራት የሚችል ቁመና እንዲኖረው ለማድረግ በርካታ ስራ ተሰርቷል፡፡ አንደኛ በአመቱ መጀመሪያ ልክ ለውጡን ስንጀምር በመዋቅራችን በጣም ብዙ ውዥንብሮች ነበሩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደ ስርአት ለውጥ ይቆጠራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህንን ለውጥ ኢህአዴግ ይመራዋል ወይ? ይባላል፡፡ ከዚህ አኳያ ብዥታዎችን ለመቅረፍ ለውጡ ኢህአዴጋዊ፣ ህዝባዊ እና ህገ-መንግስታዊ መሆኑ ላይ መላው መዋቅር እንዲስማማ፣ ኢህአዴግ በጉባኤው የወሰነውን አቅጣጫ ይዘን ስልጠና ሰጥተናል፡፡ ይህ ስልጠና እስከ መላው አባል ድረስ ወርዷል፡፡

በዚህ መሰረት ለውጡ በህዝብ ገፊነት እና በኢህአዴግ ተፈጥሮአዊ ተራማጅነት፣ ሁሌም ራሱን ከመድረኩ አንጻር እየቃኘ የሚሄድ ድርጅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመጣ ለውጥ ስለሆነ ኢህአዴግ ይህን ለውጥ መምራት የሚችል ድርጅት ነው  የሚል አስተሳሰብ፣ አመለካከት እና ግንዛቤ በመላው አባል እና መዋቅር እንዲፈጠር የማድረግ ስራ ነው ከአመቱ መጀመሪያ ጀምሮ እየተሰራ የቆየው፡፡

አንዱ የፖለቲካ ስራ የሚባለው ለውጡን በብቃት መምራት ነው፡፡ ሁለተኛው ለውጡን ተቋማዊ የማድረግ ስራ ነው፡፡ ይህንን በየደረጃው ያለው የድርጅት መዋቅር ከአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ፅ/ቤት ጀምሮ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ እስከ ህዋስ እና መሰረታዊ ድርጅት ድረስ ያሉት አደረጃጀቶች እና ተቋማት ለውጡን በብቃት እንዲመሩት ማድረግ ነው፡፡

ለውጡን የድርጅት መዋቅሩ መምራት እና የለውጡ ባለቤት የማድረግ ስራ ነው ሁለተኛው የስራ ማዕከል ተደርጎ የተወሰደው፡፡ ከዚህ አኳያ የግንዛቤ፣ የአስተሳሰብ ጥራት የክህሎት ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ ስልጠናዎች ለአመራሩ በጋራም በተናጠልም ተሰጥተዋል፡፡ ይህ ከአመቱ መጀመሪያ ጀምሮ በአመቱ አጋማሽም ስራዎች የደረሱበትን ደረጃ እየገመገምን የግንዛቤ፣ የእውቀት፣ የክህሎት ክፍተቶችን የሚሞላ ስራ ለመስራት ተሞክሯል፡፡ አንዱ እና ዋናው በለውጡ ዙሪያ መላው አመራር አባል እና ደጋፊያችን ግልፅነት እንዲፈጥር የተሰራው ስራ ነው፡፡ ይህ ስራ ጥሩ ውጤት አስገኝቷል ብሎ መውሰድ ይቻላል፤ የሚሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩም፡፡

ሌላኛው የድርጅት እና የፖለቲካ ስራ ይህንን ለውጥ በብቃት መምራት የሚችል አመራር ከላይ እስከ ታች የማደራጀት ተግባር ነው፡፡ ለውጡን የሚመሩ አመራሮችን የማደራጀት ስራ ከተከናወነ በኋላ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ግንዛቤዎች ተፈጥረዋል፡፡ ተቋማትም እንደገና እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡

አዲስ አበባ አራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በጋራ የሚመሯት ከተማ እንደመሆኗ መጠን በአባል

***"መንግስትን መተቸት፣ አመራሩን ሂስ ማድረግ ማለት አሉባልታ፣ ውዥንብርና በሬ ወለደ የሆኑ የሃሰት መረጃዎችን ማሰራጨት ማለት አይደለም፡፡"***

ድርጅቶች መካከል ያለው የአስተሳሰብ እና የተግባር አንድነት እንዲጠናከር በየጊዜው እየተሰራ መጥቷል፡፡

እነዚህን ስራዎች ይዘን በመግባባት አዲስ አበባ ላይ የለውጡ አስተሳሰቦች በአመራሩ፣ በአባሉ እና በደጋፊው በአግባቡ እንዲጨበጡ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ቀጣዩ ተልዕኮ አድርገን የወሰድነው ህዝብ ውስጥ የምንሰራው ስራ ነው፡፡ ከወጣቶች ጋር፣ ከሴቶች ጋር፣ ከላብ አደሮች ጋር፣ ከመንግስት ሰራተኞች ጋር የተለያዩ መድረኮች እየተከፈቱ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ይህ ለውጥ ህዝባዊ እንደመሆኑ መጠን ህዝቡ ካልተሳተፈበት ስለማይሳካ ህዝቡ የዚህ ለውጥ አጀንዳ ባለቤት እንዲሆን ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ለውጡ መጀመሪያ በድርጅት ውስጥ ቀጥሎ በህዝብ ውስጥ መሪው ድርጅት ከህዝቡ ጋር ሆኖ ለውጡን ለማስፈፀም መሰራት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ሰፊ የፖለቲካና የድርጅት ስራ ተሰርቷል፡፡

የተሰራው የፖለቲካና የድርጅት፣ ስራ በጥቅሉ ስናየው ውጤት አስገኝቷል፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ባለፈው አንድ አመት ሰፋፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አንደኛ ህዝቡን ቅሬታ ውስጥ ሲያስገቡ የነበሩ የተለያዩ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ሲያስነሱ የነበሩና ሲንከባለሉ የቆዩ ጉዳዮች ላይ የለውጥ አመራሩ ፈጣን እና ቆራጥ እርምጃዎችን እየወሰደ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ የታጠሩ ቦታዎች ወደ ስራ እንዲገቡ ወይም ተመልሰው ለልማት በሚውል መልኩ ወደ መሬት ባንክ መመለስ፣ ከተማ ውስጥ ያሉ በህገ ወጥ መንገድ ተይዘው የነበሩ የመንግስት ቤቶችን በማስለቀቅ ለአቅመ ደካሞች እና ለሚገባቸው አካላት ህዝቡ በተሳተፈበት መንገድ መስጠት፣ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ተዘዋዋሪ ፈንድ መድበንም ለወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል የተለየ ትኩረት መስጠታችንን አሳይተናል፡፡

የከተማዋን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበርም በየጊዜው ከህብረተሰቡ ጋር በመወያየት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት ረገድም ቀላል የማይባሉ ህዝብ የተሳተፈባቸው የሰላም ማረጋገጥ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ እነዚህ መልካም ጅምሮች ናቸው፡፡

ያጋጠሙን ተግዳሮቶችም አሉ ከድርጅት እና ከፖለቲካ ስራ አኳያ በየደረጃው ለውጡን ተቋማዊ

**“ለውጡን የሚመሩ አመራሮችን የማደራጀት ስራ ከተከናወነ በኋላ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ግንዛቤዎች ተፈጥረዋል፡፡ ተቋማትም እንደገና እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡”**

***“እንዱና ትልቁ እውቅና መሰጠት ያለበት ለድርጅታችን ሊቀመንበርና ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ ነው፡፡”***

አድርጎ መምራት ላይ አሁንም ብዙ ልናርማቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ! በአዲሱ የበጀት አመት የበለጠ ትኩረት ሰጥተን የእርምት ስራዎችንም እናካሂዳለን፡፡

ሁለተኛው በየደረጃው አመራር ብለን የመደብነው ሃይል በሁሉም ተቋም፣ በሁሉም ደረጃ፣ በተመሳሳይ የአቅም ልክ አይደለም የሚገኘው፡፡ አንዳንዱ በከፍተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ሲገኝ፣ ሌላው ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ይገኛል፡፡ ለውጡን መሸከም የማይችል፣ ባስ ሲልም የሚያደናቅፍም ጭምር እንዳለ ታይቷል!፡፡ ስለዚህ መዋቅራችንን በላቀ ደረጃ ማጠናከር፣ ማጥራት እና በተስተካከለ መንገድ ወደስራ እንዲገባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ከተማችን የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከተማ ስለሆነች ከሁሉም አካባቢ የሚከሰተው በጐም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ ወደ ከተማዋ ይዛመታል፡፡ ስለዚህ ክልሎች አካባቢ የሚፈጠሩ ችግሮች በከተማዋ ላይ ተፅዕኖ በሚፈጥሩበት ወቅት ይህንን ለማረምና ለማስተካከል ጥረት አድርገናል፡፡ ኢትዮጵያዊ ማንነት እንገነባለን ብለን የለውጥ ማዕከል አድርገን ተግባብተን በጋራ ወደ ስራ ብንገባም አልፎ አልፎ የዘረኝነት፣ የመለያየት፣ የአክራሪ ብሔርተኝነት ምልክቶች መታየት በዓመቱ ውስጥ ካጋጠሙ ችግሮች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በዚህ በኩልም ኢህአዴጋዊ አንድነታችንና ኢትዮጵያዊ ህብረታችንን የሚያጠናክሩ ስራዎችን በመስራት በአመራር መሀል ያለው ውህደት እንዳይጎዳ፣ ይበልጥ እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

የአመራሩ ውጤታማነት በተመለከተ በተሰማራበት የስራ መስክ ውጤት ማስመዝገብ በተለይ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ህዝቡን የሚያረካ ስራ ከመስራት አንጻር የህዝብ እርካታ መጠኑ ሲታይ አሁንም ገና ብዙ መስራት እንደሚያስፈልግ የሚያሳዩ ነገሮች አሉ፡፡ በተጨማሪም ሙስናን፣ ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን መታገልና ማስወገድ ላይ የተጀመሩ ስራዎችና የተገኙ ውጤቶች አሉ፤ ለወደፊት አጠናክሮ ከማስቀጠል አኳያ ብዙ ስራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ የሚከሰቱ የጸጥታ ችግሮች ከተማችን ላይ ስጋትን ለመቀነስ፤ ከጸጥታ አኳያ ህብረተሰቡ ከጭንቀት ነጻ ሆኖ የየእለት ስራውን

**“አጀማመራችን ጥሩ ነው ብዙ ውጤቶችም ተገኝተዋል፤ ከህብረተሰቡ ፍላጎትና መሬት ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ተጨማሪ ስራዎች ይጠብቁናል፡፡”**

*“ ሰዎች ለስልጣን እየተገዳደሉ ባሉበት በእዚህ ወቅት ቁጭ ብሎ ተነጋግሮ የአገርን መሪ መቀየር እንደኛ የዴሞክራሲ ባህልን መለማመድ መጀመራችንን የሚያሳይ መሆኑን፤ ሁለተኛ ስልጣን ለህብረተሰባዊ ለውጥ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ለግለሰቦች እንዳልሆነ ማሳያ ነው፡፡”*

እንዲሰራ ከማድረግ አንጻር ገና ብዙ የቤት ስራ ይጠበቅብናል፡፡ በአጠቃላይ አጀማመራችን ጥሩ ነው ብዙ ውጤቶችም ተገኝተዋል፤ ከህብረተሰቡ ፍላጎትና መሬት ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር፤ ተጨማሪ ስራዎች ይጠብቁናል፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- የተጀመረውን አገራዊ ለውጥ ለማስቀጠልና የድርጅታችን ኢህአዴግን መሪነት ለማጠናከር አንጻር በየደረጃው ከሚገኝ አባልና አመራር ምን ይጠበቃል ይላሉ?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* የተጀመረውን አገራዊ ለውጥ ለማስቀጠል የድርጅታችንን ኢህአዴግ የመሪነት ሚና ለማጠናከር አንጻር በየደረጃው ከሚገኘው አባልና አመራር የሚጠበቀው ዋናው ነገር ለውጡ ኢህአዴጋዊ፣ ህገመንግስታዊና ህዝባዊ መሆን ላይ መጀመሪያ ግልጽ መሆን ነው፡፡ ለውጡ ኢህአዴጋዊ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው፤ ኢህአዴግ ምንጊዜም የህብረተሰቡ ንቃተ ህሊናና የእድገት ደረጃ በደረሰበት ራሱን እያረመ፣ እያስተካከለና እያደሰ የመጣ ተራማጅ ድርጅት ነው፡፡ ይህንን ተራማጅ ባህሪውን ይዞ ለውጡን ለመምራት ቆርጦ የተነሳ ድርጅት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ የሚያደርገው በየደረጃው ያለው አመራር ነው፡፡ በደረጃው ያለው አመራር ውጤታማ ከሆነ ኢህአዴግ ውጤታማ ሆነ ማለት ነው፡፡ በየደረጃው ያለው አመራር ለውጡንና የለውጡ ማእከላዊ ነጥቦች ብለን የለየናቸውን ነገሮች በብቃት ካልመራ ድርጅቱ በህዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገባ ማለት ነው፡፡

ይህን የምንልበት ዋናው ምክንያት ከለውጡ በፊት በርካታ ችግሮችን ገምግመናል፡፡ በጋራ የገመገምናቸው እነዚህ ችግሮች የመጀመሪያው በህዝቡ ውስጥ የሚመላለሱ ጥያቄዎች ተገቢውንና ፈጣን ምላሽ መስጠት አለመቻላችን ነው፡፡ በዋናነት ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህን እየቀረፉ መሔድ አለብን በሚል በተለየ ትኩረት ለመስራት እየተሞከረ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የተገኙ ውጤቶች አሉ፤ በቀጣይም ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- የተጀመረው የሪፎርም ስራ በድርጅት አቅም እየተመራ ነው ማለት ይቻላል?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* በዚህ ከተማ እየተሰሩ ያሉ የሪፎርም ስራዎችን እየፈጸመ ያለው አመራር ነው፡፡ እያስፈጸመም ያለው አመራር ነው፡፡ እያስተባበረም ያለው እንደዚሁ አመራሩ ነው፡፡ አመራሩ ደግሞ የለውጥ አመራር መሆን አለበት ብለን እንደ ድርጅት በጋራ የመደብናቸው አመራሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ የሪፎርም ስራው አነሰም በዛም እየተመራ ያለው በድርጅት አቅም ነው፡፡ ከድርጅቱ ውጭ ያለ ሊመራ የሚችል ኃይልም ስሌለለ ማለት ነው፡፡ ሌላው ይህ ሪፎርም እየተመራ ያለው ኢህአዴግ በጉባኤው ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በመሆኑ ሪፎርሙ በድርጅቱ አስተሳሰብ አመለካከት እየተመራ መሆኑ ሪፎርሙ በድርጅት አቅም እየተመራ ነው ያስብለዋል፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- ኢህአዴግ የህግ የበላይነትን በማስከበር ረገድ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው ማለት ይቻላል?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* ባለፈው አንድ አመት ውስጥ ከገጠሙን ጠንካራ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ እንደኢህአዴግ በአዲስ አበባም ብቻም ሳይሆን በአገር ደረጃ የህግ የበላይነትን ማክበር፣ ማስከበር፣ በህግ መመራትና ዴሞክራሲያዊ ባህልን እያጎለበቱ መሄድ ላይ ነው፡፡ ነጻነት፣ መብት፣ ዴሞክራሲ አንዱ ከሌላው አይነጣጠሉም:: አንዱን መጉዳት ሌላውን ይጎዳል፡፡ ለምሳሌ የዴሞክራሲ መርሆዎች "ሀሁ" የሚባለው የህግ የበላይነት መከበር ነው፡፡ ነጻነት መብትም ከህግ የበላይነት እና በህግ ከመመራት ውጭ ሊታሰብ አይችልም:: ስለዚህ የህግ የበላይነትን በተመለከተ አደጋ ላይ የሚጥሉ ነገሮች እዚያም እዚህም ተከስተዋል፡፡ እዚያም እዚያም የተከሰቱ ነገሮች መንግስትን ብዙ ዋጋ አስከፍለውታል፡፡ አዲስ አበባ ላይ ብንወስድ ዙሪያው ላይ በሚፈጠሩ ችግሮች የሚፈናቀል ሰው አዲስ አበባ ይገባል፡፡ ጫናም ይፈጥራል፡፡ የመሳሪያ ዝውውር ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ አዲስ አበባ በገፍ ለመግባት ይሞከራል፡፡ የተለያዩ ቡድኖች ተደራጅተው በየሰፈሩ የተደራጀ ሌብነት የመፈጸም ፍላጎት ይታያል፡፡ ነገር ግን በከተማው ውስጥ ያለው የጸጥታ መዋቅር ከፌደራል መንግስት ጋር በመቀናጀት በየጊዜው እየታዩ ያሉ በህግ የበላይነት ጥያቄ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እያረምን

**"የአዲስ አበባ ነዋሪ ህግን የሚያከብር አብሮነትና አንድነትን የሚያከብር ከዚህ ውጭ ለሆነ ነገር ለአዲስ አበባ ጠቃሚ እንዳልሆነ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው::"**

መጥተናል፡፡ ከዚህ አንጻር ትልቅ ምስጋና ማቅረብ የምንፈልገው ለነዋሪውና ለወጣቱ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ነዋሪ ህግን የሚያከብር አብሮነትና አንድነትን የሚያከብር ከዚህ ውጭ ለሆነ ነገር ለአዲስ አበባ ጠቃሚ እንዳልሆነ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ስለሆነም በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮችን የድርጅትና የመንግስት አመራር በጋራ ተቀናጅቶ መልክ መልክ እያስያዘ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑ በማድረግ አመቱን ሙሉ ማሳለፍ ችለናል፡፡ አሁን ደግሞ ሰፊ ስራ እየሰራን ነው ያለነው፡፡ ጥሩ ውጤት እየተገኘም ነው፤ የበለጠ ህብረተሰቡን በማሳተፍ የሚቀጥል ይሆናል ማለት ነው፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- የኢህአዴግ የለውጥ መሪነትን ለመቀበል ለሚቸግራቸው ወገኖች ያለዎት ምክር ምንድን ነው?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* አንድ መንግስትን የሚመራ ፓርቲ ረጅም ጊዜ ስልጣን ላይ ሲቆይ ከሚመጡ ጥያቄዎች አንዱ በየጊዜው ራሱን እያሻሻለ የሚሔድ እንኳን ቢሆን በየጊዜው በሂደት ከሚፈጽማቸው ስህተቶች ትችቶች ይነሱበታል፡፡ ፓርቲዎች ለረጅም ጊዜ ስልጣን ላይ ሲወጡ ቀዳሚ ጥንቃቄ የሚወስዱት ብዙ ስህተት እንዳይሰሩ ነው፡፡ ኢህአዴግ በደረሰበት የእድገት ደረጃ እንደ ድርጅት ችግር ውስጥ ሲገባ ራሱን ውስጡን እየገመገመ ከችግር ለመውጣት ጥረት እያደረገ ነው፡፡

ለምሳሌ አሁን የተፈጠረውን ለውጥ በተመለከተ በኢትዮጵያ ታሪክ የማይረሳቸው እርምጃዎች ተወስደው ነው እውን ማድረግ የተቻለው፡፡ ያለምንም ደም መፋሰስ የስልጣን ርክክብ እንዲፈጸምና የመሪዎች ለውጥ የተደረገው ኢህአዴግ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ከልብ ስላመነ ነው፡፡ ይሄ በአፍሪካ አልተለመደም፡፡ ምክንያቱም ለስልጣን ሲባል 20 ዓመትና ከዛም በላይ መዋጋት አፍሪካ ውስጥ የተለመደ ነውና!

ኢህአዴግ ለውጥን ከልብ በመቀበሉ ምክንያት በታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም ለ17 ቀናት ጥልቅ ውይይት አድርጎ ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድና የመሪዎች ለውጥ ጭምር ማድረግ አለብን በሚል ወስኗል፡፡ ይህንንም በተግባር ማረጋገጥ ችሏል፡፡ ይሄን አይነት አካሄድ ለኢትዮጵያ አዲስና ህዝቡም ሊያበረታታው እንዲሁም ሊያደንቀው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ኢህአዴግ መሆን አለመሆንን አይጠይቅም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ለስልጣን እየተገዳደሉ ባሉበት በዚህ ወቅት ቁጭ ብሎ ተነጋግሮ የአገርን መሪ መቀየር አንደኛ የዴሞክራሲ ባህልን መለማመድ መጀመራችንን የሚያሳይ መሆኑን፤ ሁለተኛ ስልጣን ለህብረተሰባዊ ለውጥ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ለግለሰቦች እንዳልሆነ ማሳያ ነው፡፡

ኢህአዴግም ይህን እርምጃ በመውሰዱ ትልቅነቱንና ለለውጡ የተዘጋጀ ድርጅት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከእዚህም በተጨማሪ የለውጥ አመራሮች ብለን የምንጠራቸው የኢህአዴግ አመራሮች ቁርጠኝነትንም ያረጋገጠም ነው፡፡ በድርጅት ደረጃ የተወሰኑትን ጉዳዮች የለውጥ አመራሩ የራሱን ፈጠራ ጨምሮ ፈጣንና አብዛኛውን ህዝብ ያስደመሙ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ከእዚህ አኳያ አንዱና ትልቁ እውቅና መሰጠት ያለበት ለድርጅታችን ሊቀመንበርና ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ ነው፡፡ እርሳቸው የወሰዷቸው እርምጃዎች በሙሉ በኢህአዴግ ደረጃ የተወሰኑ ናቸው፡፡ የማስፈጸም ብቃታቸው፣ ጥራቱና ፍጥነቱ ይበልጥ ከህዝቡ ጋር ወይም በህዝቡ ውስጥ ቅሬታ ፈጥረው የቆዩ ጉዳዮችን የፈቱ ናቸው፡፡ ለአብነትም ዴሞክራሲን ለማስፋት የተወሰዱ እርምጃዎች በኢህአዴግ ደረጃ የታዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ የለውጡን መሪነት ለመቀበል የሚቸገሩ ሰዎች ካሉ ሀሳቡ ከተጨባጭ ሁኔታው የራቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንቱም የሚታይ የሚዳሰስና የሚጨበጥ ለውጥ በመሆኑ ነው፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- የከተማችን ምሁራንና ለውጡ እየተደጋገፉ ወይንስ እየተነቃቀፉ? ለውጡ ለምሁራኑ ያስገኘው ፋይዳስ ምንድነው?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* ለውጡ ህዝባዊ ነው ሲባል የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለተሳተፉበት ነው፡፡ በለውጡ ሂደት ላይ ሚና ያልነበረው የህብረተሰብ ክፍል የለም፡፡ በመሆኑም ምሁራን የሰላ ትችት በማቅረብ፣ ባገኙት አጋጣሚ ለውጡን ሊያሳኩ የሚችሉ አበርክቶዎችን በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ስለሆነም

***“በየደረጃው ያለው አመራር ውጤታማ ከሆነ ኢህአዴግ ውጤታማ ሆነ ማለት ነው”***

ምሁራን የለውጡ ደጋፊዎች እንጂ አደናቃፊዎች አይደሉም። ነገር ግን ለውጡ ጥልቅ ሪፎርምና ተሃድሶ ስለሆነ ወደፊትም ቢሆን መሰራት የሚገባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አንደኛ ለውጡ ተቋማዊ መሆን አለበት። ሁለተኛ እያንዳንዱ አካል በሚያወራውና በሚያቀርበው ሃሳብ ልክ መስራት አለበት። ይሄ ደግሞ በሂደት እየተረጋገጠ የሚሄድ ነው።

እያንዳንዱ ዜጋና ምሁሩ ከእርሱ የሚጠበቀውን ከሰራ መንግስትና ድርጅት ደግሞ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ከተወጡ ለውጡ ተሳካ ማለት ነው። ስለዚህ አጠቃላይ ምሁራን ውስጥ ያለው አተያይ ጅምሩ ጥሩ ነው። ነገር ግን ገና መጠናከር የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ መታወቅ አለበት። ለውጡ ለምሁራን እያስገኘው ካለው ጥቅም አንጻር አንዱ ለውጡ ያመጣው ማንኛውም ዜጋ ሃሳቡን በነጻነት እንዲገልጽ ማድረግ መቻሉ ነው። ስለዚህ በየትኛውም አካባቢ ሃሳብን በነጻነት መግለጽ የቻለ ዜጋ ሁሉ የለውጡ ተጠቃሚ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ሁለተኛው ሃሳቡን በመጻፍና በመተቸት ነው። አሁን ላይ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ አቋምን ህጋዊና ሰላማዊ አድርጎ ማራመድ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን መለማመድ እነዚህ በሙሉ የለውጡ ትሩፋቶች ናቸው።

ነገር ግን አንድ እያጋጠመ ያለ ችግር አለ። ሁሉም ዜጋ ሃሳቡን በነጻነት መግለጽ አለበት መገደብ የለበትም ብለን፣ የለውጡ ማዕከል አድርገን ዴሞክራሲን ከማስፋት ጋር አያይዘን ምህዳሩ መስፋት አለበት ብለን፣ በርካታ ሚዲያዎች እንዲከፈቱ፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በፈለጉበት መንገድ እንዲደራጁ ትጥቅ ትግል ጭምር ያደርጉ የነበሩ ፓርቲዎች በሰላማዊ መንገድ ገብተው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ኢህአዴግ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። ይህንንም ምቹ ሁኔታ አብዛኛው ወገን በአግባቡ እየተጠቀመ የሚገኝ ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ ባልተገባ መንገድ ለመጠቀም ሲሯሯጥ ይስተዋላል። ይሄ መስተካከል አለበት። ከእዚህ አኳያ አንዱና ትልቁ ችግር የሚዲያ አጠቃቀማችን ላይ ነው። በተለይ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን።

ለውጡ ያመጣውን ትሩፋት በመጠቀም ወይም የለውጡ ማዕከል የሆነውን የዴሞክራሲ ምህዳር

"ችግር ስለደረሰ ኢህአዴግ ተዳክሟል፤ አገር መምራት አይችልም አብቅቶለታል የሚሉ አስተያየቶች ይነሳሉ። እነዚህ አስተሳሰቦች የኢህአዴግን የኋላ ታሪክ በሚገባ ካለመገንዘብ የሚመነጩ ናቸው። ኢህአዴግ የትኛውንም ችግር የማለፍ ብቃት የአለው ድርጅት ነው።"

*"ነጻነት፣ መብት፣ ዴሞክራሲ አንዱ ከሌላው አይነጣጠሉም፤ አንዱን መጉዳት ሌላውን ይጎዳል።"*

የማስፋት ዕድል ተጠቅሞ አዳዲስ የሚዲያ ተቋማትን ከፍተዋል፡፡ በብዙ መልኩ የሚያስቧቸውን ነገሮች ማስተላለፍ የሚፈልጉ አክቲቪስቶች፣ ጦማሪያንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ለውጡን በበለጠ መንገድ የሚያጠናክር ሳይሆን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ጥላቻና ግጭትን ሊቀሰቅሱና ሰላምን ለማድፍረስ የሚችሉ ነገሮችን የሚሰብኩ አሉ፡፡ የሀሰት መረጃን የሚያሰራጩ ሰዎች ከፍተኛ ውዥንብርና አሉባታ በተለይ ማህበራዊ ሚዲያን ተጠቅመው እዚህች አገር ሁከት እንዲነሰራፋ የሚጥሩ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡

እነዚህ አካላት ለማንም ሳይሆን ለአገራችን፣ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ሲባል በእጃቸው የሚገኘውን ሃብት ሲጠቀሙ ጥሩ አገር እንዲኖረን ለሚያግዝ ገንቢ ነገር መሆን አለበት፡፡ መንግስትን መተቸት፣ አመራሩን ሂስ ማድረግ ማለት አሉባልታ፣ ውዥንብርና በሬ ወለደ የሆኑ የሃሰት መረጃዎችን ማሰራጨት ማለት አይደለም፡፡ ይሄም የራሱ የሆነ ህግና ገደብ አለው፡፡ ስለዚህ በህጉ መሰረት አገር በሚያለማና በሚቀይር መንገድ ሚዲያዎችን በመጠቀም ረገድ ሰፊ ተግዳሮት ነው የገጠመን፡፡ በዋናው ሚዲያችንም ተመሳሳይ ነገር ነው ያለው፡፡ በጋራ ሰርተን በሚቀጥሉት ጊዜያት ማስተካከል ከሚገቡን ጉዳዮች አንዱ ይህ ዘርፍ ነው፡፡

ለውጡ ያመጣቸው ትሩፋቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ግን በተዛባና ባልተገባ መንገድ በመስራታቸው ለውጡን እየተፈታተነው ስለሆነ መታረም ይገባዋል፡፡ ለምሳሌ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ብንወስድ በአሁኑ ሰዓት ቁጥራቸው ከፍ ያለ እየተደራጁ ነው፤ አዲስ አበባ ላይ ማዕከል አድርገው መንቀሳቀሳቸውም ጥሩ ነው፤ በጋራ እንሰራለን፡፡ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከማንኛውም የተፎካካሪ ፓርቲ ጋር ቁጭ ብለን በመነጋገር በጋራ እንሰራለን፡፡ የጋራ በሚያደርጉን ጉዳዮች ላይ እንደ አንድ አገር ዜጋና እንደ አንድ ከተማ ነዋሪ በጋራ እንሰራለን፡፡

እንደ ፓርቲ ደግሞ ለያዝነው ፍልስፍና የየራሳችንን እንሰራለን፡፡ ሄዶ ሄዶ ግን የአገርን ሰላምና ልማት እንዲሁም ዴሞክራሲን ከማጎልበት በላይ ሌላ አጀንዳ መኖር የለበትም፡፡ ከእዚህ ውጪ የሚንቀሳቀሱና ጽንፈኛ ብሄርተኝነትን፣ ዘረኝነትን፣ ውዥንብርን፣ አሉባልታን መነሻ አድርገው ወደ ግጭት የሚሄዱ፣ ለዛም የሚሰሩና የሚሰብኩ፣ አንዳንዴ ደግሞ ጥቃት የሚፈጽሙ ኃይሎች አሉ፡፡ እነዚህ ሃይሎች ከዚህ ድርጊታቸው ይቆጠባሉ በሚል በማዕከላዊ መንግስት ጭምር ጥሪ ተላልፏል፡፡ ለውጡ ያመጣላቸውን እድል ተጠቅመው መልሰው ለውጡን የሚያደናቅፍ ስራ ከመስራት ይልቅ ሰላም፣ እኩልነትና ፍቅር የነገሰባት ኢትዮጵያን መገንባት ላይ ሊረባረቡ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እኛ ኢትዮጵያዊያን ጥላቻና መለያየት ፈፅሞ የማይመጥነን፣ የማይገባንም ነን፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡-በአዲሱ የበጀት ዓመት እንደ ድርጅት የምንከተላቸው አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* በአዲሱ የበጀት አመትም ዋናው ስራችን የሚሆነው የለውጡን ማዕከላዊ ነጥቦች የበለጠ አጠናክረን መቀጠል ነው፡፡ አንዱና ዋነኛው ከተማችን ለሁሉም ዜጋ ለኑሮ የተመቸች፣ የዴሞክራሲያዊ ባህል የጎለበተባት፣ የህግ የበላይነት የሰፈነባት አረንጓዴና ጽዱ፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባት እንድትሆን መስራትና ምቹ ከተማ መፍጠር ነው፡፡ በዚህም የልማት ስራዎቻችንን የስራ ዕድል መፍጠር፣ በዝቅተኛ ገቢና በኑሮ ውድነት የሚሰቃዩ ዜጎቻችን የኑሮ ሁኔታ እንዲቀየር ማድረግ ነው፡፡ ለከተማችን እድገትና ለነዋሪዎቿ ብልጽግና የጀመርነውን ስራ በማዝለቅ አስተማማኝ ሰላም፣ ዜጎች ያለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ ወጥተው የሚገቡባት ከተማ እንድትሆን ለማድረግ ከህብረተሰቡ ጋር መስራት፣ ከመላው ህዝቡ ጋር በጋራ ሆነን የህዝቡን እውነተኛ ተሳትፎን የሚያረጋግጡ ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል ከተማችንን መቀየር ነው፡፡

*ዓውደ ለውጥ፡- በመጨረሻ ሰሞኑን በአዲስ አበባና በባህርዳር ከተፈጠሩት ወቅታዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?*

*አቶ ተስፋዬ፡-* እንደ አገርና እንደ ከተማ የተፈጸመውን ድርጊት በተመለከተ በታሪካችን እጅግ በጣም አሳዛኝ ከሆኑ ክስተቶች ውስጥ በከፍተኛ አመራሮቻችን ላይ የተፈጸመው የግድያ ወንጀል አንዱ ነው፡፡ በአማራ ክልል ላይ በጣም ውድ የሆኑ የድርጅታችን አመራሮች ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ይሄ ጥቃት

***“ይሄ ጥቃት በየትኛውም መስፈርት፣ በየትኛውም ስሌት፣ በምንም ሁኔታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡”***

በየትኛውም መስፈርት፣ በየትኛውም ስሌት፣ በምንም ሁኔታ ተቀባይነት ያለው አይደለም። በሀገራችን ማንኛውም ኃይል ሥልጣን የሚይዝበት መንገድ የጠመንጃ አፈሙዝ መሆኑ ማቆም አለበት ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ ወስኗል። በሕገ መንግስታችንም የተቀመጠ ነው። ስለዚህ በባህርዳር ላይ በድርጅታችን አመራሮችና ታጋዮች ላይ የተፈፀመው ጥቃት ሰብዓዊነት የጎደለው በጭካኔ የተሞላ፣ ነውረኛና አረመኔያዊ ተግባር ነው። ይሄን ማንም ሰው ማውገዝ አለበት። መላው አመራራችንና አባላችን እንዲህ አይነት ነገር ተመልሶ እንዳይከሰት አምርሮ መታገልና ማውገዝ አለበት። እንዲሁም አገርን እየመሩ ያሉና አገራችን ካፈራቻቸው ውድ ከሚባሉ ጄኔራሎች በተለይ በኢታማዦር ሹሙ አዲስ አበባ ላይ የተፈፀመው ጥቃት እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላበትና ዘግናኝ ነው። በባህርዳርም ሆነ በአዲስ አበባ የተፈፀመው ጥቃት በጥቅሉ ሲታይ ግለሰቦች ላይ ወይም ቡድኖች ላይ የተቃጣ ጥቃት አይደለም። አገር ላይ የተቃጣ ጥቃት ነው። ህገ መንግስቱ ላይ የተቃጣ ጥቃት ነው። መላው ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመ ጥፋት ነው።

ይሄንን ጥቃት ኢትዮጵያዊያን አንድ ላይ ሆነን በአንድ ድምፅ መደገም የለበትም ብለን ማውገዝ አለብን። ስለዚህ መላው አመራር አባላችንና ደጋፊያችን በዚህ ዙሪያ ምንም ዓይነት ብዥታ ሊኖረው አይገባም በአንድ ድምፅ ሊያውግዘው ይገባል።

ሁለተኛ የተፈጸመው ክስተትና ጥቃቱ ሲታይ በጣም አስከፊና አስደንጋጭ ነው። ኢህአዴግ ልምድ ያለው ድርጅት በመሆኑ እና ለበርካታ ጊዜያት የተለያዩ ቀውሶችን ያለፈ ድርጅት ባይሆን ኖሮ አገርን ጭምር አደጋ ላይ የሚጥል ጥቃት ነው የተፈጸመው። ነገር ግን ምንም ያክል አስከፊና ከባድ ቢሆንም በጋራ ሆነን ይህን ማለፍ እንደምንችል መላው አመራር፣ አባልና ደጋፊያችን በሙሉ ልቡ ማመን አለበት። ብዙ አይነት ችግሮችን አልፈን እናውቃለን። እንደ ድርጅትና እንደ መንግስት ነገሮችን የማለፍ ብቃትና ችሎታ ያለን ነን። ስለዚህ አሁን ያጋጠመን ችግር አንድ ላይ ሆነን በጋራ ሰርተን ተጋግዘንና ተባብረን ማለፍ እንችላለን። የተሰው ጓዶቻችንን የምንክሳቸው የተሰውለትን የለውጡን ዓላማ ከግብ በማድረስ ብቻ ነው።

ከዚህ አኳያ አንዳንድ ነገሮች ግልጽ መሆን አለባቸው ብዬ የማምናቸው መጀመሪያ በዚህ ጥቃት ዙሪያ ብዙ ዓይነት አሉባልታና ውዥንብሮች ይነዛሉ። አሁንም ተመልሶ ለሌላ እልቂት የሚዳርጉ ወሬዎች ይናፈሳሉ። እነዚህ ማንንም ስለማይጠቅሙ አባሉ፣ አመራሩና ደጋፊዎቻችን ህብረተሰቡን የማስገንዘብ ስራ መስራት ይጠይቃል። ስለዚህ መጀመሪያ ላይ ራሳችን ንቁና ግልጽ መሆን አለብን። ቀጥሎ በህዝብ የመሪነት ሚና እንደተሰጠው መሪ ድርጅት ለህዝቡ ትክክለኛውን ነገር በማስረዳት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት ይጠበቅብናል። ስለሆነም ውዥንብር በመንዛት ችግር ሊፈጥሩ የሚያስቡ አካላትን በቃችሁ ልንላቸው ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ ይህ ችግር ስለደረሰ ኢህአዴግ ተዳክሟል፤ አገር መምራት አይችልም አብቅቶለታል የሚሉ አስተያየቶች ይነሳሉ። እነዚህ አስተሳሰቦች የኢህአዴግን የኋላ ታሪክ በሚገባ ካለመገንዘብ የሚመነጩ ናቸው። ኢህአዴግ የትኛውንም ችግር የማለፍ ብቃት የአለው ድርጅት ነው። በመሆኑም አሁን ከገጠመን ችግር ተነስተን ለምን ተፈጠረ የሚለውን በዝርዝር ገምግመን በውስጣችን ያለውን ችግር በደንብ አጥርተን የበለጠ ተጠናክረን መውጣት የምንችልበት እንጂ ድርጅታችንን የሚያፈርስ ሊሆን እንደማይችል መላው አመራርና አባል አውቆ መንቀሳቀስ አለበት።

የከተማችን ነዋሪዎችም እንደተለመደው በአገራችን አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን፤ የተጀመረው የለውጥ ጉዞ እንዲሳካ፤ በአፍሪካ ቀንድ ያለውን ቀውስ በመፍታት ቀደም ባሉት ጊዜያት ሀገራችን የነበራትን ልምድ በመጠቀም ተቋቁማ እንደመጣችው ሁሉ በቀጣይም ወደ ከፍታው ማማ እንድትሸጋገር የጀመረውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በየተሰማራንበት መስክ በማበርከት የራሱን አስተዋጽኦና አሻራ በማስቀጠል ለውጡ ግቡን እንዲመታ ከድርጅታችንና ከመንግስት ጎን መሰለፍ እንደሚገባው በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

*“የተሰዉ ጓዶቻችንን የምንክሳቸው የተሰዉለትን የለውጡን ዓላማ ከግብ በማድረስ ብቻ ነው።”*


መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ/ም ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ስርዓተ ሲመታቸው ሲካሄድ አዲስ አበባችን እንዲህ ነበረች፡፡ በዚህ ምስል ላይ ከሚታዩት ዛሬን የዘለቀች ሰንደቃችን ብቻ ነች፡፡





በመዲናችን ዘመናዊ የዳቦ መጋገሪያ ፋብሪካ ሲገነባ መሆኑን ሠቼም ሰምተዋል፡፡ የዳቦ ጉዳይ አይደል እስኪ ለዚህ በድመት ቅርፅ ለተጋገረው ዳቦ ማስፈያ ካኘሽን ይፃፉልትና በኢሜይል አድራሻችን ይላኩልን፡፡

awdelewt@gmail.com



*ጀምስ ጋረፊልድ 20ኛው የአሜሪካ ፕሬዜዳንት ብቸኛው ግራኝ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ በአንድ እጃቸው ላቲንኛ በሌላኛው ደግሞ ግሪክኛ በአንድ ጊዜ በመፃፍ የታወቁ መሪ ነበሩ፡፡*

# በጎ ፈቃደኝነት ከዘመቻ ወደ ባህል

በዘመን ጆነዲ



## 1. መግቢያ

የሰው ልጅ ከውልደቱ እስከ እድገቱ ባለው ጊዜ  የቤተሰቡ፣ የራሱ፤ የእምነቱ፤ የአካባቢው፣ ብሎም በትምህርት ቤት ህይወቱና በቅርበት የሚመለከተው አካባቢ ባህሪ ውህድ ነው። ከዚህ አኳያ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ከቤተሰቡ ከወረሰው ባህሪ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው የሚያድግበት አካባቢም ተጽዕኖ ያሳድርበታል። ከዚህ አኳያ የሰው ልጅ በአካል፣ በስነምግባርና በእውቀት በአዎንታም ሆነ በአሉታ መልማት የሚችለው ከልጅነት ጀምሮ በሚያልፉቸው መንገዶች መሆኑ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይሆንም። ግለሰብን ከዛም አለፍ ሲል ህብረተሰብን መርዳትም ሆነ ሀገርን በቅንነት ማገልገል አብሮ ከሚወለድ ሰውኛ ባህሪ ባሻገር ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከሚያድጉበት ማህበረሰብ፤ ከሚከተሉት እምነትና ከሚያራምዱት የህይወት ፍልስፍና የሚቀዳና የሚለመድ መልካም ምግባር ነው። የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም ከራስ ውስን ሀብት ቆርሶ ለሌላ የሚሰጥ ጊዜ፣ ጉልበትና እውቀት በመሆኑ በዚህ መልካም ምግባር ውስጥ ለመሳተፍ የበጎ ፈቃደኛው ማንነትና እምነት ወሳኝ ነው።

## 2. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንነት

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማለት ያለ ምንም ቁሳዊ ትርፍ  ራስን ለሌሎች የመስጠት አገልግሎት ነው ማለት ይቻላል። አንድ ሰው ለለፋሁበት፤ ይህን አገልግሎት ለሰጠሁበት ይከፈለኝ ሳይል ከገንዘብ በላይ ለሚያገኘው እርካታ በግል አልያም ከመሰሎቹ ጋር በህብረት ሌላውን የሚያገለግልበት መንገድ ነው። አንድ ሰው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሲሰጥ ራሱን እንደማደስ ይቆጠራል ይላሉ በፅንሰ ሃሳቡ ዙሪያ ሃሳባቸውን ያሰፈሩ ጸሀፍት። የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የራስን ህይወት በማነፅ ረገድም ወደር የለውም። የበጎ ፈቃድ



***የአሜሪካ የኒውክለር ጦር መሳሪያ በጀት የሚመደበው በመከላከያ ሚኒስቴር በኩል ሳይሆን በኢነርጂ ልማት ሚኒስቴር በኩል ነው።***

አገልግሎት የራስ መተማመንን ይጨምራል፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ለመርዳት ሲጥርና በተግባር ያንን ሲያደርግ የራሱን መልካም ማንነት እየገነባና በውስጥ ይቻላል የሚል መንፈስን ጭምር እያዳበረ እንደሚሄድ መገመት አያዳግትም፡፡


ሌላው ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ ግለሰቦች ጤናማና ረጅም እድሜ እንደሚኖሩም ይገለፃል፡፡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሙሉ አካል ከአዕምሮ ጋር ተዳምሮ የሚሰጥ አገልግሎት እንደመሆኑ በራሱ ለጤናማ ህይወት ጭምር ወሳኝም ነው ይላሉ በዘርፉ ላይ ረጅም ጊዜያት ጥናትና ምርምር ያደረጉ ምሁራን፡፡ ከዚህ በግለሰብ ደረጃ ከሚመዘን ስነልቦናዊ ጥቅም ባሻገር የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሀገር የሚያበረክተው ማህበረሰባዊ ጥቅሙ የጎላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ቤተሰባዊ ፍቅርን በማጠናከር፣ አካባቢያዊ ትስስርን በማጎልበት፣ አብሮነትን በማጎልበት፤ አዲስና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ወዳጅነት ለመመስረትም ወሳኝ ነው፡፡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሚዛናዊ የሆነና ከጨለምተኝነት የፀዳ፤ የነገውን ብርሀን በውጣ ውረድ ውስጥ አሻግሮ የሚያይና ለችግሮች እጅ የማይሰጥ ጠንካራ ትውልድ በመገንባት ረገድ የላቀ ፋይዳ አለው፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አንድ ሰው በሰለጠነበትና ማህበረሰቡን በተሻለ መንገድ ማገልገል እችላለሁ ብሎ በሚያስብበት ማንኛውም መስክ የሚሰጥ አገልግሎት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ህብረተሰባዊ ለውጥ ለማምጣት ጭምር መሰረት ነው፡፡

## *2.1. የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዓለም አቀፋዊ ገፅታ*

በቅርብ ጊዜ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመላክተው በመላው አለም ያሉ ወጣቶች ከ35 ቢሊዮን በላይ የሚሆን ሰዓታትን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያውላሉ፡፡ በዓለም ነባራዊ ሁኔታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት 27 በመቶ ከፍተኛ ስራ የመቀጠር እድል እንደሚያስገኝ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተመለከተ በሚያወጣው ሪፖርት ተመላክቷል፡፡

የተመድ ሪፖርት እንደሚያሳየው ወጣቶች በተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም በውስጣዊና ውጫዊ የኮሙኒኬሽን ስራ፣ በድረ ገጽ፣ ማህበራዊ ሚዲያና መሰል ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ በበጎ ፈቃደኝነት ፕሮግራሙን እያገዙ ይገኛሉ፡፡ እንደ ድርጅቱ ሪፖርት ከሆነ በአመት 6 ሺህ 500 ወጣት የኢንተርኔት በጎ ፈቃደኞች ተመድን ያገለግላሉ፡፡ እንደ ተመድ መረጃ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት የሆኑ 1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ወጣቶች በአለም ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ የወጣት ስብስብ ማህበራዊ ለውጥ በማምጣት፣ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችንና የሪፎርም ስራዎችን በማፍለቅና ውጤታማ በማድረግ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ወጣቶች የሰላምና መረጋጋት እጦት፤ አሉታዊ የአየር ንብረት ለውጥ፤ ስጋት እየሆነባት ላለችው አለም ሰላምና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት፤ ለኑሮ ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ስነ ምህዳር ለመፍጠር ወሳኝ ከመሆናቸው አኳያ የዓለም መንግስታት የወጣቶችን ተሳትፎ ለማጠናከር በጎ ፈቃደኝነት አንዱ አማራጭ መሆኑ ይታመናል፡፡ የተለያዩ አካላት ወጣቶች ለዓለም ሰላምና ልማት ካላቸው ፋይዳ አንፃር አሁንም ዓለም በደንብ እየተጠቀመባቸው አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ይህንን በማጤን የበጎ ፈቃደኞች ድርጅትን በ1970 እ.ኤ.አ አቋቁሟል፡፡ በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ለማበረታታት ለአገልግሎት እውቅና በመስጠት ጭምር ሰይሟል፡፡

በታሪክ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ትርጉም በቅጡ ተመዝግቦ መታወቅ የጀመረው በ1755 እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ቃሉ ቮለንቴሪ ከሚል የፈረንሳይኛ ቃል እንደተወሰደም ይነገራል፡፡ ትርጉሙም ራሱን ለውትድርና ያዘጋጀ ፈቃደኛ ሰው የሚሰጠው ስያሜ ነው፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሁንም ድረስ ከወታደራዊ አገልግሎት መስጠት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ትርጓሜ ነው ያለው፡፡ አንድ ዜጋ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በኋላ ይህን የውትድርና አገልግሎት ማለትም አገሩን በዚህ የማገዝ አገልግሎት ዛሬም በተለያዩ አገራት እየተከናወነ



*አሜሪካ ለእግረኛ ጦር ጀግኖች ተዋጊዎቿ ከሸለመችው 2500 የክብር ሜዳሊያ ውስጥ 1 ሺህ 198ቱ የተሰጡት የዛሬዋ አንድነቷ የተጠበቀ አሜሪካን ለመገንባት በተደረገ የእርስ እርስ ጦርነት ገድል ለፈፀሙ ወታደሮች ነው፡፡*

ነው።

በ1981 የመጀመሪያው በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ የሚሰራ የወጣት ክርስቲያን ወንዶች ማህበር “ወወክማ” ቀጥሎም የወጣት ክርስቲያን ሴቶች ማህበር “ወሴክማ” ተመሰረተ። በአሜሪካ የእርስ በእርስ ጦርነት ሴቶች ህይወታቸውን ለወታደሮች ቁሳቁስ በማቅረብ መስዋዕት ማድረግ ጀመሩ። በጊዜው የጦር ግንባር መልዓክ፤ በመባል ትጠራ የነበረችው ክላራ ባርተን እና ቡድኖቿ ለወታደሮች ድጋፍ ማድረግ ጀመሩ። ይህች እንስት የአሜሪካንን ቀይ መስቀል ማህበር በ1881 ያቋቋመችና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶችን ማሰባሰብ የጀመረች በበርካታ የነፍስ አድን ስራ ላይ መሰማራት የቻለ የበጎ ፍቃድ ቡድን መስራች እንስት ናት። በአጠቃላይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አካባቢ በአሜሪካ ሰዎችን ለመርዳት በተለያዩ ጊዜያት የበጎ ፈቃደኞች ህብረት እንደተቋቋመ ይነገራል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በጦርነት የተጎዱ ወታደሮችን እገዛ የሚያደርግ የበጎ ፍቃደኞችን ስብስብ ያቀናጁ የነበሩ ተቋማት እዚህም እዚያም ብቅ ማለት ጀመሩ። የመገልገያ እቃዎችን ማሰባሰብ፣ ወታደሩን በፍቅርና በእንክብካቤ መሸኘትና የተጎዳውን መንከባከብ የበጎ ፍቃደኞች ተግባር ሆነ። ይህ ጦርነት ካበቃ በኋላ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት እየተለመደ የመጣ በመሆኑ ይህን ማህበረሰብን የማገልገል ውስጣዊ ፍላጎት በድህነት ላይ ያሉ ሰዎችን ለመርዳት ጭምር ተጠቀሙበት። የአሜሪካው ፒስ ኮርፕስ የበጎ ፈቃደኞች ማህበር በዚህ መንገድ የተመሰረተ ሲሆን ዛሬ ዓለም ላይ አንጋፋ ከሚባሉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። እ.ኤ.አ በ1964 የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ሊንደን ቢ ጆንሰን በድህነት ላይ ጦርነት ሲያውጁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም ይበልጥ አብሮ ማደግ ችሏል። በ2012 በአሜሪካ በተደረገ ጥናት 26 በመቶ አሜሪካዊ ጎልማሳ 175 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የ7 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሰዓት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል። በ1960ዎቹ ትውልደ አርጀንቲናው የነጻነት ታጋይ ኤርኔስቶ ቼጉቬራ ማንኛውም ሰራተኛ በስራ ቦታው የተወሰኑ ሰዓታትን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት አውጆም ነበር። በአጠቃላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአገር መሪዎችም ጭምር አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመለወጥ ከፖሊሲዎቻቸው ጋር አጣምረው እንዲፈፀም የሚገፋፉት ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

አለም አቀፍ ስምምነት የተደረሰባቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ስንመለከት የመጀመሪያው የትምህርት ድጋፍ አገልግሎት መስጠት ይገኝበታል። ተማሪዎች ኃላፊነትን መውሰድና መሸከም እንዲችሉና ማህበረሰቡን ማገልገል አለብኝ የሚል ስሜት እንዲያዳብሩ በተማሪነት ዘመናቸው የዚህ አገልገሎት ተጠቃሚ ማድረግ መልካም ርምጃ እንደሆነ ይገለፃል። በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የትምህርት እገዛ የሚደረግላቸው ተማሪዎች አንድ ራሳቸውን ለማገዝ መልካም አጋጣሚ ከመሆኑ ባሻገር በማህበረሰቡ የሚደረግላቸው ድጋፍ እነሱን ለነገ ህይወታቸው የሚያዘጋጅና የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን እንዲለምዱ መሰረት የሚጥል ጭምር ነው።

ሌላው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዓይነት ሙያዊ የሆነ ድጋፍ ለማህበረሰቡ የሚሰጥበት ነው። አንድ በጎ ፈቃደኛ ግለሰብ በትምህርትና በልምድ የያዘውን እውቀት ተጠቅሞ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ህብረተሰቡን ማገልገል ይችላል። በመደበኛ የስራ ሁኔታ የጤና ባለሙያው፤ የጤና ባለሙያውን ዋጋ፤ መሀንዲሱም የመሀንዲሱን ዋጋ፤ የግብርና ባለሙያውም የሙያውን ዋጋ ብቻ ሁሉም እንደ ፈርጁ የልፋቱ ዋጋ ይሰጠዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ባለሙያ የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት ውስጥ ሲገባ ለላቤ፤ ለሙያዬ፤ ለሰራሁበት ዋጋ ይከፈለኝ ሳይል በሙያው ህብረተሰቡን ያገለግላል። ይህ በሁሉም ዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ዜጋ ከአገሩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር መፈፀም የሚችለው ምስጉን ተግባር ነው። አንዳንድ አገራት ላይ ሙያዊ የሆነ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት የተለመደ ቢሆንም ኢትዮጵያን በመሰሉ የአፍሪካ አገራት ላይ ግን ይህ ብዙም ያልተለመደና መሰራት የሚገባው ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተወለዱበት አካባቢና ህዝብ ብቻም የሚወሰን አይደለም። በጎ ፈቃድ አገልግሎት ድንበር ዘለል ነው። በአደጉ አገራት ያሉ በርካታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከአገራቸው አልፈው



*የጀርመን ወታደሮች በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የፓሪሱን ኤፍልታወርን ሲጎበኙ ፈረንሳዊያን የአሳንሰሩን ኬብል በመቁረጥ ወታደሮቹ በደረጃ መወጣጫ ሽቅብ እንዲወጡ አስገድደዋቸዋል።*

በማደግ ላይ ያሉ አገራትን ዜጎች ሲረዱና በሙያቸው ያለምንም ክፍያ ሲያገለግሉ ይስተዋላል፡፡ ይህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሌላ መልካም ገፅታ ነው፡፡ በማሳደጊያ ተቋማት፣ የህክምና ተቋማትንና ከመንግስት አስተዳደር ውጭ በሆኑ የበጎ አገልግሎት ሲጪ ተቋማት ውስጥ በመሳተፍ ድንበር ዘለል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

ሌላው በሁሉም የዓለም አካባቢዎች ብሎም በአገራችን በተለይ በክረምት መርሃ ግብር የሚፈፀሙና በርካታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶች የሚሳተፉበት የበጎ ፈቃድ አገልገሎት አይነት የአካባቢ ጥበቃ ነው፡፡ ይህ በአብዛኛው የዓለማችን ክፍልም በስፋት የሚፈፀም ሲሆን በአገራችንም በተለይ በክረምት ወራት ይተገበራል፡፡

በአደጋ ጊዜ የሚደረግ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም ሌላው ተጠቃሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዓይነት ነው፡፡ በተፈጥሮ አደጋ ጊዜ ማለትም የጎርፍ፣ የእሳት፣ የድርቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና መሰል አደጋዎች ሲፈጠሩ በጎ ፍቃደኞች በመረባረብ ለወገን ደራሽነታቸውን በተግባር ያሳያሉ፡፡ በዓለማችን ታሪክም በ2004 በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥና የሱናሚ፤ የካትሪን አውሎ ንፋሶች አደጋ፤ በምዕራብ አፍሪቃ ተከስቶ በነበረዉ የኢቦላ ቫይረስ ወረርሽኝ መከላከል ላይ በርካታ የዓለማችን የበጎ ፈቃደኞች የተሳተፉበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ 2012 የሃሪኬን የመሬት መንሸራተት /2012 hurricane Sandy emergency/ የበጎ ፈቃደኞች ምግብና አልባሳትን በማሰባሰብ ያደረጉት ርብርብ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አብሮነት፣" መተሳሰብና መደጋገፍ ጥቅም ለዓለም የታየበት ሆኖ አልፏል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማህበረሰቡ የሚያስብ ትውልድ በመቅረፅ በኩል ያለው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡ የትምህርት መስጫ ተቋማት ደግሞ ለዚህ አይነተኛ ማሳያ ናቸው፡፡ በአቅም ደከም ያሉ ትምህርት ቤቶችን የመማር ማስተማር ሂደት የተሳለጠ ለማድረግ በትምህርት ቤቶችም ይሁን በተማሪዎች በኩል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚሰሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ግለሰቦችም አሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችንና ሌሎችን በማስተማር ሂደት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ የሁለተኛና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማስጠናት ጊዜያቸውን መልካም ስራ በመስራትና ትውልድ በመቅረፅ የሚሰጥ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም ሌላው ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ሂደት ለተማሪዎች ተጨማሪ አቅም የሚፈጥርና የአቅም ክፍተታቸውን የሚሞላ ከመሆኑ ባሻገር የተማሪዎችን የእርስ በእርስ ትስስር የሚያጠናክር፣ ወንድማማችነትን የሚያዳብር፤ የተማሪዎችን ስነምግባር ለማነፅ መልካም አጋጣሚን የሚፈጥርና ለበጎ ፈቃደኛውም ሆነ አገልግሎቱን ለሚያገኙ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው ነው፡፡

ሌላው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዓይነት ከላይ ከተገለፁት ለየት ያለ ይዘት ያለው ነው፡፡ ኮርፖሬት በጎ ፈቃደኝነት ሲሆን ይህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአንድ ተቋም ሰራተኞች በመረጡት የእርዳታ ተቋም ውስጥ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጡ የድጋፍ አበል በመስጠት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የሚያበረታታ ስርዓት ነው፡፡ ተቋማት ራሳቸውን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰጡ ግለሰቦችን የሚያበረታቱበት ሁኔታ በተፈጠረ ቁጥር የበጎ ፈቃደኛው ቁጥር መጨመሩ እሙን ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስርዓት ተቋማት ውስጥ መፈጠሩ ሰራተኞችን በማቆየትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ወደር የማይገኝለት ስልትም ጭምር ነው፡፡

በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚሰጠው የማህበረሰባዊ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ሌላው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሆን ይህ አገልግሎት በቁጥር አነስ ያለ ሰው ተሰባስቦ ማህበረሰቡን የሚያገለግልበትና የሃይማኖትና ለትርፍ የማይንቀሳቀሱ ተቋማት በስፋት የሚሳተፉበት ነው፡፡ በአገራችን ይህ ዓይነቱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በርካታ ሲሆን ሰዎች በቡድን በመደራጀት የበጎ ፈቃድ አገልገሎት ለማህበረሰቡ ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ ስለ በጎ ፈቃድ ዓይነቶች ይህን ያህል ካልን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ለምን ያስፈልጋል የሚለውን ወደ ማብራራት እንሂድ፡፡



*ዩሚንግ-ከአሜሪካ ግዛቶች የሴቶችን የመምረጥ መብት ቀድማ የተቀበለች ግዛት ብቻ ሳትሆን ሴት አገረ ገዢን መርጣ ቀድማ የተመራችም ናት፡፡*

# *3. የተለያዩ አገራትን የበጎ ፍቃድ ተሞክሮ በወፍ በረር እንመልከት*

## *3.1. የአሜሪካን የሰላም ጓዶች /ፒስ ኮርፕስ/*

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በዓለም ታሪክ ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በነበሩት ጆን ኦፍ ኬኔዲ አነሳሽነት በአሜሪካ ኮንግረንስ ፀድቆ፣ በህግ ማእቀፍ ተደግፎ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ እውን የሆነው (የአሜሪካን የሰላም ጓዶች) ፒስ ኮርፕስ የተባለው የበጎ ፈቃድ ድርጅት ነው፡፡ ከአሜሪካ ውጪ ሰዎችን የመርዳት አላማ ያለውና የአሜሪካንን ባህል ጭምር በሌሎች ሀገራት ለማስረፅና የሌላውንም አለም ባህል ለመረዳት ያለመ ነበር፡፡ ፒስ ኮርፕስ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ አተኩሮ የሚሰራ የበጎ ፈቃድ ድርጅት ነው፡፡ በድርጅቱ በበጎ ፍቃድ ለማገልገል የፈለገ ሰው የመጀመሪያው መስፈርት የመጀመርያ ዲግሪ ያለውና የአሜሪካ ዜጋ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ዜጋ በበጎ ፍቃደኛነት ከተመዘገበ በኋላ ከአገር ወጥቶ ለ2አመታት ማገልገልም ግዴታው ይሆናል፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከ1961 እስከ 2015 እ.አ.አ ወደ 220 ሺህ የሚጠጉ አሜሪካውያን የፒስ ኮርፕስ አባል ሆነዋል፡፡ በ141 ሀገራትም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ፒስ ኮርፕስ (የአሜሪካን የሰላም ጓዶች) አሜሪካውያን አዳጊ ሀገራትን ጭምር ታች ድረስ ወርደው የማገዝ ፍላጎት እንዳላቸው በተግባር ያሳዩበትም ጭምር ነው፡፡

ፒስ ኮርፕስ (የአሜሪካን የሰላም ጓዶች) የሌሎች ሀገራት ዜጎች ለአሜሪካ ያላቸውን እይታ፣ አሜሪካውያንም ለሌሎች ሀገራትን የሚያዩበት መንገድ እና አሜሪካውያን ራሳቸው ሀገራቸውን እንዴት ማየት እንዳለበቸው ጭምር ያስተማረ የበጎ ፈቃድ ድርጅት ነው፡፡ ፕሬዝዳንት ኬኔዲ "ሀገሬ ምን ሰራችልኝ አትበሉ እኔ ለሀገሬ ምን ሰራሁ ብላችሁ ጠይቁ" በማለት ለወጣቶች የተናጋሩትም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ድርጅት መቋቋም ጋር ተያይዞ እንደሆነ ነው የሚነገረው፡፡ ይህ ንግግር ለአሜሪካውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው አለም ህዝብ ሁሉ ዘመን የማይሽረው መልእክት ሆኖ ዛሬም ድረስ ይኖራል፡፡

ፒስ ኮርፕስ (የአሜሪካን የሰላም ጓዶች) በአዳጊ ሀገራት ያለውን ችግር ለመፍታት የማስተማር አላማ ያለው እና ችግሮችን ቀድሞ መከላከልን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ አርሶ አደሮች ምርታቸው እንዲጨምር የዘመናዊ እርሻ ስልጠና ይሰጣል፣ እኩል የትምህርት እድል ለሁሉም በሚልም ይሰራል፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ ወባን በመከላከል፣ በአደጋ ወይም በቀውስ ጊዜ አገልግሎት መስጠት እና በሰላም ዙሪያ ትኩረት አድርጎ ይሰራል፡፡

## *3.2. የቻይና ወጣት በጎ ፍቃደኞች ማህበር*

በ1993 እ.ኤ.አ የተመሰረተው የቻይና ወጣቶች በጎ ፈቃድ ማህበር በመላው ሀገሪቱ በስፋት የተስፋፋ ሲሆን 89 ሺህ የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከላትና ከ100 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞችን የያዘ ነው፡፡ በዚህ ማህበር 110 ሚሊዮን ወጣቶች ከ4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሰዓታት በላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለህብረተሰቡ አበርክተዋል፡፡

ድህነትን በመቀነስ ረገድ የቻይና በጎ ፈቃድ ወጣቶች ማህበር በአገሪቱ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ጭምር ይነገራል፡፡ የቻይና የወጣቶች የበጎ ፈቃድ ማህበር የህክምና እርዳታና መሰል አገልግሎቶችን በገጠር አካባቢዎች ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ይህ ማህበር በጎ ፈቃደኞችን በክረምት መርሀ ግብር ከፍተኛ ድህነት ያለባቸውና ኋላቀር ወደሚባሉ አካባቢዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ያሰማራል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ



*በ1705 (እ.ኤ.አ) የሩሲያው ንጉስ ታላቁ ጴጥሮስ ፂማሞች ተጨማሪ ግብር እንዲከፍሉ ያደርጉ ነበር፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ እንደ ምዕራባዊያን ወንዶች እንዲላጩ ለማስገደድ ነበር፡፡*

መሰረት በዚህ የክረምት ወራት አገልግሎት 10 ሚሊዮን የኮሌጅ ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡

ሌላው በዚህ ማህበር የሚደገፈውና ተመሳሳይ ተልዕኮ ያለው የቻይና ድህነት ቅነሳ በጎ ፈቃድ ወጣቶች ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ በ1996 እ.አ.አ ተቋቁሞ ሰፊ ስራ ያከናወነ ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ በከተማ የሚኖሩ ወጣቶችን በማነሳሳትና በማደረጃት ከ6 ወር እስከ 2 አመት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከፍተኛ ድህነት አለባቸው በሚባሉት ምዕራባዊ ቻይና አካባቢዎች ሰጥቷል፡፡ ይህ ፕሮግራም በምዕራብ ቻይና ገጠራማ ግዛቶች በድህነት ቅነሳ እና ዜጎች የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ በማስቻል ረገድ አመርቂ ለውጥ አምጥቷል፡፡

የቻይና በጎ ፈቃድ ወጣቶች ማህበር ለማህበረሰቡ የተለያየ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር በማህበረሰባዊ ግንባታ ላይም ይሳተፋሉ፡፡ በ1994 እ.ኤ.አ አንድ ሰው ለአንድ የሚል ስያሜ በተሰጠው ፕሮግራም ወጣቶች ለአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ብቻ የተለየ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በዚህ ፕሮግራም በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን በማፈላለግና ከአንድ የማህበረሰብ አካል ጋር በመጣመር ለረጅም ጊዜ አብረዋቸው በመቆየት የተለያየ እገዛ በማድረግ አገልግለዋል፡፡ የቻይና በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ማህበር ባከናወነው መጠነ ሰፊ የበጎ ፈቃደኝነት ስራ ሞዴል የወጣቶች ኮምዩኒቲ/ማህበረሰብ የተመሰረተ ሲሆን እስከአሁን ባለው መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ 1000 የወጣቶች ሞዴል ኮምዩኒቲ እና 3000 የሚሆኑ ደግሞ በግዛቶች ደረጃ ሞዴል የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ተፈጥረዋል፡፡

## 4. በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ቅኝት

በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተጀመረበት ትክክለኛ ጊዜ በውል ባይታወቅም በህብረተሰባችን ዘንድ ያለው ማህበራዊ ትስስርና እርስ በእርስ የመደጋገፍ ባህል ስር የሰደደ እንደሆነ መግለፅ ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ በተለይ በችግር ጊዜያት በነበረው ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተጎዱና እገዛ የሚያስፈልጋቸውን የታመሙና አቅመ ደካሞችን የአቅማቸዉን አዋጥተውም ቢሆን የመርዳት ባህላቸው ጠንካራ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአገራችን የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለውና ከህዝባችን እለታዊ ማህበራዊ መስተጋብሮች ጋር የተቆራኘ አገልግሎት እንደሆነ ታሪካችን ያሳየናል፡፡

በተመሳሳይ የአገራችን ህዝቦች የሚያጋጥሟቸውን የኑሮ ውጣ ውረዶችን፣ የአቅም ውሱንነቶችን ለመቋቋም የሚረዱ እንደ እቁብ፣ እድር፣ ደቦ፣ ጂጊና ወንፈል የመሳሰሉትን እርስ በእርስ መልካም ጉርብትናና መዛመድ ይፈጥራሉ፤ ለመተጋገዝና ለመተባበርም መልካም አጋጣሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን አሰራሮችን በፍላጎታቸው በመተግበር ማህበራዊ ቀውሶችን ለመከላከል ለዘመናት ሲተገብሩት የነበረው አሰራር ተቋማዊ ባያደርጋቸውም ማህበረሰባችን የበጎ ፈቃደኝነትን መርሆዎችን ቀድሞ መገንዘቡንና መተግበሩን የሚያሳዩ አንኳር ተግባራት ናቸው፡፡

በ1930ዎቹ የፋሺስት ኢጣሊያ መንግስት አገራችንን ዳግም በወረረበት ወቅት ጀግኖች አርበኞች ከፋሺስት ጦር ጋር በወቅቱ ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግል በደረሰው ጉዳት በየማዕዘኑ ያለው የአገሪቱ ህዝብ ርብርብ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ከዚህ በበጎ ፈቃደኝነት በውስጥ ከሚደረግ መተጋገዝ ባሻገር በየአካባቢው ጉዳት የደረሰባቸውንና የቆሰሉ ወታደሮችን በመንከባከቡ ሂደት ድንበር ተሻጋሪ የውጭ አገራት በጎ ፈቃደኛ ዜጎች በተለይም የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ አባላት ለዜጎቻችን ያበረከቱት ሰብዓዊ አገልግሎት በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተቋም መመስረት መሰረት መጣሉ ይነገራል፡፡ እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም የተመሰረተው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር እንዲሁም በ1934 ዓ.ም የተመሰረተው የኢትዮጵያ ስካውት ማህበር በእነዚህ የውጭ አገር በጎ ፈቃደኞች አማካኝነት በተፈጠረ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ፅንሰ ሃሳብና አስፈላጊነት ማህበረሰባችን በመረዳቱ እነዚህ ተቋማት እውን እንዲሆኑ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ በዘውዳዊ አገዛዝ ዘመን በ1960ዎቹ እንደተመሰረተ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ በበጎ ፈቃድ



*አንድ ቀን የሰው ልጅ መኖሪያው እንደሚሆን የሚታሰበው ማርስ ፕላኔት የራሱ ሰንደቅ ዓላማ ከወዲሁ ተበጅቶለታል፡፡ በፕላኔታሪ ሳይንቲስት ቻይናዊው ፓስካል ሊ በ1998 የተነደፈው ይህ ሰንደቅ ዓላማ ሶስት ቀለማት ቀይ አረንጓዴ ሰማያዊ ቀለማት ጎን ለጎን የተቀመጠለት ነው፡፡*

አገልግሎት መስፋፋት ዙሪያ የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ እ.ኤ.አ በ1962 ዓ.ም ከውጭ አገር የመጡ 279 የአሜሪካን የሰላም ጓዶች /Peace Corps/ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ፅንሰ ሃሳብ ይበልጥ በማህበረሳባችን ውስጥ እንዲሰርፅ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ከሁሉ በላይ ከ1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የተለያዩ ስያሜና ዓላማዎችን በመያዝ በመንግስት የተከናወኑ ማህበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ የሰላም ጓድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዘመቻ፣ የፊደል ሰራዊት የበጎ ፈቀድ አገልግሎት ዘመቻ፣ የጸረ- ወባ ዘመቻ፣ የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የስራ ዘመቻ እና የመሠረተ ትምህርት ዘመቻዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት በበጎ ፈቃደኞች የተከናወኑ ተግባራት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲጎለብት መሰረት ሆነዋል፡፡

በ1996 ዓ.ም ተቀርፆ ወደ ስራ የገባው የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ፖሊሲ ወጣቶች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የአካባቢ ጥበቃና ማህበራዊ አገልግሎት እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት ተሳትፈው እራሳቸውንና ማህበረሰባቸውን ሊጠቅሙ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ ፖሊሲ መነሻ የተቀረጸው የኢትዮጵያ ወጣቶች እድገት ፓኬጅም የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች በመንግስት የወጡ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኘሮግራሞችን መሰረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የማስፈጸሚያ ስልቶች ተነድፈውላቸው ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባና እንዲሁም መንግስት በቀየሰው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ አተገባበር ዙሪያ የራሳቸውን ተሳትፎ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ሊያረጋግጡ እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

በአገራችን ህገ መንግስቱ የሰጣቸውን የመደራጀት መብት ተጠቅመው የተደራጁ የተለያዩ የወጣት አደረጃጀቶች በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ እነዚህ አደረጃጀቶች በዋናነት የወጣቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ዋነኛ ተልዕኮአቸው ቢሆንም ህብረተሰባዊ ለውጥ ለማምጣት የሚተጉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ህብረተሰባቸውን ያለማንም ገፋፊነት ለማገልገል የሚያስችል ስብዕና ባለቤት መሆንም አለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይህንን ፍላጎት ተፈፃሚ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የወጣት አደረጃጀቶች በአገራችን የሚሰጡት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክረምት ወራት ብቻ የታጠረ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የበጎ ፈቃድ ከደረሰበት አለም አቀፋዊ ደረጃ አኳያ በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልገሎት በተናጥል ካለው የመረዳዳት ህበረተሰባዊ መሰረት ባሻገር በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ከመምራትና ለሀገራዊ ስኬት ከመጠቀም አኳያ ብዙ የሚቀር ነገር እንዳለ መናገር ይቻላል፡፡ የኢፌዴሪ ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በ2002 ዓ.ም የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተቀናጀ አግባብ መምራት የጀመረ ሲሆን ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስታንዳርድን በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ወጣቶች በዕረፍት ጊዜያቸው ለማህበረሰባቸው የሚጠቅም አገልግሎት እንዲያበረክቱ ከወጣት አደረጃጀቶች ጋር በጋራ በመሆን ይሰራል፡፡ በተቋሙ አስተባባሪነት በወጣቶች እየተሰጠ የሚገኘው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የክረምትና የበጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች በሚሉ ሁለት ምዕራፎች በመክፈል በመሰጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን በተለይ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በስፋት የሚሰራበት ሆኖ ይገኛል፡፡ በዚህም የአገራችን ወጣቶች እውቀት፣ ጊዜና ጉልበታቸውን ለውጥ በሚያመጣና ጠቃሚ በሆኑ ተግባራት ላይ በማዋል በመንግስትና በህበረተሰቡ ያልተሸፈኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክፍተቶችን ለመሙላት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን መንግስትና ህብረተሰቡ ሊያወጧቸው የሚችሉትን በርካታ ሃብቶችን ለማዳን ዕድል መፍጠሩን ከሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል፡፡

አገራችን የወጣት አገር ናት፡፡ በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥም ከሀገሪቱ 105 ሚሊዮን ገደማ ከሚጠጋ አጠቃላይ ህዝብ ቁጥር ውስጥ 70 በመቶ ያህሉ ወጣት መሆኑ አገራችን ከሌላው አገር በተሻለ ወጣቶችን በዚህ መስክ በማሳተፍ እጅግ ዉጤታማ ማድረግ የሚቻልበት እድል ሰፊ መሆኑን ያመላክታል፡፡




*ከ117,000 በላይ የሰው ሃይል ወደ መስክ የሚያሰማራው የተመድ ሰላም አስከባሪ ተቋም የዓለም ሃገራት ከድምር ወታደራዊ ወጪያቸው አንፃር የተመድ ሲነፃፀር ከ0.5% የአነሰም ነው፡፡*

የአገሪቱን ወጣቶች ከግማሽ በመቶ በላይ እንኳን መጠቀም ቢቻል ምን ያህል ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል መገመት አያዳግትም፡፡ በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያለበት ሁኔታ በተለያየ ፈርጁ የሚጠቀስ ነው፡፡ በግልና በቡድን ሆነው አልያም የበጎ አድራጎት ተቋማት ጋር በመሆን በተለይ የሰዉ ድጋፍ የሚፈልጉና አቅመ ደካማ የሆኑ ሰዎችን በሆስፒታሎች የሚገኙ ህሙማን የሚንከባከቡ በቁጥር ይሄን ያህል ናቸዉ ብሎ ማስቀመጥ ባይቻልም  በራስ ተነሳሽነት ምግባሩን የሚፈጽሙ የበጎ ፈቃደኞች እንዳሉ መናገር ይቻላል፡፡ ከዚህ ባሻገር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ አንዳንድ ወጣቶችም እንዲህ በበጎ አድራጎት ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን በበጎ ፈቃደኝነት የእረፍት ጊዜያቸውን በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጡ እንዳሉም ይታመናል፡፡ ይህ በተናጥል የሚደረግ መልካም ጅምር ሲሆን በአጠቃላይ ከአገራት ተሞክሮና አገራዊ ፋይዳው በመነሳት በአገራችን የበጎ ፈቃድ አገልገሎት ገና ስር ያልሰደደና በቁንፅል ተግባራት ብቻ የታጠረ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የክረምት ወራትን ጠብቆ የሚፈፀም ተግባር አለመሆኑን በመስኩ የዳበረ ልምድ ያላቸው አገራት ተሞክሮ ያረጋግጣል፡፡ በአገራችን በመንግስት ደረጃ የበጎ ፈቃድ አገልገሎት ከወጣት አደረጃጀቶች ጋር በመቆራኘት በስፋት የሚፈፀመው ከወርሃ ሐምሌ ጀምሮ የሚደረግ የሁለት ወራት ተግባር ነው፡፡ በእነዚህ ወራት በርካታ ወጣቶች በችግኝ ተከላ፣ በክረምት ትምህርት መርሃ ግብር፣ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ የአረጋውያንና የአቅመ ደካሞችን መኖሪያ በመጠገን፤ በደም ልገሳ፤ በመንገድ ትራፊክ ማስተባበር፤ በሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ መገኖችን በመደገፍ፤ ወዘተ ላይ እንዲሳተፉ የማድረግ ተግባር ይፈፀማል፡፡ ይህ በራሱ የሚበረታታ ጅማሮ ቢሆንም ወቅትንና በተለይም ክረምትን ብቻ ጠብቆ የሚከወን በመሆኑ ህብረተሰባችን ከበጎ ፈቃደኞች ማግኘት ከሚገባው አገልግሎትና አገራችን ከምትገኝበት የእድገት ደረጃ፤ በርካታ ማህበራዊ ችግሮች ለዘመናት ተንከባልለው የሚገኙባት ከመሆኗ አንፃር በቂ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከክረምት መርሃ ግብር ወጥቶ ሰፋ ባለ ሁኔታ አመቱን ሙሉ በመተግበር ለአገር ገፅታና ለህብረሰተባዊ ለውጥ በዘላቂነት መጠቀም የሚገባ መሆኑን የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል፡፡ በተለያዩ የሙያ መስኮች ላይ እውቀትና ልምድ ያካበቱ ዜጎች ህበረተሰባቸውን ያለምንም የልፋት ዋጋ ማገልገል መቻል አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከፖሊሲ ጀምሮ መመሪያዎችን ጭምር ይህንን የሚተገብሩና አገራዊ ፋይዳውን በማጤን የሚከወኑ መሆን ይገባቸዋል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በየስራ መስኩ ቢሆን፤ የግብርና ተማሪውና ተመራቂው ግብርና ላይ ያለውን ማህበረሰብ በዛ ደረጃ መደገፍ ቢቻል፣ ህክምና ተማሪና ተመራቂውም እንደዛው ስለ ጤና አጠባበቅና ራስን እንዴት በመጀመሪያ እርዳታ ማከም እንደሚቻል ማስተማር ቢቻል፣ የህግ ተማሪውም ስለ ህግ የበላይነት፣ የሂሳብ ተማሪም አርሶ አደሩን ይሁን አርብቶ አደሩን እንዲሁም ነጋዴውን ስለሂሳብ አያያዝና መሰረታዊ የቁጠባ እውቀት ማስተማር ቢችል በተመሳሳይ የምህንድስና ሙያ ያለውም የገጠር መንገዶችን፣ ትምህርት ቤቶችን ጤና ኬላዎችን እና መሰል ግንባታዎችን መደገፍ ቢችሉ 50 ሎሚ ለ50 ሰው ጌጡ እንዲሉ እያንዳዱ የበጎ ፈቃድ ስራ ተደማምሮ የሚኖረው ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ በአጠቃላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ህብረተሰባዊ ለውጥ ለማምጣት መጠቀም የሚገባንና እጃችን ላይ ያለ ግዙፍ ሀብት መሆኑን መገንዘብ የሚገባ ይሆናል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአንድ ወቅት የለብ ለብ ስራ ብቻ ሳይሆን መሆን ያለበት ዓመቱን ሙሉ ወጣቱ እያሰበበት የሚቆይና የዜግነት ግዴታውና ማህበራዊ ሀላፊነቱ  አድርጎ የሚወስደው መሆን አለበት፡፡ ከክረምት ጊዜው ባለፈ በዓመቱ ያለውን የእረፍት ጊዜ ማህበረሰቡን ማገልገል ላይ ሊያውለው ይገባል፡፡ ይህ ጉዳይ አገራዊ በሆነ እቅድና መነቃቃት መመራት ጭምር ይገባዋል፡፡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አገር መገንባት



*የአሜሪካ ጠፈርተኞች የመምረጥ መብት በጠፈር ስምሪት ላይ እያሉ የሚካሄዱ ምርጫዎች እንዳያመልጣቸው ምርጫቸውን በዲጅታል መልዕክት ለጠፈር መቆጣጠሪያ ጣቢያ በመላክ ይሳተፋሉ፡፡*

ላይ ሊያተኩር ይገባል። ስለ ዴሞክራሲያዊ አንደነት ማስተማር፣ ኢትዮጵያዊነት መገንባት ላይ መስራት አለባቸው። ለዚህ ደግሞ የበጎ ፈቃደኝነት ስራ ትልቅ መድረክ ነው። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መዳረሻውን ከችግኝ ተከላ እና ከክረምት ትምህርት ማስተማር መሻገር መቻል አለበት። ወጣቱን ስለአንድነት ማስተማር አለበት። የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲታሰብ ችግኝ መትከል ብቻ አይደለም፤ ወደ ሰው አዕምሮ ግንባታ ጭምር መምጣት አለበት። የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰፋ ብሎ መታሰብ አለበት።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ለህዳሴ ጉዞአችን መሳካትና ለህብረተሰባዊ ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ ለዛ መጠቀም ይገባል። የተቀናጀ አሰራር መመሪያና ፖሊሲ ጭምር ሊኖረው ይገባል። ይህ አገልግሎት አገር የመለወጥ ሃይል ጭምር እንዳለው መዘንጋት የለበትም። ለአገራዊ ለውጥ መሰረቱና ቀጣይ የሀገሪቱ እጣፈንታ ያለው በወጣቱ እጅ በመሆኑ ይህን ወጣት መጠቀም የሚገባና የህልውና ጉዳይ ይሆናል። በዓመቱ ጊዜያቸውን ለዚህ በጎ ምግባር አገልግሎት የሰጡ ወጣቶች እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ሆነ ሌሎች ተቋማት እንደ ሚያደርጉት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችም በአገራችን ባሉ ተቋማት ቅድሚያ የስራ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

## *5. ማጠቃለያ*

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለበጎ ፈቃደኛውም ሆነ አገልግሎቱን ለሚጠቀመው አካል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው በሰፊው ተብራርቷል። መንግስት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የሚያበረታቱ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር አሰራሮችን በመዘርጋትና ተሳታፊዎች በማበረታታት የአገልገሎቱን ፋይዳ በማብራራት ለህበረተሰባዊ ለውጥ ለመጠቀም መትጋት ይገባዋል። በአገራችን የሚገኙ የወጣት አደረጃጀቶችም ክረምት በገባ ቁጥር የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ሃሳብ እንደ ወረት ከማቀንቀንና ከመሯሯጥ ይልቅ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ፋይዳ በማስረፅና ይህን መስክ የወጣቱን ስብዕና ለመገንባት ጭምር በመጠቀም በአጭር ጊዜ ሳይሆን የረጅም ጊዜ እቅድ አውጥተው ወጣቶችን የማብቃትና የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የህይወት ዘመን ባህላቸው እንዲያደርጉት መስራት የሚጠበቅ ይሆናል።

የአገራችን ወጣቶች ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በማንኛውም የስራ መስክ ላይ የተሰማሩ ወጣት ባለሙያዎች ሳይማር ያስተማራቸውን ለእነሱ የዛሬ ማንነትና ስኬት ከባድ ዋጋ ከፍሎ ለዚህ ያበቃቸውን ህብረተሰብ ጊዜ ሊመድቡለትና ሊያገለግሉት፤ በተቻለ አቅም ውለታውን ሊመልሱና ደረስኩልህ ሊሉት ይገባል። አገራችን እንደሌ አገራት ዜጎች በበጎ ፈቃድ አገልገሎት መስክ የሚሰማሩ ወጣቶችን በማስፋትና ከአገር አቀፍ ወደ አህጉር አቀፍ ብሎም ዓለም አቀፍ ደረጃ በማሳደግ ሌሎች አገሮችን ጭምር ሄዶ ማገልገል የሚችል ሰብዓዊነትን የተላበሰና የፓን አፍሪካኒዝም ጽንሰ ሀሳብን የሚያቀነቅን ሉዓላዊ ዜጋ ባለቤት መሆኗን ጭምር ለመፍጠር መስራት የሚገባ ይሆናል። የቀደምት አባቶቻችን ታሪክ ከኮሪያ አስከ ኮንጎ፤ ዛሬም ላይ ከላይቤሪያ እስከ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲና ደቡብ ሱዳን በሰላም አስከባሪነት የተሰሩ ደማቅ ስራዎች ወጣቱ ሊማርባቸዉ የታላላቆቹ ስብእና እንዲጋባበት ማድረግ ያስፈልጋል።

የግልና የመንግስት ተቋማት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው ህብረተሰባቸውን ሲያገለግሉ ለነበሩ ወጣቶች በስራ ገበታም ሆነ ተያያዥ ገዳዮች ቅድሚያ በመስጠትና ከሁሉ በላይ ተግባራቸውን በማበረታታት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እያለሙ የሚለሙበት ዋጋ ያለው የህይወት ዘመን ሰናይ መስክ መሆኑን በተጨባጭ በመደገፍ ማሳየት መቻል የሚገባው ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ እንደሚሉት ኢትዮጲያ የወጣቱ ናት፤ መጪዉ ዘመንም ከሁሉ በላይ የወጣቱ ነው። ዛሬም አገር በመገንባት ግምባር ቀደም ሚናውን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ከ30 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች በዓመት ሁለት ጊዜ የአንድ ሰዓት የበጎ ፈቃድ ተግባር




**በትዊተር 7ፅ አሜሪካዊያን ትዊት የሚደርጉት እያንዳንዷ መረጃ በኮንግረስ ላይብረሪ አርካይቭ ውስጥ ይከዘናል።**

ውስጥ ቢሳተፉ በቀላሉ የ60 ሚሊዮን ሰዓት ትርፍ እናገኛለን፤ በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደው ለሀገሬ እሰጣለው የተሰኘው የበጎ ፈቃድ ተግባር ያመላከተን ሀቅ ተግባሩን ተቋማዊ ካደረግነው ግዙፍ የችግር ተራሮችን መናድ እንደምንችል ያመላከተ ሆኖ አልፏል፤ በተጨማሪም ባሳለፍነው የክረምት ወቅት የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ወጣቶች በጣናን ኬኛ የጸረ-እምቦጭ መከላከል ተግባር ምን ያህል የወጣት አቅም እንዳለንና እስካሁንም በአግባቡ ባለመጠቀማችን የቁጭት ስሜት ፈጥሮብናል፡፡


እንዴት ተቋማዊ እናድርገው ለሚለው በቅርቡ የተቋቋመው የሰላም ሚኒስተር ይህንን ተግባር ተቋማዊ አሰራር ዘርግቶ በስሩ ቢያቅፈው፤ እ.ኤ.አ በ1994 አንድ ሰው ለአንድ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በአካል ጉዳተኞች፤ በአቅመ ደካሞች፤ በአረጋውያን፤ ወዘተ ላይ የተለየ ድጋፍ በመስጠት ደማቅ ታሪክ መጻፍ የቻሉበትን ተግባር፤ እኛም ከከተማችን ብሎም ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በመነሳት፤ ባለ ሀብቱ፤ የመንግስት ተቋማት፤ የመንግስትና የግል ባንክና ኢንሹራንስ ተቋማትን በመጠቀምና በማሳተፍ የቻይናውን ተሞክሮ በዚህ መልክ ብናሰፋው፤

በከተማችን ከሚገኘው ከ 170 ሺህ በላይ  የመንግስት ሰራተኛ በሚሰራበት ተቋም በወር ለተጨማሪ አንድ ሰዓት ቢሰራ፤ ይህም በዓመት 2,040,000 ሰዓት ይሆናል፡፡ ይህ ተግባር በተለይም የመልካም አስተዳደር ማነቆ የሆኑ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ቢሰጥ አንድ እርምጃ ወደ ፊት መሻገር ያስችላል፡፡ ይህንንም አገልጋይነት በተግባር፤ የሀገር ፍቅር በተግባር፤ ወዘተ በሚሉ መልእክቶች በማጀብና የተሻለ የበጎ ፈቃድ ስራዎችን ለሰሩ ተቋማትና ግለሰቦች እውቅና በመስጠት ወደ ተቋም ደረጃ ማሸጋገር፤ ህብረተሰቡም የኑሮው አንዱ ዘይቤ እንዲያደርገው ማድረግ ይቻላል፡፡ መምህሩ ለአንድ በማስተማር፤ የጤና ባለሙያውም ህሙማንን በማከም፤ በመንከባከብ፤ ምክር በመስጠት፤ መሀንዲሱም የተበላሹ መንገዶችን፤ ድልድዮችን በመጠገን፤ ሙያዊ እገዛ በማድረግ የትምህርት ቤት፤ የጤና ተቋማት፤ ወዘተ ግንባታ ላይ ንድፈ ሀሳቦችን እንዲያቀርብ፤ ሙያዊ ክትትል በማድረግ ወዘተ መሳተፍ ይቻላል፤ ለዚህም የመምህራን ማህበርን፤ የጤና ባለሙያዎች ማህበርን፤ ወዘተ ካሉ የሙያ ማህበራት ጋር በመቀናጀት ጊዜና ከፍተኛ የመንግስት ካፒታል የሚጠይቁ ተግባራትን ተደራሽ ማድረግ ይቻላል፡፡




***በ1996 የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ የምርጫው አሸናፊ ከመታወቁ አስቀድሞ በሰንጠዥ የቃላት ጨዋታ ዝግጅቱ ላይ የአሸናፊውን ስም በፍንጭነት ተጠቅሞ ነበር-ሲገጣጠም፡፡***

# የማስላት ጥበብ




አራት አይነት ዕቃዎች በአራት መደብ ጥቅል ዋጋቸው ተቀምጧል። የእርስዎ ችሎታ መሆኑን የሚያፈጋግጡልን ነገር የየመደቡን ጥቅል ዋጋ አጢነው የአራቱንም አይነት ዕቃዎች ነጠላ ዋጋ ማስቀመጥ ነው። በየመደቡ የተቀመጠው ዋጋና የዕቃ ዓይነት ብዛት ስስሌትዎ ፋይዳ እንዳለው ከአሰቡ ልክ አለበዋል። መልስዎን በኢሜል አድራሻችን መላክዎን አይዘንጉ።

awdelewt@gmail.com



በአለፉት 50 ዓመታት ውስጥ በ52 አገራት ሴቶች የርዕሰ ብሄርነትን በትረ ስልጣን ጨብጠዋል።

አስገራሚና አስደናቂው ነገር የዴሞክራሲ ዓርማ ነኝ የምትለዋ አሜሪካ ከእነዚህ 52 አገራት ተርታ መሰለፍ የተሳናት መሆኗ ነው።

# "ሥርዓት ሲበጅለት የሚገባው"



# ህግ አልባው የጦር መሳሪያ ዝውውር

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የጦር መሳሪያ ዝውውር መረጃ እንደሚያመለክተው በነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ ከሕዝብ ብዛት አንፃር ሲሰላ ከአሜሪካ ሕዝብ 89 በመቶው በመታጠቅ ቅድሚያውን ይወስዳሉ፡፡ ከመቶ ሰው መካከል ሰማንያ ዘጠኙ የጦር መሣሪያ አላቸው፡፡ ከአሜሪካ በመቀጠል እስከ አስረኛ ደረጃ የሚገኙት ደግሞ የመን 61 በመቶ፣ ስዊዘርላንድ 46 በመቶ፣ ፊንላንድ 45 በመቶ፣ ሰርቢያ 38 በመቶ፣ ቆጵሮስ 36 በመቶ፣ ሳዑዲ ዓረቢያ 35 በመቶ፣ ኢራቅ 34በመቶ፣ ኡራጓይ 32 በመቶ፣ ስዊዲን 32 በመቶ ናቸው፡፡

ይህ በአደጉት አገራት የሚታየው የእኔ እበልጥ እኔ የጦር መሳሪያ የደረጃ ሰንጠረዥ በአህጉራችን አፍሪካ የአለውን ስንቃኝ በጎረቤታችን ሱዳን የሚኖሩ ሁለት ሚሊዮን ገደማ ሱዳናውያን በእራሳቸው የታጠቁ ሲሆን፣ ግብፅ በበኩሏ ሁለት ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝቧ እንደታጠቀ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከህዝብ ብዛቷ አንጻር ከመቶ ሲሰላ ደግሞ 3 ነጥብ 5 በመቶ ገደማ ይሆናል፡፡ ዜጎቻቸው መሳሪያ ከታጠቁ 178 አገሮች 37ኛ ከሰው ብዛት ደግሞ 115ኛ ናት፡፡

በኤርትራም ቢሆን ወደ 20 ሺህ የሚጠጋ መሳሪያ በዜጎች እጅ የሚገኝ ሲሆን በህዝበ ውሳኔ እራስ አገዛዟን ካረጋገጠች ቅርብ ጊዜ የሆናት ደቡብ ሱዳን ከአንድ እስከ ሦስት ሚሊዮን ዜጎቿ እንደታጠቁ ይታመናል፡፡ ይህም በከፍተኛው ግምት ሲሰላ ከህዝብ ብዛቷ 28 ነጥብ 2 በመቶ ነው፡፡ በርካታ የኬንያ ዜጎችም ባለመሳሪያ ናቸው፡፡ ከአጠቃላይ አገሪቱ ዜጎች 650 ሺህ የሚሆኑት የታጠቁ ናቸው፡፡ ከመቶው ሲሰላ 1 ነጥብ 4 ነው፡፡ ሶማሊያ 9 ነጥብ 1በመቶ የሚሆኑት ዜጎቿ ባለመሣሪያ ሲሆኑ፣ በአሃዝ ሲገለጽም 650 ሺህ ይገመታል፡፡ ጂቡቲ በበኩሏ 2ነጥብ8 ከመቶው ዜጎቿ የታጠቁ ናቸው፡፡

በአጎራባቾቻችን ሀገራት በስፋት የሚታየው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር የአገራችን ኢትዮጵያም ፈተና ሆኗል፡፡ በተለይ ደግሞ ባለፉት ሶስት አመታት ስፋት እና መጠኑ እየጨመረ መጣ እንጂ አልተገታም፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በመጋቢት ወር የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ የህዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ጠቅሶ እንደዘገበው ባለፉት አራትና አምስት ወራት ውስጥ ብቻ ወደ 60 ሺህ 94 የተለያዩ ሹጉጦች፣ ወደ 136 ሺህ 95 የተለያዩ የሽጉጥ ጥይቶች፣ እንዲሁም ወደ 9 ከባድ መትረየስ፣ 5 ክላሾች፣ 2 ዝናር የጦር መሳሪያ እንዲሁም የተለያዩ የጦር መሳያዎች በዓቃቤ ህግ መዝገብ ክስ የተከፈተባቸው ናቸው፡፡ በምርመራ ላይ ያሉ እንዲሁም በቅርቡም የተያዙ አሉ፡፡ የክስ መዝገብ ከመክፈት ባሻገር የጦር



*የእግር ኳስ ጦርነት በ1970 የፈፋ የዓለም ዋንጫ ኤልሳልቫዶር ሆንዱራንስን በማሸነፏ ምክንያት የተቀሰቀሰ ጦርነት ነው። ለ100 ሰዓታት ወይም ለአራት ቀናት ብቻ ነው ጦርነቱ የቆየው።*

መሳያዎችን ሲያዘዋውሩ የነበሩት ተሽከርካሪዎች ጭምር ውሳኔ አግኝተው ውርስ እንዲሆኑም ተደርጓል።

በዓለም ላይ በየዓመቱ 12 ቢሊዮን ጥይቶችና ስምንት ሚሊዮን የጦር መሣሪያ ተመርቶ ወደ ገበያ ይቀላቀላል፡፡ ከዓለም ሕዝብ ደግሞ 10 ከመቶው ታጥቋል። የጦር መሣሪያ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገም ነው፡፡ መቀመጫውን ስቶክሆልም ስዊድን ያደረገው ዓለም አቀፍ የሰላም ምርምር ተቋም በምህፃሩ SIPRI/ሲፕሪ/ ያወጣው ዘገባ እንደሚያሳየው የንግዱ ዋነኛ ተጠቃሚዎች በዩናይትድ ስቴትስ እና በምዕራብ አውሮፓ የሚገኙ የጦር መሣሪያ አምራች ኩባንያዎች ናቸው። የጥይቶች፣ ታንኮች እና ሰው አልባ የጦር አውሮፕላኖች (ድሮኖች) ንግድ ከአምስት ዓመታት በተለይም እ.ኤ.አ ከ2016 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገና አድጓል።

ንግዱ በቀደሙት ዓመታት ከነበረው የ1 ነጥብ 9 በመቶ እድገት ወደ 38 በመቶ አሻቅቧል። አዲሱ የዓለም የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ ዘገባ እንደሚያትተው በ2016፣ የዓለማችን 100 ትላልቅ የጦር መሣሪያ አምራች ኩባንያዎች ከጦር መሣሪያ፣ ከመለዋወጫዎቻቸው እና ከወታደራዊ አገልግሎት ቁሳቁስ ሽያጭ 375 ቢሊዮን ዶላር ማፈስ ችለዋል። በተለይ የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች የጦር መሣሪያ ምርት ሽያጭም ጨምሯል። እንደ ሲፕሪ ዘገባ በዓመቱ የአሜሪካን ኩባንያዎች ሽያጭ በአራት ከመቶ ጨምሮ በአጠቃላይ ወደ 217 ቢሊዮን ዶላር አድጓል። ይህ የሆነው ግን በአሜሪካን ወታደሮች የውጭ ስምሪት ምክንያት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሀገራትም በተለያየ መንገድ ለሚገለጸው ጥቅም ሲሉ ብዙ የጦር መሣሪያ በመሸመታቸው ነው እንደ ጥናቱ።

የዓለማችን ትልቁ የጦር መሣሪያ አምራች የዩናይትድ ስቴትሱ ኩባንያ “ሎክሂድ ማርቲን” ኤፍ ሰላሳ አምስት የተባሉትን የጦር አውሮፕላኖቹን እንደ ብሪታንያ፣ ጣልያን ወይም ኖርዌይ ለመሳሰሉ ሀገራት በመሸጥ ትርፍ ዝቆበታል። ዋነኛ ደምበኛው ግን የዩናይትድ ስቴትስ አየር ኃይል ነው። የሲፕሪ ጥናት በግልጽ እንደሚያሳየው ከአጠቃላዩ የዓለም የጦር መሣሪያ ንግድ 58 በመቶው በአሜሪካን ኩባንያዎች የተካሄደ ነው። በዚህ ንግድ የምዕራብ አውሮፓ ሀገራት ሁለተኛውን ቦታ ሲይዙ ሩስያ ደግሞ በሰባት በመቶ ሦስተኛው ደረጃ ላይ ትገኛለች።

***“በአራቱም አቅጣጫዎች ማለትም በደቡብ ሞያሌ፣ በምስራቅ ቶጎ ውጫሌ፣ በምዕራብ ጋምቤላ ሱዳን አዋሳኝ፣ በሰሜን ከሱዳን መተማ፣ እና በቤንሻጉል ጉምዝ አካባቢ ወደ ሃገር ውስጥ እንደሚገቡ አብዛኞቹም ቱርክ ሰራሽ እንደሆኑ ያረጋግጣል፡፡”***



*የአሜሪካ ደህንነት ተቋም (secret Service) ባራክ ኦባማን መጠበቅ የጀመረው ከምርጫው ቀን 18 ወራት ቀደም ብሎ ነው። በአሜሪካ ታሪክ እንደ ኦባማ ከመመረጣቸው ቀደም ብሎ የደህንነት ተቋሙን የረጅም ጊዜ ጥበቃ አገልግሎት የአገኘ ፕሬዚዳንት የለም።*

ከአውሮፓ የጣልያን እና የፈረንሳይ ኩባንያዎች የጦር መሣሪያ ንግድ ዝቅተኛ ሲሆን ትልቁን ድርሻ የሚይዙት ብሪታንያ እና ጀርመን ናቸው። ለምሳሌ የጀርመኖቹ ታንክ አምራች ኩባንያዎች (crows mafia and Rinmental) ክራውስ ማፌይ እና ራይንሜታል በ2016 ንግዳቸው ከፍ ካሉ ኩባንያዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው።

በሲፕሪ የጦር መሣሪያዎች እና የወታደራዊ ወጭዎች መርሃ ግብር ሃላፊ ኦድ ፍለሮን የጦር መሣሪያዎች በብዛት መሸጣቸውን ከሚካሄዱ ጦርነቶች ጋር በቀጥታ ማገናኘቱ አስቸጋሪ መሆኑን አልፎ አልፎ በሁለቱ መካከል ትስስር መኖሩን ደቡብ ኮሪያን ምሳሌ በማድረግ ይገልጻሉ። በ2016 የደቡብ ኮሪያ ኩባንያዎች የጦር መሣሪያ ንግድ በ20 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ ማለቱን የተለያዩ አለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ዘግበው ነበር። ፍለሮን ደቡብ ኮሪያ በጎረቤትዋ በሰሜን ኮሪያ የኒዩክልየር ትንኮሳ ምንክያት ከፍተኛ ስጋት እንዳደረባት፤ ይህም ወታደራዊ ወጪዋ እንዲጨምር ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህ ንግድም የሀገሪቱ የጦር መሣሪያ አምራች ኩባንያዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ንግዳቸውም በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። ይህ የሆነው ሀገሪቱ በምትገኝበት የፀጥታ ሁኔታ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ ተቋማት ከአገራቸው ገበያ ተሻግረው በዓለም አቀፉ ገበያም በንቃት እየተሳተፉ ነው።


የዘርፉ ተንታኞች ቻይናም ከዓለም ዋነኛ የጦር መሣሪያ አምራቾች አንድዋ ልትሆን ትችላለች የሚል እምነት አላቸው። ሆኖም ስለቻይና አስተማማኝ መረጃ ስላላገኙ አሃዛዊ መዘርዝሩ ውስጥ አላካተቱዋትም። በሌላ በኩል የሲፕሪ ዘገባ እንዳሳየው፣ የጦር መሣሪያ በመሸመት የሚታወቁት በርካታ የአፍሪቃ እና የደቡብ አሜሪካ ሀገራት በየጊዜው በሚዋዥቀው የነዳጅ ዘይት ዋጋ ሰበብ ገንዘብ ስላነሳቸው ብዙ መሣሪያ መግዛት አልቻሉም።

በሕገ ወጥ መንገድ እየተካሄደ ያለው የጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር ለአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሰላም እና ምጣኔ ሀብት እድገትም መሰናክል ነው። ከአፍሪካ ጋር የንግድ ልውውጥ ለማድረግ ለሚፈልጉ ምዕራባውያን መንግሥታት እና ተቋማት በአህጉሩ ስላለው የደህንነት እና የንግድ ስራ ሁኔታ ምክር የሚሰጠው ኤክስ ኤክስ አፍሪካ የተባለው ድርጅት  ሕገ ወጡ የጦር መሳሪያ ንግድ በተለይ በጅቡቲ መስፋፋቱን ይገልጻል። ይህን በተመለከተ ድርጅቱ ባወጣው ልዩ ዘገባ መሰረት፣ አብላጫው የጦር መሳሪያ ወደ ጅቡቲ የሚገባው የሰው ልጅ ክቡር ህይወት እንደቀልድ ከሚቀጠፍባትና ማባሪያ የለሽ የእርስ በእርስ ጦርነት ከሚካሄድባት የመን ነው። ይህ ከሀገሪቷም አልፎ እኛን ለመሰሉ የቅርብ ጎረቤት አገራት ከፍተኛ የእራስ ምታት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

አገራችን አነስተኛ የጦር መሣሪያ መሥራትን ወደ ውጭ መላክንም ሆነ ማስገባትን እንዲሁም ወደ ሌላ አገርም ሆነ ሰው ማስተላለፍን የሚመለከት የሕግነት ቅርፅ ይዞ የወጣ አዋጅ ደንብ ወይንም መመርያ አሊያም የማስተዳደርያ ሥርዓት የሌላት መሆኑ ደግሞ ሌላኛው የእራስ ምታታችን ነው። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55(1)(ሸ) ላይ እንደተገለጸው የጦር መሣሪያ አያያዝን በተመለከተ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ መንግሥት ነው። በህጋዊ መንገድ በብቸኝነት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለውም ይኸው አካል ብቻ ነው። በመሆኑም አገሪቱ ካላት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና በቀጠናው ካለው ጂኦ ፖለቲክስ አኳያ ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማራገፊያም መተላለፊያም መሆኗ አይቀሬ ነው።

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽንን የቅርብ ጊዜ መረጃዎች መነሻ አድርገን የህገ ወጥ መሳሪያ  ዝውውሩን ብንመለከት በርካታ ሽጉጦች፣ ክላሽ፣ ጥይቶች፣ ቦንቦች እና የቡድን መሳሪያ እንዲሁም መትረየስ በአራቱም አቅጣጫዎች ማለትም በደቡብ ሞያሌ፣ በምስራቅ ቶጎ ውጫሌ፣ በምዕራብ ጋምቤላ ሱዳን አዋሳኝ፣ በሰሜን ከሱዳን መተማ፣ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ አካባቢ ወደ ሃገር ውስጥ እንደሚገቡ አብዛኞቹም ቱርክ ሰራሽ እንደሆኑ ያረጋግጣል።

የተቋሙ ድረ ገጽ ባለፉት ጥቂት ወራት ባልተለመደ መልኩ መዲናችን አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ



*ከመጀመሪያዎቹ አምስት የአሜሪካን ፕሬዚዳንቶች ውስጥ ሁለተኛው ፕሬዚዳንት ጆን አዳምስ ብቻ ነው ባሪያ አሳዳሪ ያልነበረው። ቀዳሚው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን እስከ ዕለተ ሞቱ ከ300 በላይ ባሮች ነበሩት። ጆን አዳምስ ሁለተኛው ፕሬዚዳንት ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያው ምክትል ፕሬዚዳንትም ነበር።*

ክልሎች ህገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር በስፋት መስተዋሉን ይገልጻል፡፡ ዝውውሩ በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የተከሰተ ቢሆንም የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላና የአማራ ክልሎች የቀዳሚነቱን ስፍራ ይይዛሉ፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከደቡብ ሱዳን ጋር እንደመዋሰኑ ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ሁነኛ በር ሆኖ እያገለገለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ናኮሞ በመባል የሚጠራው ልዩ ወረዳ ዋነኛው ሲሆን ቡዋ አልመሀል በተባለ ኬላና አልፎ አልፎም ከመሀል ሀገር መሳሪያ እንደሚገባም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የጋምቤላ ክልልም ከደቡብ ሱዳን ጋር በሚዋሰንባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር አለ፡፡ በክልሉ በሚገኙ 13 ወረዳዎች ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውሩ ከፍተኛ መሆኑም ይነገራል፡፡ የጦር መሳሪያዎቹ መነሻቸው ከደቡብ ሱዳን ሲሆን መድረሻቸው ደግሞ በጋምቤላ በኩል አድርገው ወደ መሀል አገር በተለይም በርካታ ታጣቂዎች ወደሚንቀሳቀሱባቸው የአገራችን ክፍሎች ነው፡፡

“በዓለም ላይ በየዓመቱ 12 ቢሊዮን ጥይቶችና ስምንት ሚሊዮን የጦር መሣሪያ ተመርቶ ወደ ገበያ ይቀላቀላል፡፡ ከዓለም ሕዝብ ደግሞ 10 ከመቶው ታጥቋል፡፡ የጦር መሣሪያ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገም ነው፡፡”

የአማራ ክልል ከሱዳን ጋር በሚዋሰንበት አካባቢም ከፍተኛ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር መኖሩን የክልሉ የጸጥታ ቢሮ መረጃ ያመላክታል፡፡ በተለይ ደግሞ በመተማ በኩል ቱርክ ሰራሽ ሽጉጦች፣ የእጅ ቦንቦች፣ ክላሾችና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥይቶች በቦቴ መኪናዎችና በተለያዩ ዘዴዎች ወደ መሃል አገር ለመግባት ሲሉ በተደጋጋሚ ጊዜ በቁጥጥር ስር እየዋሉ ነው፡፡ እነዚህ የጦር መሳሪያዎች አሁን አሁን ለህገ ወጥ ተግባራት ማስፈጸሚያ ከመዋላቸው ባሻገር እንደ አንድ የንግድ ዘርፍ የሚታዩበት ሁኔታም እየተፈጠረ ነው፡፡ በሰሜኑም ሆነ በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች የጦር መሳሪያ ግብይቱ ከወትሮው በተለየ መልኩ ፍጥነቱን ጨምሯል፡፡ በቀደሙት ጊዜያት በገጠር ቀበሌዎች እልፍ ሲል ደግሞ በወረዳ ከተሞች ይደረግ የነበረው የጦር መሳሪያ ግብይት በተለይ ከቅርብ ጊዜያ ወዲህ የአገሪቱን የተለያዩ ክፍሎች እያዳረሰ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ አንዳንዶች እንደሚሉት ከሆነ የጦር መሳሪያ ባለቤት መሆን አሁን አሁን የአየር ያህል ቁልፍ ጉዳይ ሆኗል፡፡

አሁን ባለው የጦር መሳሪያ ግብይት ዋጋ



በአንድ ወቅት የአሜሪካ ጦር ሃይልና አየር ሃይል በ1968 ጨረቃ ላይ ወታደራዊ የአየር ሃይል ቤዝ የማቋቋም የጋራ ዕቅድ ነበራቸው፡፡ ወታደራዊ ቤዙ የጨረቃ መሬት ውስጥ ለውስጥ ለመገንባት የታሰበ ነበር፡፡




***"በቀደሙት ጊዜያት በገጠር ቀበሌዎች እልፍ ሲል ደግሞ በወረዳ ከተሞች ይደረግ የነበረው የጦር መሳሪያ ግብይት በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የአገሪቱን የተለያዩ ክፍሎች እያዳረሰ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።"***

መሰረት ኤኬ አርባ ሰባት ታጣፊ ክላሽ ከአርባ እስከ ሃምሳ አምስት ሺህ ብር፤ ስታር ሽጉጥ ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ አምስት ሺህ ብር፤ ማካሮቭ ከሃያ እስከ ሰላሳ ሺህ ብር፤ ኤፍ ዋን ቦምብ ከአንድ ሺህ እስከ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር እንዲሁም የጥቃት ርቀታቸው አጭር የሆኑ ሌሎች የእጅ ቦምቦች ደግሞ ከሶስት እስከ ስድስት መቶ ብር በመሸጥ ላይ ይገኛሉ እንደ የሁኔታው አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ ማንኛውም ዓይነት የከባድ መሳሪያ ማቅረብ የሚችሉ ኃይሎች እንዳሉም ይነገራል።

ህገ ወጥ መሳሪያ ዝውውር የክልሎች ብቻ ሳይሆን የመዲናዋን አዲስ አበባ ራስ ምታትም ከሆነ ሰነባብቷል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ የመግባታቸው ዜና በተደጋጋሚ እየተሰማ ነው። በተለያዩ መንገዶች ወደ ከተማዋ ሊገቡ የነበሩ ከ10 ሺህ በላይ ሽጉጦች፣ 30 ክላሽንኮቭ ጠብመንጃዎች፣ 4 መትረየስ እና ከ19 ሺህ በላይ ጥይቶችም ከህገ ወጦች ላይ በቁጥጥር ስር እንደዋለ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው ግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ.ም በፅህፈት ቤታቸው ለጋዜጠኞች መግለጫ በሰጡበት ወቅት ተናግረዋል። በህገ ወጥ መንገድ ሲያዘዋውሩ የተገኙ አካላትን ለፍርድ የማቅረቡ ስራም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ዝውውሩን ማስቆም አልተቻለም። ስለሆነም ከተለያዩ አገራት በድንበር በኩል የሚገባውን ሕገ-ወጥ የጦር መሳሪያ አስመልክቶ ጠንከር ያለ ሕጋዊ አሰራር ሊኖር እና ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውሩን ለመግታት የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር ህግ ያስፈልጋል።

በግለሰቦች ወይም በአነስተኛ ቡድኖች ሊያዙ የሚችሉ ሕገ ወጥ መሳሪያዎች መሰራጨታቸው ኃይል መጠቀም ለእዚያውም በተመጠነና ህጉ በሚፈቅደው አይነትና መጠን መጠቀም የመንግሥት ብቻ የሆነ ስልጣን ሆኖ ሳለ በሌሎች ሰዎች፣ ቡድኖችና ድርጅቶች እጅም እየገባ መሆኑ አደገኛ እንደሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይገልጻሉ። የሕገ ወጥ መሳሪያ ዝውውር፤ በክልሎች ከሚነሱ ግጭቶች፣ ከፕሮፓጋንዳ መሳሪያነቱ



*እንኳንስ ምድራችን ላይ ጨረቃም ላይ እንደተውለበለበ የሚነገርለት የአሜሪካን ባንዲራ ንድፍ የወጣው በአንድ የ17 ዓመት አሜሪካዊ ተማሪ ነው። ለባንዲራው ንድፍ በትምህርት ቤቱ የተሰጠው ውጤት (B) ቢሆንም ሃገሩ አሜሪካ ግን የእድሜ ልክ ምልክት አድርጋ ተቀብላዋለች።*

*እንዲሁም በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ ድርጅቶች ጋርም ያያይዙታል። እነዚህ መሳሪያዎች በዘራፊዎች ወይም ህገ ወጥ የፖለቲካ አላማ ባላቸው ሰዎች እጅ ሊገቡ የሚችሉበት እድል መኖሩ፤ መንግሥትን ሀይል ከማሳጣቱ ባሻገር ህብረተሰቡን አደጋ ላይ የሚጥልም እንደሆነም ተንታኞቹ ያስረዳሉ።*

*ዝውውሩ የህዝቡን ወጥቶ መግባትንም አስጊ እንደሚያደርገው፤ ኅብረተሰቡ መንግሥት ላይ አመኔታ ሲያጣ ቤተሰቡን ለመጠበቅ ወደ ጦር መሳሪያ ሽመታ ሊያመራ የሚችልበት አግባብ መኖሩ ስጋትን የሚፈጥር መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ህግና ስርአትን የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መንግሥት ሳይዘገይ አስፈላጊ የሆነ ቁጥጥር ማድረግ እንደአለበትም የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያመላክታሉ።*

*ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመቆጣጠር፤ መሳሪያ ማን እንደሚይዝና እንደሚያዘዋውር የሚወስን ሕግ መውጣት አለበት። በእርግጥ ከዚህ ቀደም ግለሰቦች በቂ ምክንያት እስካላቸው ድረስ ለመንግሥት አሳውቀው የመሳሪያ ባለቤት መሆን ይችላሉ። ሆኖም ዜጎች ያለ መንግሥት እውቅና መሳሪያ መታጠቅ ከጀመሩ፤ ስርዓት አልበኝነት እየሰፈነ በሂደትም ቡድኖች መደራጀታቸው የማይቀር በመሆኑ የመንግሥትን ኃይል መገዳደራቸው አይቀሬና ህዝብንም አደጋ ውስጥ እንደሚከት ግልጽ ነው። ተራው ዜጋ በድብቅ መሳሪያ ከታጠቀ ብቸኛ ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው ፖለቲካዊ ነው። በተለይም የጦር መሳሪያ ስርጭቱ በተደራጀ ኃይል ቁጥጥር ስር የሚውል ከሆነ ወደ እልቂት ማምራቱ አይቀርም። ከዚህ በፊት ያለው ሕግ እንዳለ ሆኖ፤ ሕጉን ማጥበቅ ካስፈለገ አንድ ሰው መሳሪያ መያዝ እንዲፈቀድለት የሚጠየቁ መስፈርቶች ጠንካራ መሆን አለባቸው።*

*በኢትዮጵያ እየተስፋፋ የመጣውን ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ለመቆጣጠር "የጦር መሳሪያ አያያዝ፣ ዝውውርና አጠቃቀም" አዋጅ እየተዘጋጀ መሆኑን ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ድረ ገጽ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ግልጽ የሆነ የጦር መሳሪያ አያያዝ፣ ዝውውርና አጠቃቀም መመሪያም ሆነ አሰራር የለም። በዚህም ምክንያት በፀጥታ አካላትም ሆነ ግለሰቦች የጦር መሳሪያ አያያዝና አጠቃቀም የሚመራው በዘፈቀደ ነው። ስለሆነም በአገሪቱ የፌደራል ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስና ልዩ ሃይል፣ ሚሊሻ እና ሌሎች የጸጥታ አካላት መያዝ የሚፈቀድ እና የማይፈቀድ መሳሪያ ዓይነቶችም ሆነ አጠቃቀም በግልጽ አይታወቅም።*

*ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀውም ይህንን በዘፈቀደ የሚከናወን አሰራር ስርዓት በማስያዝ በአገሪቱ በስፋት የሚስተዋለውን ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር መግታት የሚቻልበትን መንገድ ለመፍጠር መሆኑን መረጃው ኮሚሽነሩን ዋቢ በማድረግ ያትታል። በመሆኑም ግለሰቦችም ሆኑ የፀጥታ አካላት መያዝ የሚችሉት የመሳሪያ ደረጃ ምን አይነት መሆን እንዳለበት በሚቀመጠው መስፈርት ተለይቶ ተግባራዊ እንደሚደረግም መረጃው ያመለክታል። የአዋጁ መውጣት ማንም እንደፈለገ የተከለከለ የጦር መሳሪያ እያነሳ ህብረተሰቡን ለስጋት የሚያጋልጥበት ሁኔታን የሚያስቀር በመሆኑ በቅርቡም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይፀድቃል የሚል እምነት አለን።*

*በአጠቃላይ ሕግና ስርአት ማስጠበቅ የመንግሥት ኃላፊነት ነው። ከሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ጋር ተያይዞ በአገራችን እየተስተዋለ ባለው ሁኔታ ላይ መንግሥት ሳይዘገይ አስፈላጊ የሆነ ቁጥጥር ማድረግ አለበት። አስፈላጊውን ንቅናቄ ማድረግም አለበት። ከዚህ በፊት ያለው ሕግ እንዳለ ሆኖ፤ ሕጉን ማጥበቅ ካስፈለገ አንድ ሰው መሳሪያ መያዝ እንዲፈቀድለት የሚጠየቁ መስፈርቶች ጠንካራ መሆን አለባቸው። የተለያዩ አገራት ልምድ በሚታይበት ጊዜ የጦር መሳሪያን አያያዝና አጠቃቀም የሚቆጣጠር አንድ መንግስታዊ ተቋም ያለ በመሆኑ ይህንም ተሞክሮ በቀጣይነት በአገር ውስጥ ለመተግበር ጠንክሮ መስራት አስፈላጊ ነው እንላለን።*



***የፌብሩዋሪ 19 ቀን 1913ቱ  የሜክሲኮው 34ኛ ፕሬዚዳንት ፔድሮ ላስኩሬን የምድራችን አጭሩ የመሪነት ዘመንን ክብረ ወሰን ጨብጧል። ፕሬዚዳንት ከሆነ አንድ ሰዓት እንኳ ሳይሞላው አያሻንም ብሎ ወርዷል። 45 ደቂቃ ብቻ የመምራት ክብረ ወሰኑ ግን እነሆ 106 ዓመታት ዘልቋል።***



ለንቺ ወዲህ
እኔ ወዲያ
ለንተ እንዲህ
ለንቺ እንዲያ
ጠባባሉን ትተን
ልዩነት ፀጋነት እንዲሆን
ጠባሳታችንን ለቁጠን
ተብሳልተን ተዋህደን
ውዴ ዘጠዴ ፓንዳ እንሁን!

## ቁጥሮች

*10 ቢሊዮን ማይል* :- በአንድ ሰው ውስጥ በሚገኙ ሴሎች ውስጥ የሚገኝ  የዲኤንኤ ጥቅል ክር ተበትኖ ቢቀጣጠል የሚደርሰው ርዝመት መጠን

*6.5 ጫማ* ፦ በአንዲት የሰውነታችን ሴል ውስጥ የሚገኝ ጥቅልል የዲኤንኤ ክር ርዝመት።

*1%*:- በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኘው ዲኤንኤ ውስጥ genes (ባህሪያተ ዝርያን) የሚያበጀው የዲኤንኤ መጠን የተቀረው 99% ዲኤንኤ አስፈላጊነቱ እንቆቅልሽ እንደሆነ ይገኛል። የሳይንቲስቶች ፍንጭም ከመላምት ግምት የዘለለ አይደለም።

*99.9%* በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኘው ዲኤንኤ መጠን ውስጥ በሁላችንም ውስጥ የሚገኝ ተመሳሳይ የዲኤንኤ መጠን

*8%* በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኘው ዲኤንኤ ውስጥ በጥንት ዘመን የሰውን ልጅ ሲያጠቁ ከነበሩ ቫይረሶች የተወረሱ የዲኤንኤ መጠን ሲሆን ይህም ከ40 ሚሊዮን ዓመታት በፊት የተዛመደ እንደሆነ ይነገራል። ከ20k-25k በዲኤንኤያችን ውስጥ የሚገኘው የጅንስ ዘረመል መጠን

*2 ቢሊዮን*:- በዘንድሮው የፈረንጆቹ ዓመት 2019 በ50 ሃገራት መሪዎቻቸውን ሊመርጡ ወደ ምርጫ ጣቢያ የሄዱ (የሚሄዱ) መራጮች ብዛት። ከእነዚህ መራጮች ውስጥ ህንድ 800 ሚሊዮን፣ ኢንዶኔዥያ 187 ሚሊዮን ናይጀሪያ 84 ሚሊዮን የተመዘገቡ  መራጮች ናቸው።

*ቁማር ለበጀት*:- የዛሬ አስር ዓመት አሜሪካ ከ30 ዓመት በሁዋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቆማሪዎች ገቢ ግብር 1.78 ቢሊዮን ደላር ቅናሽ አሳየ። በ2 ነጥብ 6 በመቶ በማዘቅዘቁ ምክንያት የበጀት ጉድለት እንዲታይ ምክንያት ሆኗል። ይህንን ጉድለት ለመሙላት ቁመራን ማጧጧፍ በመሆኑ 25 ክልሎች (ስቴቶች) ቁመራን የሚያበረታቱ አሰራሮችን በዘመቻ መልኩ ዘርግተው ነበር።



በስመ ጥሩው አሜሪካዊ ኦራተር ጆርጅ ብሉኒ ጃኔስፕሬስ ቡናን በማስተዋወቅ የሚያገኘውን አብዛኛውን ገቢ በቅርቡ በመፈንቅለ መንግስት የተወገዱትን በአለም አቀፍ ፍርድቤት በጥብቅ የሚፈለጉትን የሱዳኑን ፕሬዝዳንት ኦማር አልበሽር ላይ ክትትል የሚያደርገውን ሳተላይት ወጭ መሸፈኛ የአደረገ ሰው ነው።

# ኪጋሊ እንደምን ጽዱ ሆነች



**ኪጋሊ የሚያስቀና ብቃትዋ እንደ መርካቶ በቀን ሁለቴ መጠረግዋ አይደለም፤ አንድም ሰው እንኳን ገበያ ውስጥ ቆሻሻ አለመጣሉ ነው፡፡**


ሩዋንዳ በማዕከላዊ አፍሪካ የምትገኝ ሰፊና የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ ስብጥርን ያቀፈች ሀገር ናት፡፡ በያዝነው የፈረንጆች ዓመት በተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት 12 ነጥብ 7 ሚሊዮን የህዝብ ብዛትና 26 ሺህ 338 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አላት፡፡ ኪንያሩዋንዳ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛና ስዋህሊ በስፋት የሚነገሩ ቋንቋዎች ናቸው፡፡

በሀገሪቱ የክርስትና ኃይማኖት ቀዳሚውን ስፍራ ሲይዝ ሌሎች አገር በቀል እምነቶች ደግሞ ተከታዩን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ሩዋንዳ ከሶስት ዋና ዋና ጎሳዎች የተውጣጡ ህዝቦች የሚኖሩባት ሲሆን ሁቱ 84 በመቶ፣ ቱትሲ 15 በመቶ እና ታው አንድ በመቶ ከአጠቃላዩ የህዝብ ቁጥር ይሸፍናሉ፡፡

## *የሩዋንዳ ጥቁር ታሪክ*

ከሚያዝያ እስከ ሰኔ 1994 እ.ኤ.አ በአንድ መቶ ቀናት ውስጥ ብቻ ከስምንት መቶ ሺህ በላይ ሩዋንዳዊያን በእርስ በእርስ ጦርነት ያለቁበትና ደም የተቃቡበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በአገሪቱ ልቅሶና ዋይታ እዚህም እዚያም ይሰማ ነበር፡፡ የሰው ልጅ እንደቅጠል የረገፈበት በመሆኑም በአለም አሰቃቂው እልቂት ተብሎ በታሪክ ድርሳናት ተመዝግቧል፡፡

የዘር ማጥፋት ወንጀሉ እንዲጫርና እንዲስፋፋ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛው መነሻ ግን ከሁቱ ጎሳ የሚመዘዘው የወቅቱ የሩዋንዳ ፕሬዝዳንት ጁቬኔል ሀቤራሪማ ሚያዝያ 1994 እ.ኤ.አ በአውሮፕላን አደጋ መሞታቸው ነው፡፡ ቀደም ባሉ ጊዜያት አልፎ አልፎ የሚነሱ ብጥብጦች ቢኖሩም ነገር ግን በሁቱና በቱትሲ ጎሳዎች መካከል የነበረው ጥላቻ ሰፍቶ ለበርካታ ሩዋንዳዊያን ህልፈት መንስኤ ሆኗል፡፡



*በኪስዎ 10 ዶላር ከአለዎት እና ምንም ዓይነት ብድርም ሆነ ዱቤ የሌለብዎት ከሆኑ እውነት እውነት እንልዎታለን እርስዎ ከ25% አሜሪካዊ የተሻለ ሃብታም ነዎት፡፡ የብድር ኑሮ አሜሪካ!*

ሁለቱ ጎሳዎች በጣም ተመሳሳይ የሆነ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ቢሆንም በመካከላቸው የተዘራው የጥላቻ ዘር አፍርቶ ሀገሪቱን የጦር አውድማ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ዛሬ ይህ ታሪክ ከተፈጸመ ከ20 አመት በኋላ ሩዋንዳዊያን ካለፈው ታሪካቸው ተምረውና "ይቅር ለእግዜር" ተባብለው በተባበረ ክንድ አገራቸውን በእድገት ጎዳና እየመሯት ይገኛሉ፡፡

ከሩዋንዳ ፈጣን እድገትና አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመተግበር ካስመዘገበችው ስኬቷ ባሻገር እኛም ኢትዮጵያዊያን የዘር ጥላቻን አሽቀንጥሮ በመጣልና ያለፈውን ቁርሾ በመተው ለልማታችንና ለሀገራዊ አንድነታችን መትጋት እንደሚኖርብን ህያው ትምህርት መውሰድ እንችላለን፡፡

"ከሩዋንዳ ፈጣን እድገትና አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመተግበር ካስመዘገበችው ስኬቷ ባሻገር እኛም ኢትዮጵያዊያን የዘር ጥላቻን አሽቀንጥሮ በመጣልና ያለፈውን ቁርሾ በመተው ለልማታችንና ለሀገራዊ አንድነታችን መትጋት እንደሚኖርብን ህያው ትምህርት መውሰድ እንችላለን፡፡"

## ጽዳትና ኪጋሊ

የሩዋንዳ መናገሻ ኪጋሊ የአዲስ አበባን ሩብ የሚሆን ህዝብ የሚኖርባት በጽዳቷ ቀልብን የምትገዛና ለብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ተምሳሌት የሆነች ከተማ ነች፡፡ በ2008 እኤአ የአካባቢን ስነ ምህዳር የሚበክሉ የፕላስቲክ ውጤቶች እንዳይመረቱ በምትኩ አካባቢን በማያበላሹ ምርቶች እንዲተኩ በመወሰኑ ለከተማዋ ጽዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በአብዛኛው የአፍሪካ ከተሞች የሚስተዋለውን የፕላስቲክ ተረፈ ምርት በዚች ከተማ አይመለከቱም፡፡ እግር ጥሎዎት ሩዋንዳ ከደረሱ በያዙት ሻንጣ ውስጥ የፕላቲክ ውጤቶች ካሉ በሌሎች አካባቢን በማይበክሉ ምርቶች እንዲተኩ ይነገርዎታል፡፡ ህዝቡ ቆሻሻን የሚጠየፍ ባህል ከማዳበሩ በተጨማሪ አስገዳጅ የህግ ማእቀፍ በማውጣቱ ብሎም ለተግባራዊነቱ ርብርብ በመደረጉ ተጨባጭ ለውጦች ሊመጡ ችለዋል፡፡

## ኡሙጋንዳ

የኪጋሊ ከተማ በመላው አፍሪካ ንጹህ የሆነች ከተማ ነች፡፡ እንደ ሩዋንዳ ህዝብ በራስ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት የአካባቢውን ንጽሕናን የጠበቀ የአፍሪካ ሀገር የለም፡፡ በዚህም ሩዋንዳን የጎበኙ ሁሉ ውብና ጽዱ መሆንዋን ይመሰክራሉ፡፡

*እስራዔላዊያን ዘንድ ጎረመስኩ ብሎ ሱሪ ዝቅ ማድረግ የለም 18 ዓመት የሞላው/ት ወጣት ወንዱ 2 ዓመት ከስምንት ወር ሴቷ ደግሞ 2 ዓመት የሃገሪቱ ጦር ሃይል አባል ሆነው በውትድርና የማገልገል ግዴታ ብቻ ሳይሆን ባህልም አላቸው፡፡ ትኩስ ጉልበቱን ከከፋም ህይወቱን ለሃገሩ ሲሰጥ ሃገሩን የመውደድ ሃገርን የማስቀደም ውርስ ያስቀጥላል፡፡*

የኪጋሊ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤታቸውን ወይም የአካባቢያቸውን ንጽህና በመጠበቃቸው የሚያተርፉትን ስለሚያውቁ ጎትጓች ወይም ህጋዊ ጫና እንደማያስፈልግ ያምናሉ፡፡ ጽዳት የሩዋንዳዊያን ሀብትና ኩራት ነው፡፡ የተማረው፣ ያልተማረው፣ ሃብታምና ደሀው የጎዳና ተዳዳሪዎች ሳይቀሩ ስለጽዳት ጠቀሜታ ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ የያዙ ናቸው፡፡

ሩዋንዳዊያን በአገራችን ደቦ ወይም ወንፈል እንደምንለው ባህላዊ የመረዳጃ ስርዓት አላቸው፡፡ ኡሙጋንዳ ይሰኛል፡፡ ኡሙጋንዳ በወሩ የመጨረሻ ቀን ላይ ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ ቀኑ 5ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚካሄድ አገር አቀፍ የጽዳት ዘመቻ ሲሆን ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ የሆነና ከ18 እስከ 65 ዓመት ዕድሜ ያለው በኡሙጋንዳ ውስጥ የመሳተፍ የውዴታ ግዴታ አለበት፡፡

በከተማዋ በወሩ መጨረሻ ቅዳሜ ጠዋት ከጽዳት ስራ ውጭ ምንም ነገር አይታሰብም፤ ሱቆች ይዘጋሉ፣ የህዝብ ማመላለሻዎችንም ሆነ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ከቦታ ቦታ ማዘዋወር አይፈቀድም፡፡ በዚህ ቀን የከተማዋ ነዋሪ ሙሉ ትኩረቱ በጽዳት ስራው ላይ ነው፡፡ በከተማዋ በየቦታው መጸዳዳት ነውር ከመሆኑ በተጨማሪ ከፍተኛ ቅጣትን ያስከትላል፡፡ ለዚህም የሚሆን ዘመናዊ የህዝብ መጸዳጃዎች በመገንባት ማንኛውም ሰው በተመጣጣጣኝ ክፍያ የሚስተናገድበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

ከጽዳት ስራው በተጨማሪ በከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች፣ በአደባባዮች፣ በአገልግሎት መስጫ ተቋማ ትና በተከለሉ ፓርኮች እጽዋትን የመትከልና የመንከባከብ ስራ ይሰራል፡፡ ይህም ከተማዋ ንጹህና ማራኪ ከማድረግ በተጨማሪ የደን ሽፋኗ እንዲያድግና የአገሪቱ የቱሪዝም ፍሰት በአመቱ አስር በመቶ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ የሩዋንዳ ልማት ቦርድ መረጃ እንደሚያሳየው ባለፈው የፈረንጆች ዓመት 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ቱሪስቶች አገሪቷን ጎብኝተዋታል፡፡ በዚህም ከ3,74 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ችለዋል፡፡

በዚህ የትብብርና የጽዳት ስራ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሜን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ ግለሰቦችና የከተማዋ ነዋሪ ይሳተፋሉ፡፡ እነሆ ይህ

*“ጽዳት የሩዋንዳዊያን ሀብትና ኩራት ነው፡፡ የተማረው፣ ያልተማረው፣ ሃብታምና ደሀው የጎዳና ተዳዳሪዎች ሳይቀሩ ስለጽዳት ጠቀሜታ ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ የያዙ ናቸው፡፡”*



*ብራዚል፣ አውስትራሊያ፣ ኢኳዶር፣ እስኮት ላንድ እና ኩባ የዜጎቻቸውን የመምረጥ መብት ለማስፋት የመመረጥ እድሜ መነሻ 16 ዓመት እንዲሆን ያደረጉ አገራት ናቸው፡፡*

የጽዳት ባህል ከጀመረ በርካታ አመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ስኬትም አስመዝግቧል። የኪጋሊ ከተማም ውብና የነዋሪው የአይን ማረፊያ እንድትሆን አድርጓታል።

## *መዲናችን ከኪጋሊ ምን ትማራለች?*

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ከተማዋን ጽዱና ከአፍሪካ ሞዴል ከተማ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል። ኤጀንሲው የከተማዋን ጽዳት ለማስጠበቅ ብሎም ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለአለም አቀፍ ተቋማትም ሆነ ለጎብኝዎች ተመራጭ ከተማ እንድትሆን ለማስቻል በዘርፉ ስኬታማ የሆኑ የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ በመቀመር ተግባራዊ እያደረገ ነው።

አቶ ካሳሁን ጸጋየ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው። በ2010 ዓ.ም የሩዋንዳን ዋና ከተማ ኪጋሊን የጎበኙ ሲሆን ከተማዋን እግር ጥሎት ምድሯን ለረገጠ ቀርቶ ተወልዶ ለአደገባትም የአገሬው ሰው ቀልብን የምትገዛ መሆኗን ይመሰክራሉ።

ሩዋንዳዊያን የዛሬ 20 አመት ባሳለፉት አስከፊ የእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ቀባሪ አጥተው በወዳደቁ የሰው ልጅ አካላት እና በሌሎች የቆሻሻ ክምሮች ምክንያት ከተሞቻቸው ጽዳት ርቋቸው ለአይን የሚያስጠይፉ ለአፍንጫ የሚከረፉ ሆነው ነበር። ከዚህ አስቃቂ ታሪክ በኋላ ኡሙጋንዳ የተሰኘውን የመረዳጃ ባህል ወደ ጽዳት ስራው በማምጣት ኪጋሊንም ሆነ ሌሎች የሩዋንዳ ዋና ዋና ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ ማድረግ እንደተቻለ አቶ ካሳሁን ያስረዳሉ።

በጉብኝታቸው ወቅት የኪጋሊ ነዋሪዎች ጽዳት የህይዎታቸው አንድ አካል መሆኑን መታዘባቸውንና ይህንን ልምድ በአገራችን ርእሰ ከተማና በሌሎች የክልል ከተሞች ተግባራዊ በማድረግ ውብና ጽዱ አካባቢን መፍጠር እንደሚቻል ጽኑ እምነት አላቸው።

ኪጋሊ በህዝብ ብዛትም ሆነ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር ስትነጻጸር ውድድር ውስጥ የማትገባ አነስተኛ ከተማ ነች። ከተማዋ ጽዱ የሆነችው ለጽዳትና ውበት ስራ በርካታ ገንዘብ በመበጀቷ ሳይሆን የአመለካከት ቀረጻ አስቀድሞ በመሰራቱና የአመራር ቁርጠኝነት በመኖሩ መሆኑን  የጠቀሱት አቶ ካሳሁን በዚህ መንገድ ከተማችንም ሆነ ሀገራችን ከተጓዘች እንደ ሩዋንዳ ውብና አረንጓዴ መሆን እንደሚቻል አጫውተውናል።

መንግስት ብቻውን የከተሞችን ጽዳት መጠበቅ ስለማይችል ከሁሉም የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ወጥ የሆኑ አሰራሮችን በመዘርጋትና ሁሉንም የከተማዋ ነዋሪ በማሳተፍ የጽዳት ባህልን ማዳበር ይቻላል።

የከተማችን ነዋሪዎች እንደ ኡሙጋዳ ያሉ እድር፣ እቁብ፣ ማህበርና ሌሎች ማህበራዊ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ከሰርክ ስራዎቻቸው ጎን ስለአረንጓዴ ልማት ፋይዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት የመዲናችንን ጽዳት አንድ እርምጃ ወደ ፊት ማስኬድ ይቻላል።

እድሮች ሙታንን ከመቅበርና የአዘኑትን ከማጽናናት ባለፈ በከተማዋ የሚታዩ ስር የሰደዱ ማህበራዊ ችግሮችን ከመንግስት ጎን በመሰለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው። በመዲናዋ ከ7 ሺህ 500 በላይ እድሮች እንደሚገኙ የሚገልጹት የአዲስ አበባ እድሮች ሰብሳቢ አቶ ታምራት ገብረማርያም እድሮች ያላቸውን አቅም በመጠቀም የከተማዋን ጽዳትና ውበት መጠበቅ እንደሚቻል አስረድተዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ፊትአውራሪነት በየወሩ መጨረሻ በሚካሄደው የጽዳት ዘመቻ እድሮች አባላቶቻቸውን በመቀስቀስና ተሳታፊ እንዲሆኑ እየተደረገ መሆኑን ያጫወቱን አቶ ታምራት የከተማዋን ጽዳት ለመጠበቅ በተደራጀ አግባብና በቀጣይነት ባለው መንገድ ተሳትፎአቸውን አጠናክረው



*መሳው የዓለማችን ህዝብ በሙሉ አኗኗሩ እና ፍጆታው እንደ አሜሪካዊያን ቢሆን ይህንን አኗኗር በዘላቂነት ለማስቀጠል አራት ምድሮች (ፕላኔቶች) በአስፈለጉ ነበር። የአዲስ አበባ ሰው ሲተርት ‹‹ሲያገኝ እንደ አሜሪካ፣ ሲያጣ እንደ ባዶ ታኒካ›› የሚለው ለካስ እውነት ነው።*



ጎዳናዎችን ማፅዳትና ለዓይን ማራኪ ማድረግ የኪጋሊ ነዋሪዎች የዕለት ከዕለት ተግባር ነው እንደሚቀጥሉ አስረድተዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ 600 ማህበራትን ያቀፉ 74 የጽዳት የሽርክና ማህበራት፣ 11 ሺህ በጽዳት ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች፣ 5 ሺህ የመንገድ ጽዳት ሰራተኞች እኛ በርካታ የመረዳጃ ማህበራት ቢኖሯትም የከተማዋ ጽዳት ግን አሁንም በሚፈለገው ደረጃ ሊሆን አልቻለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቆሻሻን በማስወገድ ከተማን ጽዱ ማድረግ እንደማይቻል ጥሩ ማሳያ መሆኑንና ከተማዋን ከቆሻሻ ነጻ ለማድረግ እንደ ሩዋንዳዊያን ጽዳትን ባህሉ ያደረገና ባለቤት የሆነ ማህበረሰብ መፍጠር እንደሚገባ የፅዳትና ውበት ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ዑደት ዳይሬክቶሬት ፋይሬክተር አቶ ካሳሁን አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

## *የከተማችን ጸዳት እንዲጠበቅ ምን ይደረግ?*

## 1. የጽዳት ዘመቻዎችን ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ

### 1.1 ከተማ አቀፍና ሀገር አቀፍ የጽዳት ዘመቻዎችን ማጠናከር

በከተማችን በመንግስት ተቋማት ቀስቃሽነት ብሎም በተዋቂ ግለሰቦች አነቃቂነት ህብረተሰቡን ያሳተፉና ለውጥ ያመጡ የጽዳት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ህዳር 30 ቀን 2010 ዓ.ም በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ መሪነት በየካ ክፍለከተማ ወረዳ ስድስት በሴቶች መታሰቢያ አደባባይ የተጀመረውና በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የቀጠለውን የጽዳት ዘመቻ ተጠቃሽ ነው፡፡

የህዳር 30ው የጽዳት ተሞክሮ ቀጣይነት እንዲኖረውና የተሳለጠ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርአትን ለመተግበር ፖሊሲ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የህዝብ ንቅናቄና የአስተሳሰብ ቀረጻ ስራ መስራት ወሳኝና ተቀዳሚ መሆኑን ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ባህል ለማሻሻል በመንግስት ብቻ



*የኢራቅ ፕሬዚዳንት ሳዳም ሁሴን ለዳግም የ2002 የፕሬዚዳንትነት የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘፈኑ የጥቁር ዕንቁዋ አሜሪካዊት አቀንቃኝ ዊትኒ ሆስተን "አይሳቭዩ ኦልዌይስ" ዘፈን ወደ አረብኛ የተመለሰውን ተጠቅሟል፡፡ የአረብኛ ቅጅውም "ቢሆን ዘፈኑስ ከልቡ ዘፈን ነው ሳዳም ባያረክሰው!" ተብሎለታል፡፡*

የሚከወን ባለመሆኑ ነዋሪው፣ የግል ባለሀብቶችንና ሌሎች አካላት የሚሳተፉበትን ዘላቂ የጽዳት ዘመቻ ባህልን ማስረጽና ለተግባራዊነቱም መረባረብ ይገባል፡፡

## 1.2. ህዳር ሲታጠን

በ1911 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም በአውሮፓ ለሚሊዮኖች ህይወት መቀጠፍ ምክንያት የሆነው "ስፓኒሽ ፍሉ" የተባለ የኢንፍሉዌንዛ በሽታ ወረርሽኝ ተከስቶ ነበር፡፡

በተመሳሳይ ይህ በሽታ በኢትዮጵያ ለበርካቶች ሞት ምክንያት ሲሆን የተለያዩ ስያሜዎችም ተሰጥተውት ነበር፡፡

የታሪክ ምሁሩ ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሀፋቸው ላይ እንደሰፈረው የኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር መንገድ ስራ በጀመረበት ወቅት በሽታው በመነሳቱ ምክንያት "የባቡር በሽታ" ይባል እንደነበር ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የተከሰተበትን ወር ተከትሎም "የህዳር በሽታ" ተብሎ መጠራት እንደጀመረም ያስረዳል፡፡

በሽታው በህዳር ወር 1911 ዓ.ም በአዲስ አበባ ብቻ ከ6 ሺ ሰው በላይ ሰዎችን ለሞት የዳረገ ሲሆን ይህንን እልቂት ተከትሎ የበሽታው መንስኤ ቆሻሻ እንደሆነ በመታመኑ ህዝቡ ቆሻሻ ከየቤቱ አውጥቶ እንዲያቃጥል ከቤተመንግስቱ አዋጅ ተላለፈ፡፡

ከጊዜ በኋላም "አየሩ ስለታጠነ ነው በሽታው የጠፋው" በሚል እሳቤ በየዓመቱ ህዳር በገባ በአስራ ሁለተኛው ቀን ቆሻሻን የማቃጠል ባህልን እንደቀጠለና ቀኑም "ህዳር ሲታጠን" የሚል ስያሜን ሊያገኝ እንደቻለ በዚሁ የታሪክ ድርሳን ተቀምጧል፡፡

ቆሻሻን በማቃጠል ማስወገድ የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የሚረዳ ቢሆንም ለአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ አስተዋፅኦ ስላለው ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

የሚቃጠሉት ቁሳቁሶች በተለይም ፕላስቲክ ነክ ምርቶች ካርበን፣ ሜቴንና ካርበን ሞኖክሳይድ የተባሉ ንጥረ-ነገሮችን በውስጣቸው ስለሚይዙ ለአየር ብክለት መንስኤ ይሆናሉ፡፡ ይህንን የጽዳት ባህል ዘመናዊ የቆሻሻ አወገገድ ስርዓትን በመከተል በሌሎች ቀናት በመተግበር ማስፋፋት ይገባል፡፡

*"ኪጋሊ ጽዱ የሆነችው ለፅዳትና ውበት ስራ በርካታ ገንዘብ በመበጀቷ ሳይሆን የአመለካከት ቀረፃ አስቀድሞ በመሰራቱና የአመራር ቁርጠኝነት በመኖሩ ነው፡፡"*



*ቪክቶሪያ ውድሃል አሜሪካዊት ገና የመምረጥ መብታቸው እንኳ ባልተረጋገጠበት በ1872 ለአሜሪካ ፕሬዝዳንት የተወዳደረዎች ብርቱ ሴት ናት፡፡ የምል ስትሬት ድለሳ ስራን የሰራች የመጀመሪዋ አሜሪካዊትም ናት፡፡*

## 2. ቆሻሻን ወደ ኃይል ምንጭነት የሚለውጡ ፕሮጀክቶችን ማበራከት

ረጲ የደረቅ ቆሻሻ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት በይፋ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ ፕሮጀክቱ 25 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል በአመት የሚያመነጭ ሲሆን ሃይል ከማመንጨቱ በላይ ከተማችን ጻዳቷ እንዲጠበቅ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ከውሀና ኢነርጂ ሚኒስትር ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ከደረቅ ቆሻሻ የኤሌክትሪክ ሃይል የሚያመነጨው ረጲ የደረቅ ቆሻሻ ማመንጫ ፕሮጀክት ኃይል ለማመንጨት በየዕለቱ 1,400 ቶን ደረቅ ቆሻሻ ይጠቀማል፡፡ ይህም በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ የተሰበሰበው ቆሻሻ ዓላማው ሃይል ለማመንጨት ቢሆንም የከተማዋን ፅዳት ለመጠበቅም ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ግልፅ ነው፡፡ ከሃይል ማመንጫው ከሚገኘው የአመድ ተረፈ ምርት በአመት ከ3 ሚሊዮን በላይ ለአገር ውስጥ ግንባታ የሚውል ብሎኬት እና ጡብ ማምረት ይቻላል፡፡ በዚህ ላይ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለብሎኬት ማምረቻ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ለስራ እድል ፈጠራም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

## 3. ወንዞችን ያማከለ ፕሮጀክት መቀየስ

አዲስ አበባ ሰባት ዋና ዋና ወንዞችና 65 ገባሮች ቢኖሯትም የቆሻሻ መድፊያ ከመሆናቸው ውጭ የመዝናኛና የአይን ማረፊያ አካባቢዎች ሆነው እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ ሳይሆኑ ቆይተዋል፡፡

የካቲት 14ቀን 2011 ዓ.ም የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት በይፋ ሲጀመር የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ኢንጅነር ታከለ ኡማ እንደገለጹት ከጽዳትና ውበት ባለፈ የቱሪዝም ተጠቃሚነትን ዓላማ ያደረገ ሲሆን 29 ቢሊዮን ብር ወጭ እንደሚጠይቅ አስረድተዋል፡፡

መርሀ-ግብሩ አዲስ አበባን ለሁለት ከፍለው የሚፈሱ ወንዞች ላይ ያተኮረ ሆኖ ከሰሜን አዲስ አበባ እንጦጦ ተራራ እስከ አቃቂ ወንዝ ያለውን 56 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን ድልድዮች፣ ሰው ሰራሽ ሐይቆች፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣የመዝናኛ ማዕከላት፣ የውኃ ትራንስፖርት እና የንግድ ማዕከላትን ያካተተ ግንባታም እንደሚካሄድ ገልጸዋል፡፡


ከተማችን ከሀገራችን በተጨማሪ የአፍሪካ መዲናና አለምአቀፍ መቀመጫ እንደመሆኗ ለከተማዋና ለነዋሪዎቿ የሚመጥን የተፋሰስና የአረንጓዴ የወንዝ ዳር መናፈሻ ያስፈልጋታል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ስለሺ ደገፉ በበኩላቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠንሳሽነት የተጀመረው የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክት ፋይዳው የጎላና ለከተማዋም ሆነ ለነዋሪዎቿ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን በማስገኘት አረንጓዴና ነፋሻማ ከተማን ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

## *ማሳረጊያ*


ጽዳት የአንድ ማህበረሰብ የስልጣኔ መገለጫና የከተሜነት አንዱ ማሳያ ነው፡፡ መዲናችንም ከተመሰረተች ከ130 አመት በላይ ያስቆጠረች ብትሆንም እድሜዋን የሚመጥንና የህዝቦቿን የእድገት ደረጃ የሚስተካከል የጽዳት ባህል የላትም፡፡ ለዚህም መንግስት የሚያደርገው ርብርብ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም እንደ ሩዋንዳዊያን ነዋሪውን በማሳተፍ ጽዳትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ጽዳት ባህል ሲሆን ልክ እንደ ሰርክ ስራዎቻችን ቅድሚያ ሰጥተን የምንሰራው ይሆናልና ከተማችንም ጽዱ፣ ምቹና ለኑሮ ተስማሚ ትሆናለች፡፡



ካናዳ በአለማችን የመጀመሪያው ኤሌክትሮኒክስ ገንዘቦችን ምንዛሬ ኤቲኤም ፈለሰፈች፡፡ ኤቲኤሙ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የአላቸውን የውጭ አገር ገንዘቦች ወደ ካናዳ ዶላር ወይም በተቃራኒው ይመነዝራል፡፡




እንግዲህ ክረምት ገባ አይደል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ የአንገት ልብስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እርስዎም ከአንድ ሱቅ ገብተው አንገተዎ ላይ ጠምጠም አድረገው እየወጡ ነው፡፡ የገዙት የአንገት ልብስ የትኛው እንደሆነ ያመላክቱና! ለማነፃፀሪያነት ከታች የቀሩት ዘጠኙ የአንገት ልብሶች ተቀምጠዋል፡፡ awdelewt@gmail.com



*ሂላሪ ክሊንተን የአሜሪካ ቀዳማዊት እመቤትነትንና ሴናተርነትን ለ20 ቀናት ደርበዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በሴናተርነት ቃለመሃላ ፈፅመው ስራቸውን የጀመሩት ጃንዋሪ 1/2001 ሲሆን ባለቤታቸው ፕሬዚዳንት ክሊንተን የዋይት ሃውስ ቤተመንግስትን የለቀቁት ደግሞ ጃንዋሪ 20/2001 ቀን ነው፡፡*

# የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ ለምን ታጠፈ?




- እንደ መግቢያ
- የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ ስንል
- የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራዎች ፋይዳ
- የውጪ አገራት አጭር ተሞክሮ
- የአገራችን የህብረተሰብ የተሳትፎ ሁኔታ
- የከተማችን የህብረተሰብ ተሳትፎ ታሪክ
- የተገኙ ውጤቶች
- የታጠፈበት ምክንያት፤ የከተማ አስተዳደሩ ምላሽ

## እንደ መግቢያ

የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራ ተሳታፊውን ህዝብም ሆነ መንግስትን በጋራ ተጠቃሚ የሚያደርግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአለም መንግስታት ትልቅ ትኩረት እየሰጡት የመጡት የህዝብ አስተዳደር ዘይቤ ነው፡፡ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራ የመንግስትን ጉድለቶች ህዝቡ እንዲሸፍን የሚያስችል በመሆኑ፤ ግልጸኝነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የልማት ስራዎችን ቀጣይነት በማረጋገጥ ረገድ የማይተካ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም እንደኛ በማደግ ላይ ላሉ አገራት በልዩ ሁኔታ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ዛሬ ትልቁ የመንግስታት ፈተና ህዝቡን በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ማድረግ አለመቻል ነው፡፡ ህዝብ በራሱ ጥቅም ዙሪያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመሳተፍ አስተዋጽኦ ለማበርከት ምን ጊዜም ወደኋላ የማይል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት ላይ እምነት ካጣ ደግሞ ተሳትፎው ይቀንሳል ብቻ ሳይሆን በአመጽ ከስልጣን እስከማውረድ እንደሚደርስ የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ በአንድ በኩል የህብረተሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ማለት የህዝቡን እምነት ያተረፈና ቅቡልነት ያለው መንግስት አስተዳደር እንዳለ እንደማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በአገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህዝቡን በልማትና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ለማሳተፍ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ተሳትፎው ከሚጠበቀው አንጻር ብዙ የሚቀረው መሆኑ ሁሉንም የሚያግባባ ነው፡፡ ህገመንግስቱም ሆነ ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎቻችን የህዝቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ምቹ ሆነው ሳለ፤ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩ በየአመቱ የሕዝቡን ልማት ለመደገፍ ከፍተኛ በጀት በመመደብ እየሰራ ባለበት በአሁኑ ጊዜ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አለመቻሉ በራሱ ትልቅ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡



*ከማንቂያ ባለሰዓት ደወል (አላርም) ከመፈልሰፉ በፊት ኖከር አፕስ {Knocker- ups} የተባሉ አንቂዎችን ቀጥሮ መጠቀም ነበር፡፡ አንቂዎቹ ቀጣሪያቸው በፈለገው ሰዓት ላይ መስኮቱን በአተር ፍሬዎች ደጋግመው መስኮቱ ላይ በመወንጨፍ ያነቁ ነበር፡፡*

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲን ያለፉት አመታት ሪፖርቶችን መለስ ብሎ ለማየት እንደተሞከረው የከተማችን ነዋሪ በህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ዙሪያ ተሳትፎውን ከጊዜ ወደጊዜ እያሳደገ መምጣቱን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ህዝቡ በአካባቢው ልማት ለመሳተፍ ዝግጁ እስከሆነ ድረስ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራን ለማሳለጥ ትልቅ እድል እንዳለ ተጨማሪ ማመላከቻ ነው፡፡ በመሆኑም የህግ ማዕቀፎች በተሟሉበት፣ የከተማ አስተዳደሩ የህዝቡን ተሳትፎ ለመደገፍ ትልቅ በጀት እየመደበ ባለበት እንዲሁም የከተማችን ህዝብ ለተሳትፎ ከምንጊዜውም በላቀ መልኩ ዝግጁ ሆኖ ሳለ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራን ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እንደምን ተሳነን? ብሎ መጠየቅና በሰከነ ውይይት ተገቢውን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል ብለን እናምናለን፡፡

“አንዳንድ ምሁራን ተሳትፎ ማለት ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ ማለት ነው ብለው ሲሞግቱ ሌሎቹ ደግሞ በየትኛውም ውሳኔ ላይ ህብረተሰቡ መንግስት ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ ከቻለ ብቻ ነው ተሳትፎ አለ ማለት የሚቻለው ብለው ያምናሉ፡፡ ኢኮኖሚስቶች ደግሞ ተሳትፎ ማለት ህዝቡ ከልማቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡”

በከተማችን የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራ ባለፉት ስምንት አመታት እጅግ እየጎላ የመጣና በመንግስትና በህዝቡ መካከል ድልድይ ሆኖ ያገለገለ፤ በየአመቱ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ከህዝብ በማሰባሰብ የተለያዩ የልማት ስራዎችን በመስራት የሚታወቅ ትልቅ ተቋም መሆኑን ማንም አሌ ሊለው የሚችል አይደለም፡፡ ኤጀንሲው በአሁኑ ወቅት በአዲሱ አመራር ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጠውና የላቀ የህዝብ ተሳትፎ ልማት ስራዎቸን ያከናውናል ተብሎ ሲጠበቅ ፈጽሞ ማንም ባልገመተው መንገድ ተግባራቱን ለእያንዳንዱ ተቋም በመተው እንዲታጠፍ ተወስኗል፡፡ ለምን ታጠፈ? የሚለው ጥያቄም በየደረጃው በሚገኝ አመራር ሆነ በህዝቡ ዘንድ ግራ እስከማጋባት መድረሱን በየመድረኩና በየአካባቢው እያስተዋልን ነው፡፡ በጉዳዩም ዙሪያ እየተሰጠ ያለው ምላሽም ለአመራሩም ሆነ ለአካባቢ ኮሚቴ አባላት እንቆቅልሽ እንጅ አጥጋቢ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የዝግጅት ክፍላችን ለምን ታጠፈ የሚል ሙግት ማንሳትን መርጧል፡፡ በሙግቱም ስለህብረተሰብ ተሳትፎ ፋይዳና ስለአስገኘው ተጨባጭ ጥቅም፣ ለምን እንደታጠፈና የቀጣይ የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ዳስሷል፡፡



*በአሜሪካ ወታደራዊ ቤዞች ውስጥ የሚገኙ ወታደራዊ መደብሮች የወረቀት ኖትን እንጂ ሳንቲም አይቀበሉም፡፡ እንደ አሜሪካ መከላከያ ገለፃ ምክንያቱ ደግሞ ሳንቲሞቹን ማጓጓዝ አዋጭ አይደለምና ነው፡፡*

## የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው ?

ሕብረተሰብ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ተመሳሳይ ባህሪና ጠባይ እንዲሁም የጋራ ጥቅም ያላቸው እንዲሁም ተመሳሳይ ባህል፣ ቋንቋ፣ አጊያጌጥና ተያያዥ እሴቶች ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጹሁፍ ውስጥ ህብረተሰብ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በአካባቢያቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት ለመወጣት በቀጠና የተደራጁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከኤጀንሲው ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳያው በከተማችን ውስጥ ከ770 በላይ የልማት ቀጠናዎች ያሉ ሲሆን ነዋሪው አካባቢውን ለማልማት የሚመክረው በየቀጠናው በመረጣቸው የአካባቢ ልማት ኮሚቴ አማካይነት ነው፡፡

ተሳትፎ የሚለውን ሀሳብ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ትርጉም ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ ምሁራን ተሳትፎ ማለት ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ ማለት ነው ብለው ሲሞግቱ ሌሎቹ ደግሞ በየትኛውም ውሳኔ ላይ ህብረተሰቡ መንግስት ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ ከቻለ ብቻ ነው ተሳትፎ አለ ማለት የሚቻለው ብለው ያምናሉ፡፡ ኢኮኖሚስቶች ደግሞ ተሳትፎ ማለት ህዝቡ ከልማቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ አንዳንድ ምሁራን የህብረተሰብ ተሳትፎ የመንግስት ፕሮጀክቶችን ወጤታማነት ማረጋገጫ መሳሪያ እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡


ሳሙኤል ፖል የተባለ የዘርፉ ተመራመሪ ከአካባቢ ልማት አንጻር የህብረተሰብ ተሳትፎ ማለት “የአካባቢው ነዋሪ በነቃና በተደራጀ መንገድ በአካባቢው የጋራ ጉዳዮች በተለይም በልማትና በመልካም አስተዳደር ጉደዳዮች ላይ በቀጥታ በመሳተፍ ተጽእኖ መፍጠር ሲችልና ጥቅሞቹን በጋራ የሚያጣጥምበት የአመራር ዘይቤ ነው” ሲል ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ ህብረተሰቡ በአካባቢው ልማት ላይ ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ በሶስቱ የአመራር ዑደቶች ማለትም በማቀድ፣ በመተግበርና በመገምገም ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፍ ማድረግ ነው የሚለው ብያኔ ከሞላ ጎደል ሁሉንም የሚያስማማ ነው፡፡

የዓለም ባንክ በ1987 ባሳተመው የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ምንነት ላይ ይህንኑ የሳሙኤል ፖል ብያኔን ተጠቅሞ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ አጭር ጹሁፍ ውስጥም የአዲስ አበባን የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራን የሳሙኤል ፖል ብያኔ ተስማሚ በሆነ መንገድ ገልጾታል፡፡ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስንል ህዝቡ ችግሮችን የሚለይበት፣ የመፍትሄ ሀሳብ በራሱ የሚያመነጭበትና ችግሩን ለመፍታት ሀብት የሚያሰባስብበትና ውሳኔ የሚሰጥበት በመሆኑ የነዋሪዎች ተሳትፎ ከብያኔው ጋር አንድ አይነት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

## የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራዎች ፋይዳ

ቀደም በአሉት ዓመታት የዓለም ባንክ የህብረተሰብ ተሳትፎ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት በተለያየ ጊዜ ባሳተማቸው ጹሁፎች ላይ ይፋ አድርጓል፡፡ በዚህም ዘርፉ በቀላሉ የአካባቢውን እውቀትና እምቅ ችሎታ ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ የመጀመሪያው ፋይዳ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ “የአገሩን በሬ በአገሩ ሰርዶ” እንዲሉ የአገሬ ሰው የምሁራን ወይም የጥናት ጋጋታ የማይፈታውን ውስብስብ ችግሮች ከችግሩ ጋር የኖሩትና መንስኤውን ጠንቅቀው የሚያውቁት የአካባቢው ነዋሪዎች እንደዋዛ ሲፈቱት ማየት የተለመደ ተግባር እየሆነ መጥቷል፡፡ እንደ ከተማችን ተጨባጭ ሁኔታም ነዋሪው ያሉበትን ችግሮች መንግስትን ሳይጠብቅ ገንዘቡን በማዋጣት፣ጉልበቱንና እውቀቱን ተጠቅሞ አሁን ላይ የከተማዋ አብዛኛው አካባቢ በማልማት ለኑሮ ምቹና ውብ በማድረግ የከተማዋን ችግር እየቀረፈ መጥቷል፡፡

ሌላውና በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጠው የህብረተሰብ ተሳትፎ ፋይዳ መንግስት የሚሰራቸውን ማናቸውንም ስራዎች ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡ ህዝቡ የባለቤትነት



*አሜሪካኖች ለፕሬዚዳንቶቻቸው ደህንነት እጅግ በጣም ስሱ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ፕሬዚዳንቱ በጽህፈት ቤታቸው ውስጥ ሆነው እንኳን በትክክል የትጋ እንደሚገኙ የሚጠቀም ክብደትን መሰረት ያደረገ የሴንሰር ስርዓት በቢሯቸው ውስጥ ሳይቀር ተዘርግቷል፡፡*



ቂርቆስ ክ/ከተማ ጎተራ ኮዶሚኒየም በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ የህዝብ መናፈሻ

መንፈስ እንዲሰማው ማድረግ የሚቻለው በማሳተፍ ብቻ ነው፡፡ ተሳትፎውን በሚገባ ያረጋገጠ ህብረተሰብ ከመንግስት ብቻ እያንጋጠጠ የሚጠብቅ ሳይሆን የራሱን ድርሻም ለመወጣት ጥረት የሚያደርግ ይሆናል። በመሆኑም ህዝቡን በተደራጀ መንገድ ማሳተፍ ከተቻለ ከፍተኛ የሆነ ሀብት በቀላሉ ለማሰባሰብ ምቹ እድል ይፈጥራል ማለት ነው። ህዝብን ማሳተፍ ከተቻለ የጥቅም ግጭቶችን ለመፍታትም እዳውን ገብስ ማድረግ ይቻላል። ያለውን መካፈልና ማን ምን ድርሻ ሊኖረው እንደሚገባ ህዝቡ እራሱ ያውቃልና ጦር ሳይማዘዝ ደም ሳይፋሰስ የጥቅም ግጭቶችን መፍታት ይችላል፡፡

የልማቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥም የህብረተሰቡ ተሳትፎና ድርሻ የጎላ ነው። የተለያዩ አገራት የጥናት ወረቀቶች እንደሚያመላክቱት ለአንድ የልማት ፕሮጀክት ተብለው የሚፈጠሩ የህብረተሰብ ተሳትፎ አደረጃጀቶች ከፕሮጀክቶቹ መጠናቀቅ በኋላም እንደማይፈርሱና ይልቁኑ ወደሌላ የልማት ስራዎች እንደሚሸጋገሩ ያረጋግጣሉ፡፡ በመሆኑም የህዝቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ ከተቻለ ህዝቡ የተሰራውን ፕሮጀክት መጠበቅና መንከባከብ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ የልማት ስራዎችን ወደመስራት የሚሸጋገርና የባለቤትነት ስሜት እንደሚፈጥርበት ያደርገዋል። እነዚህ ከላይ የተገለጹ ሀሳቦች በሙሉ የዓለም ባንክ ያመነባቸውና በግልጽ በዶክመንቶቹ ያመላከታቸው ሀሳቦች ናቸው፡፡

## *ከህብረተሰብ ተሳትፎ አንጻር የውጪ አገራት አጭር ተሞክሮ*

የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንደየ አገሩ የእድገት ደረጃ ቢለያይም በኢኮኖሚ በበለጸጉት አገራት የሚገኙ ዜጎች መብታቸውን ለማስከበርና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሁሉም መስክ የሚያደርጉት ተሳትፎ የጎላ




*በግምት 15 የራሽያ ከተሞች በቱሪስት ስመኅብኝት ልዩ ፍቃድ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እነዚህ ከተሞች ውስጥ ጥብቅ ምስጢር ያለባቸው ስሞችና ስፍራዎች ስለሚገኙ ነው፡፡*

ነው፡፡ ለምሳሌ በአውሮፓና አሜሪካ የሸማቾች ማህበር እጅግ በጣም ጠንካራና አላስፈላጊ የዋጋ ንረትን በመከላከል ረገድ ሚናው እጅግ የጎላ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ እንደ እኛ አገር የመሰረታዊ ፍጆታ ዋጋ ኀዋኀዋ እንዳይጫወት ቀጥ አድርገው ገበያውን የሚመሩት በሚያደርጉት ተሳትፎ ነው፡፡ የዜሮ አምስት ሳንቲም የመሰረታዊ ሸቀጥ ዋጋ ጭማሪ ነውጥ በሚያስነሳ መልኩ ተደራጅተው መብቶቻቸውን በተሳትፏቸው ያረጋግጣሉ፡፡

የአብዛኛው አገራት ተሞክሮም ተመሳሳይ ነው፡፡ እኛም የሁሉንም አገራት ተሳትፎ ለመፈተሽ ብንሞክር እጅግ አስደናቂ የሆኑ ተሞክሮዎችን ማግኘት እንደምንችል ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ይሁን እንጅ ጊዜና ቦታ ስለማይፈቅድልን የከተማ ልማት ሚኒስቴር በተሞክሮነት የቀሰማቸውን የአምስት አገራት የህብረተሰብ ተሳትፎን በአጭሩ ቃኝተን በዚህ መልኩ ይዘን ቀርበናል፡፡

የመጀመሪያዋና ለከተማችንም ዋነኛ ተሞክሮ ትሆናለች ብለን የቃኘናት የሩዋንዳን ዋና ከተማ ኪጋሊን ነው፡፡ ኪጋሊ በጽዳቷና ውበቷ ከአፍሪካ ከተሞች በቀዳሚነት መጠቀስ የቻለች ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ በዘመናዊ የጽዳት አስተዳደሯ ከአፍሪካም ብቻ ሳይሆን ከአውሮፓ ከተሞች ጋርም እንድትስተካከል አድርጓታል፡፡ በየመንገዱ በድፍረት መጸዳዳት ቀርቶ ከእጅ የሚጣሉ ብጣሽ ወረቀቶችን በኪጋሊ ዋና ዋናና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ፈልጎ ማግኘት ይከብዳል፡፡ ኪጋሊ ንጹህና ውብ ከተማ እንድትሆን ያስቻላትም የተለየ ሀብትና ቆሻሻ የማታመነጭ ከተማ ሆና ሳይሆን ቆሻሻን የሚጠየፍ ማህበረሰብ መፍጠር በመቻሉ ነው፡፡ ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ቆሻሻን በአግባቡ ያስወግዳል፡፡ ቆሻሻውንም በየፈርጁ በመለየት የሀብት መፍጠሪያ እንጅ እንደ ችግር አይታይም፡፡ በዚህም ሩዋንዳዊያን ዋና ከተማቸውን ንጹህና ውብ እንዲሁም አረንጓዴ በማድረግ ለሌሎች አገራት ምሳሌ መሆን ችለዋል፡፡ የኪጋሊ ነዋሪዎች ከጽዳት ባሻገር ለአረንጓዴ ስፍራዎችም የተለየ ፍቅርና ቦታ ይሰጣሉ፡፡ አረንጓዴ ስፍራዎች ላይ ሳት ብሎ እግር መስደድ ነውር ነው፡፡ ከአገራችን ተሞክሮ ለመቅሰምና ጎብኝተው ለመመለስ ወደ ከተማዋ ያቀኑ አንዳንድ

***"ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ የህዝቡን ተሳትፎ ለማቀጣጠል ምቹ ሁኔታ ባለበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲን በከተማ ደረጃ ተቋሙን ከተልዕኮ ውጪ ማድረጉ ግርምት የፈጠረባቸውም አሉ፡፡"***



*በታላቁ የግሽበት ዘመን {Great depression} በ1933 የወጣው ረቂቅ ህግ የአሜሪካዊያን የግል ሃብት ከአንድ ሚሊዮን ዶላር እንዳያሻቅብ የሚያግድ ነበር፡፡*


ሰዎች እንደለመዱት አረንጓዴ ቦታዎች ውስጥ ዘው ብለው ገብተው ፎቶ ሲነሱ በሀገሬው ሰው ቆፍጠን ያለ ወቀሳ እንደሚያስተናግዱ ይሰማል፡፡ ይህ ተሞክሮ ወደ ሀገራችን መምጣት አለበት፡፡ አዲስ አበባም ከምትታወቅበት አፍንጫ ከሚሰነፍጡ መንገዶቿና ከቆሻሻ ክምሯ ተላቅቃ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ ከተማ እንድትሆን ከኪጋሊ ያገኘቻቸውን ተሞክሮዎች ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች፡፡ ይህ መልካም የሆነ ጅማሬ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና የታሰበውን ዓላማ እንዲመታ የተጠናከረ የህብረተሰብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

ሌላው በታንዛኒያ ያለን የህብረተሰብ ተሳትፎን ስናይ፤ የታንዛኒያ መንግስት ማንኛውንም የልማት ስራ ለማከናወን መጀመሪያ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚንቀሳቀሰው ህዝቡን በየአካባቢው በማደራጀትና የህዝብ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በመምረጥ ነው፡፡ ህዝቡ በአካባቢው የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፍ በማድረግም ጥሩ ተሞክሮ አለው፡፡ በታንዛኒያ የአካባቢ ልማት ኮሚቴዎችና አደረጃጀቱ በመንግስትና በህዝቡ መካከል የመረጃ ልውውጥ መድረክ በመሆን እንደሚያገለግልም የተቀመሩ ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም መንግስት ከህዝቡ መረጃ መሰብሰብ በሚያስፈልገው ወቅት የመንደር የልማት አደረጃጀቶች ተዓማኒ የመረጃ ምንጭ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ መንግስት ህዝቡ ጋር ተደራሽ ማድረግ የሚፈልገውን መረጃም በቀላሉ ለማድረስም የተሻለው አማራጭ ይህ የመንደር የልማት አደረጃጀት ነው፡፡ መንግስት ህዝቡን በማንኛውም የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች በማሳተፉም በየአካባቢው ያሉ ችግሮችን በወቅቱና በፍጥነት በመፍታት መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲያጎለብትም አስችሎታል፡፡

በቻይና ያለውን የህብረተሰብ ተሳትፎን ስንቃኝም ቻይናዊያን ቀደም ብለው ጠንካራ የሥራ ባህላቸውንና በአነስተኛ ቴክኖሎጂ ጉልበትን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅመው የማምረት አቅማቸውን ያሳደጉት በህዝቡ የነቃ ተሳትፎ ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔን ማሻሻል፣ ማህበራዊ ልማት ከህብረተሰቡ ጋር እንዲዛመድ በማድረግ ረገድ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነበር፡፡ በቻይና ህዝቡን በማሳተፍና የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው በማድረግ መስራት በመቻላቸው በሁሉም የልማት መስኮች ውጤታማ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ቻይና አሁን ላይ የኢኮኖሚ አቅሟ አድጓል፡፡ የዜጎችም የነፍስ ወከፍ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተለወጠ መጥቷል፡፡ የስራም ባህላቸው የተሻለና በመደራጀት ውጤት እንደሚመጣ አምነው በመስራታቸው ዓለምን ያጥለቀለቀ ምርት በማምረት አገራዊ ተሳትፎአቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ደቡብ ኮሪያም በዜጎቿ መካከል ቀና የሆነ የውድድርና የተሳትፎ መንፈስ በመፍጠር፣ የሥራ ቀናትና ሰዓት በማሻሻል፣ እንዲሁም የቁጠባና ብድር ማህበራት እንዲስፋፉ በማድረግ የህዝቡ ተሳትፎ እጅግ እየጎለበተ እንዲመጣ አድርጋለች፡፡ በተለይ ማንኛውንም ተግባር ከመፈጸሟ በፊት ዜጎቿ አምነውበት እንዲገቡና ውጤት እንዲመዘገብ ቀድማ እየሰራች በመምጣቷ መንግስት በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ የህብረተሰብ ተሳትፎውና አሳታፊነቱም ተጠናክሮ እንዲቀጥል በደቡብ ኮሪያ የተለያዩ የልማት መርሀ ግብሮች ሳይቀር በትምህርት ቤቶች ከሰንደቅ ዓላማ መስቀልና ማውረድ ጋር በማዛመድ በመፈክሮችና በሌሎች አመቺ ዘዴዎች ለተማሪዎች የማሳወቅና የማስገንዘብ ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህም ምክንያት ደቡብ ኮሪያ በህዝቡ ተሳትፎና ተራማጅ አስተሳሰብ በአላቸው መሪዎቿ ዛሬ ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ እንድትደርስ አስችሏታል፡፡

በሕንድም የህብረተሰብ ተሳትፎው ይበልጥ ጎልቶ የሚታወቀው በህዝቡ ወደር የለሽ የቁጠባ ባህል ነው፡፡ ከየትኛውም የአለማችን ህዝብ የላቀ የመቆጠብ ባህል ያለው ሕንድ አገር ነው፡፡ ሕንዶች በልተው ጠጥተው የተረፋቸውን ሳይሆን ከሚያገኙት ገቢ ላይ መቆጠብ ባህላቸው ነው፡፡ የገቢ መጠናቸው የቁጠባ መጠናቸውን ይወስናል እንጂ ከመቆጠብ አያግዳቸውም፡፡ እንዲቆጥቡ ያደረጋቸው መሰረታዊ ምክንያትም ኢንቨስትመንት ነው፡፡ አንዳንድ አላዋቂ የአገራችን ዜጎች እንደሚሉት ሕንዶች ስግብግብ ሆነው ሳይሆን ነገን በተሻለ ለመኖር በማሰብ ዛሬ ቁጠባን ባህላቸው አድርገው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ህዝባዊ መሰረት ያለው የቁጠባ ባህላቸውም አገራቸውን አስተማማኝ የኢንቨስትመንት ካፒታል ክምችት እንዲኖራት ከማስቻሉም በላይ ሕንድ ዛሬ



*የ1896 የእንግሎ ዛንዚባር ጦርነት የዓለማችን አጭር ጦርነት ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል፡፡ 38 ደቂቃ ብቻ ነው የፈጀው ዛንዚባሮች እጅ እስኪሰጡ፡፡*

በፍጥት በማደግ ላይ ካሉ አገራት እንድትሰለፍ አድርጓታል፡፡ ይህም ሊሳካ የቻለው ህዝቡ በንቃት ቁጠባ ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ በመቻላቸው ነው፡፡ በመሆኑም እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ህዝቡ የሚሳተፍባቸው የተለያዩ የልማት መርሀ ግብሮች ያሉ መሆናቸውን ማየት ይቻላል፡፡ አገራችን ከእነዚህ የህዝብ ተሳትፎዎች ብዙ መማርና የጀመረችውን አሳታፊነት አጠናክራ መቀጠል ከቻለች የተሻለ ለውጥ እንደምታስመዘግብ አያጠራጥርም፡፡ ህዝቡንም አሳትፋ ለማደግ የምትችልበት እድል አለ፡፡ ይህን እድል በአግባቡ መጠቀም፣ አገርና ህዝብን ማሳደግና መለወጥ ደግሞ የለውጡ አመራር ሚና ሊሆን ይገባል፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው አምስቱም አገራት የተለያየ የህብረተሰብ ተሳትፎ ተሞክሮን ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ እየሆኑ እንደመጡ የተቀመረው ተሞክሯቸው ያመላክታል፡፡ ህዝብን እያሳተፉ መስራት ለውጤት እንደሚያበቃም አይተናል፡፡ የአገራችን የህዝብ ተሳትፎ ተሞክሮስ ምን ይመስላል?

## *የአገራችን የሕዝብ ተሳትፎ ሁኔታ*

በአገራችን በሕገ-መንግስቱም ሆነ ሕገ-መንግስቱን ተከትሎ በተቀረጹ የልማትና የመልካም አስተዳደር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ ጽንሰ ሀሳብ በጉልሁ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 "ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳባቸውን የመስጠትና የመጠየቅ መብት አላቸው" ይላል፡፡ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 6 ደግሞ "የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የህዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት" ብሎ በግልጽ ይደነግጋል፡፡

ፖሊሲዎቻችንም የህዝቡን ተሳትፎ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ሀምሌ 2001 ዓ.ም የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጉዳዮች ፖሊሲ ካለ ህዝብ ተሳትፎ የኢትዮጵያ ህዳሴ እውን እንደማይሆን በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የህዝቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የከተማችን አስተዳደርም ሆነ በየደረጃው የሚገኙ አካላት ከፍተኛ የሆነ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውም የሚታወቅ ነው፡፡ ህዝቡም ተሳትፎውን ከጊዜ ወደጊዜ እያሳደገ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም በአገራችን የህብረተሰብ ተሳትፎን በስፋት ለማካሄድ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ማለት ነው፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ የህብረተሰቡ ተሳትፎ በአካባቢ ልማት ላይ እያደገ መምጣቱ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህን የመሰሉ የህግ ማዕቀፍ ቢዘጋጁም ጠንካራ የሆነ የህዝብ ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንጻር ብዙ እንደሚቀሩን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በአዲስ አበባ የተጀመሩ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራዎች በከተማ ልማት ረገድ ከአገሪቱ የተሻለ እንደሆነ ቢታወቅም ከጉድለት የነጻ ነው ተብሎ የሚወሰድ ግን አይደለም፡፡ በከተማዋ ውስጥ ያለውን እምቅ የህብረተሰብ አቅምን አሟጥጦ መጠቀም አለመቻል እንደ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል፡፡ ህዝቡ ለአካባቢውና ለከተማዋ ልማት በገንዘቡ፣ በጉልበቱና በእውቀቱ ሳይታክት ለመሳተፍ ዝግጁ ነው፡፡ ይሁን እንጅ አመራሩ በሚፈለገው ልክ ህዝቡን አስተባብሮና አሳትፎ ከመስራት አንጻር በየአመቱ አበረታች ለውጦችን እያስመዘገበ ቢመጣም አሟጥጦ መጠቀም ላይ አሁንም ይቀረዋል፡፡

በመሆኑም አሁን ላይ በከተማችን ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ የህዝቡን ተሳትፎ ለማቀጣጠል ምቹ ሁኔታ ባለበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲን በከተማ ደረጃ ተቋሙን ከተልዕኮ ውጪ ማድረጉ ግርምት የፈጠረባቸውም አሉ፡፡ ህዝቡን በቀጣይ እንዴት ለማሳተፍ ምን እንደታሰበም አጥጋቢ ምላሽ እየተሰጠ አይደለም፡፡ ህዝብና መንግስትን እንደ ድልድይ ሆኖ ሲያገለግል የቆየን ተቋም ማፍረስ ተገቢም አይደለም፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ውሳኔውን መለስ ብሎ በመመልከት የህዝቡን ጥያቄ ሊመልስ ይገባል፡፡




*ሲሶው የአይስላንድ ህዝብ የጦር መሣሪያ የታጠቀ ነው። በአለፉት 12 ዓመታት አንድም በጦር መሣሪያ የሚካሄድ ወንጀል አልተፈፀመም። ዜጎች ጠመንጃቸውን ለአደን ብቻ ይጠቀሙበታል። የአይስላንድ ፖሊስም የጦር መሣሪያ አይታጠቅም። ልዩ የፖሊስ ሃይል ብቻ ቢታጠቅም ጠመንጃውን ከተቆለፈበት ሣጥን አውጥቶ ለመጠቀም የበላይ አለቃ ፍቃድን ይሻል በ2016 ዓመት የፖሊስ ታሪክ ውስጥ ሁለት ሰው ብቻ ነው በፖሊስ መሣሪያ ህይወቱ የአለፈው።*

## *የአዲስ አበባ ህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራ አጭር ታሪክ*

በአዲስ አበባ ህዝቡን በተደራጀ መንገድ በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ማሳተፍ የተጀመረው ከ1987 ዓ.ም ወዲህ እንደሆነ ያገኘናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ። ከመሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት በ1987 ዓ.ም በየአካባቢው ተደማጭነት ያላቸውን ግለሰቦች እንዲያስተባበሩ በመሰየም የአካባቢ ልማት ግብረሃይል ተቋቁሞ የመንገድና የፍሳሽ ማስወገጃ ችግሮችን ለመፍታት ህዝቡ እራሱ በጉልበቱ እየተሳተፈ የአካባቢ ልማት ስራዎች ቢጀመሩም ግብረሀይሉ ጥቂት ስራዎችን ከማከናወን በስተቀር በዘላቂነት ሳይቀጥል ወዲያውኑ ተበትኗል።

በ1989 ዓ.ም የህብረተሰቡን የልማት ተሳትፎ ጥያቄ በላቀ ደረጃ ምላሽ ለመስጠት በማሰብ የአካባቢ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ተቋቁሞ ሥራ ጀመረ። ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ባለሙያዎችን በመቅጠርና በማሽን የተደገፉ ስፋት ያላቸው ሥራዎችን በመስራት በየአካባቢው መልካም የሚባሉ ስራዎችን አከናውኗል። የህዝቡ ተሳትፎ ግብአት በማቅረብ፣ በጉልበት፣ ገንዘብ በማዋጣትና በዕውቀት የነበረ ሲሆን በወቅቱ የህዝቡ ተሳትፎ እስከ 20 በመቶ እንደሚደርስ መረጃዎች ያመላክታሉ። በዚህ ወቅት ስራው እያደገ የመጣ ቢሆንም አሰራሩ ቢሮክራሲ የበዛበት በመሆኑ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም ነበር።

ስራው አንድ ጊዜ ሞቅ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ ሲል ቆይቶ በ2003 ዓ.ም በከተማው ቁልፍ ስራነት ተይዞ ዕቅድ ወጥቶለት በዕቅዱ ላይ ህዝቡ እንዲወያይና እንዲያዳብረው ተደርጎ፣ የአሰራርና አደረጃጀት እንዲሁም የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎችና ሌሎች ሰነዶች ተዘጋጅተው በአዲስ መልኩ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ በተቋም ደረጃ እንዲቋቋም ተደረገ።

ኤጀንሲው ከተመሰረተበት ጊዜም አንስቶ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እየፈታ የመጣና የሀብት አሰባሰቡም ውጤታማ እንደነበር

**"ተሳትፎውን በሚገባ ያረጋገጠ ህብረተሰብ ከመንግስት ብቻ እያንጋጠጠ የሚጠብቅ ሳይሆን የራሱን ድርሻም ለመወጣት ጥረት የሚያደርግ ይሆናል።"**



*በ2010 ዓ.ም የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ይድ {DOD`s} የተሰኘ ከቀደመው ጊዜ ምርት እጅግ ፈጣን የሆነ ሱፐር ኮምፒተር ለመገንባት 1,730 ፕሌይ ስቴሽን 3 መጫዎቻ የተለያዩ አካላትን ወስዷል።*



በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ አንድ ቀጠና አንድ ልማት ለስራ የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ ማዕከል



በቦሌ ክ/ከተማ በህብተረሰብ ተሳትፎ ልማት የተሰራ የኮብልስቶን ንጣፍ መንገድ

ይታወቃል፡፡ በተሳትፎ ደረጃም ህዝቡ ዴሞክራሲያዊ አካሄድን እንዲለማመድ ተቋሙ የማይተካ ሚና ሲወጣ ቆይቷል፡፡ አሁን ላይ በአስተዳደሩ በኩል ፈርሷል የሚል መርዶ እስከሰማን ድረስ ኤጀንሲው ለከተማዋ ነዋሪዎች ያከናወናቸው የልማት ስራዎች ህብረተሰቡን እፎይ ያስባሉና ለቀጣይ ልማት ያነሳሱ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

በከተማችን ውስጥ የምናየውንና እየተጠቀምንበት ያለውን የውስጥ ለውስጥ የኮብል ስቶን መንገድ ጨምሮ የአስፓልት፣ የጠጠርና ገራጋንቲ መንገድ አብዛኛውን የጋራ ማብሰያ፤ መታጠቢያ፤ መጸዳጃ ቤት፣ ረጃጅም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች እንዲሁም የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ማዕከላት በኤጀንሲው አስተባባሪነት በህዝቡ ተሰርተው ለአገልግሎት መብቃታቸው እሙን ነው፡፡

በኤጀንሲው የተሞክሮ ሰነድ ላይ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመላክተው ተቋሙ ባለፉት ዓመታት በተለይም በመጀመሪው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከ2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት መሰብሰቡንና በእያንዳንዷም ዓመት ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ሲሰበሰብ መቆየቱን ያረጋግጣል፡፡ አሁን ላይ ከተማ አስተዳደሩ ኤጀንሲው ፈርሷል ቢልም በአንዳንድ ቀጠናዎች ህዝቡ ገንዘብ ማሰባሰቡን እንደቀጠለ ያነጋገርናቸው የቦሌና የቂርቆስ ክፍለ ከተማና ወረዳ አመራሮች እንዲሁም የልማት ኮሚቴ አባላት አረጋግጠውልናል፡፡ በተሰበሰበው ገንዘብ ከ1 ሺህ 750 ኪ.ሜ በላይ የኮብል ስቶን መንገድ፤ ከ52 ኪ.ሜ በላይ የአስፓልት መንገድ፤ ከ400 ኪ.ሜ የጠጠርና ገራጋንቲ መንገድ፤ ከ250 በላይ የኮሚኒቲ ፖሊስ ማዕከላት፤ በርካታ መጸዳጃ ቤቶች፣ የጎርፍ መውረጃ ቦይ የውስጥ ለውስጥ መብራት፤ እንዲሁም ሰፊ የአረንጓዴ ልማት ስራ ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ የህዝቡን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ከ17 በሚበልጡ ዘርፎች ብዛት ያላቸው የልማት ስራዎች ተሰርተው ለህዝቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በ2010 ዓ.ም ባስጠናው ጥናት ላይ እንደተመላከተው የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራ የአካባቢን ገጽታ በመቀየርና የነዋሪዎችን የቋሚ ንብረት ዋጋ ከፍ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ ህዝቡ የኮብል ስቶን ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ተጨማሪ ስራዎች የአረንጓዴና የጽዳት ስራዎች በህብረተሰብ ተሳትፎ ኤጀንሲ በኩል እንዲሰራለት ፍላጎት እንዳለው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይህን ጥናት መነሻ በማድረግ ኤጀንሲው ስራውን በስፋት ይቀጥላል ተብሎ ሲጠበቅ ነው ጭራሽ መፍረሱን የሰማነው ይላሉ አመራሮቹ፡፡



*ብራዚል ውስጥ ፍርደኛ በማረሚያ ቤት የሚኖረውን ቆይታ ለመቀነስ ከፈለገ የማይንቀሳቀሱ ባለፔዳል ሳይክሎችን መጋለብ አለበት የፔዳሉ እሽክርክሪት የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጫል፡፡*

# ለምን እንደታጠፈ የከተማ አስተዳደሩ ምላሽ

ከላይ የጠቀስናቸውን በርካታ ተግባራት በጠንካራ የህዝብ ተሳትፎ ማከናወን የቻለውና በህብረተሰቡና በመንግስት መካከል ያለውን የልማት ግንኙነት የሚያጸናው ድልድይ ለምን ተሰበረ? በአመት ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት የሚሰበስበው ኤጀንሲ ለምን ታጠፈ? የህዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ተሳትፎ ለማጠናከር ምን አማራጭ ተቀምጧል? እውን ይህ ውሳኔ የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ነው ወይ? ልማትን ለማቀላጠፍ ሲሉ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ከ12 ሺህ የሚበልጡ የልማት ኮሚቴዎች እጣ ፈንታስ ምንድነው? በብዙ ድካምና ልፋት እየተቀጣጠለ የመጣው የተደራጀ የህዝብ ተሳትፎስ በምን አግባብ ይቀጥላል? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች በከተማዋ ነዋሪ ዘንድ መነሳት ከጀመሩ ውለው አድረዋል፡፡

እኛም ተግባራችን ለህዝብ ፈጣን ምላሽ መስጠት ነውና ጥናቱን ወደአጠናው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ጎራ ብለን ነበር፡፡ በቢሮው የማስፈጸም አቅም ግንባታ አማካሪ አቶ ኤፍሬም ሳህሌ የህብረተሰብ ተሳትፎ በባህሪው በአንድ ተቋም ብቻ ሊከወን የማይችል በመሆኑ የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲታጠፍ ተደርጓል ብለውናል፡፡ በዋናነት የታጠፈበትን ምክንያትም በጥልቀት አስረድተውናል፡፡ ተቋሙ ራሱን ችሎ ሁሉንም የአካባቢ የልማት ስራዎች መስራት ባለመቻሉ፣ የስራ መደበላለቅና ከጊዜ ወደ ጊዜ ተግባራቱ እየተቀዛቀዙ መምጣታቸው አበይት ምክንያቶች መሆናቸውንም በቆይታችን አውግተውናል፡፡ ስለሆነም በከተማዋ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራን በእቅዳቸው አካትተው እንዲሰሩ መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መግባቱንም ነግረውናል፡፡ በከተማችን የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ህብረተሰቡን የሚያሳትፉበት አሰራርና አካሄድ አላቸው፡፡ ለአብነት መንገዶች ባለስልጣን መንገድ ሲሰራ ህዝቡን እያሳተፈ ነው፡፡ በአካባቢ ጥበቃ፣ በጽዳት አስተዳደር፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በኮንስትራክሽን፣ በውበትና መናፈሻና በሰላምና ጸጥታም ዙሪያ ተቋማት የልማት ስራዎችን ለመስራት ሲነሱ ህዝቡን የሚያሳትፍ እቅድ አዘጋጅተው ነው፡፡ ስለዚህ ተቋሙ ታጠፈ አልታጠፈ የህብረተሰቡ የልማት እንቅስቃሴን የሚገታ ነገር አይኖርም ብለውናል አማካሪው አቶ ኤፍሬም፡፡

ጥናት በተደረገበት ወቅት ውሱንነቶችን ለመለየት መቻሉንና ኤጀንሲው ቢታጠፍም ስራውና ልማቱ ግን በየተቋማቱ የሚሰራና የሚቆም አለመሆኑንም አረጋግጠውልናል፡፡ ታጥፏል እየተባለ በሚነገርበት በአሁኑ ወቅትም በየቀጠናውና በየመንደሩ በርካታ የልማት ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙና ተቋማቱም ህብረተሰቡን እያሳተፉ ስራውን እያስቀጠሉ በመሆኑ መታጠፉ ትክክለኛና አስተዳደራዊ ወጪን የቀነሰ መሆኑንም አስገንዝበዋል፡፡

መሪው ድርጅት ኢህአዴግም በፕሮግራሙ ላይ እንዳስቀመጠው ህዝቡ በተለያዩ የሙያና የብዙሃን ማህበራት እንዲደራጅ፣ በእነዚህ አደረጃጀቶች አማካይነት ለመብትና ጥቅሙ እንዲታገል ብሎም መንግስት በሚያካሂዳቸው የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ስራዎች በነጻ ፍላጎቱ በሰፊው የሚሳተፍበትን ሁኔታ መፍጠር ዋነኛ አላማው እንደሆነ ያትታል፡፡ ከዚህ አንጻር በአለፉት አመታት ህዝቡ በተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲሳተፍ በማድረግ በርካታ የልማት ስራዎች እንዲሰሩና ለአገልግሎት እንዲበቁ ማድረግ ተችሏል፡፡ በከተማችን ተጨባጭ ሁኔታም የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ በኮንስትራክሽን ቢሮ ስር ተቋቁሞ የህዝብን ተሳትፎ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በማረጋገጥ መንግስትና ህዝብን ድልድይ ሆኖ ሲያገናኝ ቆይቷል፡፡

የኮንስትራክሽን ቢሮ ሃላፊ የነበሩትም ኢንጅነር ዮናስ አያሌውም በእዚህ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡ ኤጀንሲው ከ2003 ዓ.ም በፊት በተቋም ደረጃ እንደማይታወቅና በኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ ስር ሆኖ በአመት እስከ 540 ሚሊየን ብር ከህብረተሰቡ ይሰበስብ እንደነበር ወደ ኋላ መለስ ብለው ያስታውሳሉ፡፡



*በማንም ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከእስር ቤት ለማምለጥ መሞከር በሜክሲኮ በማረሚያ ቤት በህግ አያስቀጣም፡፡ የዚህ ህግ መነሻ "ነጻነትን መሻት የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው" ከሚል ይቀዳል፡፡*

የህረተሰብ ልማት ተሳትፎ ኤጀንሲ በሚል ስያሜ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለትና ሶስት አመት የተሻለ የልማት እንቅስቃሴና ጠንካራ የሃብት አሰባሰብ የነበረው ቢሆንም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን በየአካባቢው የህዝቡ የልማት ጥያቄ እየተመለሰ በመምጣቱ የህብት አሰባሰቡ መቀዛቀዙን ኢንጅነሩ አጫውተውናል፡፡ መንግስት መስራት ያለበትን የልማት ስራዎች በሙሉ ህዝቡ እንዲሰራ በማድረግ ህብረተሰቡ ጫና ውስጥ እንዲገባ መደረጉ ደግሞ ለተግባሩ መቀዛቀዝ ዋነኛው ምክንያት እንደነበረ ኃላፊው ነግረውናል፡፡ ይህ አካሄድ ትክክል እንዳልሆነና በህብረተሰቡና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያላላ መሆኑ ታምኖበት ተቋሙ እንዲታጠፍ መግባባት ላይ መደረሱንም ነግረውናል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ተቋማት የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራን በእቅዳቸው አካትተው ተጠያቂነትን ባሰፈነ መንገድ እንዲሰሩ የሚያስችል መመሪያ ጸድቆ ወደ ስራ የተገባ በመሆኑ ኤጀንሲው ቢታጠፍም የልማት ኮሚቴዎች ከሁሉም ተቋማት ጋር በጋራ በመቀናጀት ተግባሩን እንደሚያስቀጥሉም አረጋግጠውልናል፡፡

በቂርቆስና በቦሌ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የክፍለ ከተማና የወረዳ ኃላፊዎች እንዲሁም የልማት ኮሚቴ አመራሮች ግን ይህንን ሃሳብ ትክክል እንዳልሆነና የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ስራን የትኛውም ተቋም ተክቶ ሊሰራው እንደማይችል ይሞግታሉ፡፡ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ጽህፈት ቤት ሀላፊ አቶ ገብረ ኪሮስ ገብረ እግዚአብሔር በከተማ ደረጃ የተደረገው የተቋማት ሪፎርም ተቀራራቢ ስራና አንድ አይነት ተልዕኮ ያላቸውን ተቋማት  ወደ አንድ ማጠቃለሉ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም ከህብረተሰብ ተሳትፎ አንጻር ግን አስተዳደሩ ወይም ያጠናው አካል ተቋሙን እንዲታጠፍ መወሰኑ ትክክል አይደለም የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ ተቋሙ በአዲሱ የለውጥ አመራር ይበልጥ ተጠናክሮና ራሱን ችሎ ይወጣል ብለው ሲጠብቁ የነበረ በመሆኑ “ታጥፏል” የሚለውን ዜና ሲሰሙ ማዘናቸውንም ነግረውናል፡፡ ኃላፊው በክፍለ ከተማው ከ95 በመቶ በላይ 63 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ ንጣፍና ከ4 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር በላይ የአስፋልት መንገድ፣ የጋራ ማብሰያ፣ መጸዳጃና ሻወር ቤቶች፣ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ማዕከላት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ የመንገድ ላይ መብራትና የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች፣ እንደ ከተማ በተሞክሮነት የሚጠቀሰው የጎተራ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ነፋሻማና አረንጓዴ ስፍራዎች በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ መሆናቸውን ለአብነት በመጥቀስ ተቋማት የኤጀንሲውን ስራ ተክተው ይሰራሉ የሚል እምነት እንደሌላቸውና ተቋሙ መታጠፉም አግባብነት የሌለው መሆኑን በአጽንኦት አስገንዝበዋል፡፡ በክፍለ ከተማው የወረዳ ስምንት ምክትል ስራ አስፈጻሚና የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ጽህፈት ቤት ሀላፊው አቶ ገብረ እግዚአብሄር ዘርዓይም የወረዳቸውን ህዝብ ከ90 በመቶ በላይ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚፈቱት ይህንኑ ሴክተር በመጠቀም መሆኑን አጫውተውናል፡፡ በየአመቱ ከ3 ሚሊየን ብር በላይ እየተሰበሰበ ለልማት እንደሚውልም ነግረውናል፡፡ በተያዘው በጀት አመትም ከ1 ነጥብ 8 ሚሊየን ብር በላይ ሀብት ለማሰባሰብ አቅደው እየሰሩና ህዝቡም እየተረባረበ እንደሚገኝ አውግተውናል፡፡ ስለሆነም ይላሉ አቶ ገብረ እግዚአብሔር ይህንን የህብረተሰብ ችግር በቅርበት የሚፈታን ተቋም ማፍረስ ከመንግስት የሚጠበቅ ውሳኔ ስላልሆነ ሊታሰብበት ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡

የወረዳ ሁለት  የልማት አብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አሚር ነጋሽ ነዋሪውን ያሳተፉና ተጠቃሚ ያደረጉ በርካታ የልማት ስራዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ ጥላ ስር ተጠልለው ሲያከናውኑ መቆየታቸውን ነግረውናል፡፡ ነዋሪው እንደ አይኑ ብሌን የሚጠብቃቸውና የሚንከባከባቸው ለሌሎች አካባቢዎችም በሞዴልነት የሚጠቀሱ የሚዳሰሱና የሚጨበጡ የልማት ስራዎች በአካባቢያቸው መኖራቸውንም አጫውተውናል፡፡ በመሆኑም ተቋሙ መታጠፉና በሌሎች ጽህፈት ቤቶች ስር እንዲጠቃለል መደረጉ አግባብነት የሌለውና የልማት ኮሚቴዎችን ተነሳሽነት የሚጎዳ መሆኑንም አስረድተውናል፡፡ ስለሆነም ይላሉ አቶ ገብረ እግዚያብሔር ይህንን የህዝብን ችግር በቅርበት የሚፈታን ተቋም ማፍረስ ከመንግስት የሚጠበቅ ውሳኔ ስላልሆነ ሊታሰብበት ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡




**ግራ ዘመምና ቀኝ ዘመም የፖለቲካ ፍረጃ የተቀዳው ከፈረንሳይ ምክር ቤት አባላት ነው፡፡ይኸውም ሊብራሎች በስተግራ ኮንሰርቫቲቮቹ ደግሞ በስተቀኝ ረድፍ ይቀመጡ ነበር፡፡**


የቦሌ ክፍለ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ገብሬ ዳኘው የህዝብ ተሳትፎን ተግባራዊ ለማድረግና ነዋሪውን በተደራጀ መልኩ ለልማት ለማነሳሳት ብሎም በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ በጉልበትና በቁሳቁስ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በማድረግ ረገድ የህብረተሰብ ተሳትፎ ሚና ወደር የሌለው መሆኑን ነግረውናል፡፡ በመሆኑም በክፍለ ከተማው በአለፉት አመታት ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ በማድረግ ከስድስት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር በላይ የሚገመት ሀብት መሰብሰቡንም አውስተዋል፡፡ “ተቋሙ በየአመቱ ለክፍለ ከተማው ወጣቶችና ሴቶች የስራ እድል የሚፈጥር ሲሆን በእዚህም በርካቶች ህይወታቸውን እንዲለውጡ ከማስቻሉም በላይ ሃብት እንዲያፈሩም አድርጓቸዋል” ብለውናል አቶ ገብሬ፡፡

ህዝቡ በእኔነት ስሜት በልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፍና ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ እንዲሰራ በመደረጉም ሁሉም አካባቢውን ከጎርፍ የመታደግ፣ ውስጥ ለውስጥ የኮብልስቶን ንጣፍ መንገዶችን፣ መናፈሻዎችንና ሌሎችንም የልማት ስራዎች ማከናወን የቻለበት ሁኔታ መፈጠሩንም አረጋግጠውናል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን አገናኝ ድልድይ መስበር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደመሚያመዝንና መንግስትና ህዝብን እንደሚያራርቅ በቁጭት ገልጸውልናል፡፡ ተቋማትም ሀላፊነት ወስደው የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራን በእቅዳቸው አካትተው ሊሰሩ እንደማይችሉና ልማቱ ወደ ኋላ እንዳይመለስ ስጋት አላቸው፡፡


በክፍለ ከተማው የወረዳ 14 የአብይ ልማት ኮሚቴ ሰብሳቢ ሻለቃ ድሪባ ሆርዶፋ በአምስት ቀጣናዎችና በ30 መንደሮች ከሚኖረው የህብረተሰብ ክፍሎች በስምንት አመት ብቻ በህብረተሰብ ልማት ጽህፈት ቤት አማካኝነት ከ11 ሚሊዮን ብር በላይ ሃብት ተሰብስቦ ለአካባቢ ልማት መዋሉን አስረድተውናል፡፡ ይህ ተቋም ህብረተሰቡ አምኖ የተቀበለው በመሆኑ ቀጣናዎችን ሆነ መንደሮችን ይስተዋልባቸው የነበረውን የልማት ችግር በመቅረፍ ለኑሮ ተስማሚና ምቹ እንዲሆን ማድረግ መቻሉንም አጫውተውናል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የመሰለ የሚጨበጥና የሚዳሰስ የልማት ስራ የሚሰራ ተቋም አጥፎ ሌሎች ጽህፈት ቤቶች ተግባሩን ያከናውኑታል ማለት “ክረምትን ያወጣ ቤት በበጋ ያቃጥሉታል” እንዲሉ የተሰሩ ስራዎችን ወደ ኋላ የሚመልስ በመሆኑ ሊታሰብበት እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተውበታል፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ በስምንት አመት ውስጥ ከህብረተሰቡ በሰበሰበው በቢሊየን የሚቆጠር ሀብት ውብ፣ ለኑሮ ተስማሚና ጽዱ ከተማን ለመፍጠር ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በመሪ ድርጅቱ ኢህአዴግ ፕሮግራም ላይም እንደሰፈረው ህዝቡን በራሱ ጥቅም ዙሪያ ማደራጀት ተገቢነት እንዳለውና ይህንንም ተግባራዊ የሚያደርጉ አሰራሮችን መዘርጋት እንደሚያስፈልግ በጉልህ ተቀምጧል፡፡ ከአፈጻጸሙም መረዳት እንደሚቻለው ህዝቡ በየአካባቢው በተለያየ መልክ በመደራጀት ጥቅሙን ለማስከበር ጥረት አድርጓል፡፡ በእዚህም አመርቂ ሊባሉ የሚችሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ውጤት ከተመዘገበባቸው ተቋማት መካከል ደግሞ አንዱ የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከተማ አስተዳደሩ ኤጀንሲው የሚሰራቸው ተግባራት በማጠፍ ሁሉም ተቋማት እንዲሰሩትና የህብረተሰቡን ጫና በማቃለል የመዲናዋን ልማት ለማፋጠን መመሪያ አውጥቶ በምክር ቤት በማጸደቅ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በየደረጃው የሚገኝ አመራር በሚመራው ተቋም እቅድ ላይ ከላይ የጠቃቀስናቸውን የአመራሮችንና የህብረተሰቡን ስጋት ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤጀንሲውን ዕቅድ አካትቶ ለተፈጻሚነቱ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ አቅጣጫ ተቀምጦ ወደ ስራ ከተገባ ሰነባብቷል፡፡

ስለሆነም ተቋሙ በመታጠፉ ቀደም ሲል ያልነበሩ ችግሮች እንዳይከሰቱና የነበሩ መልካም ተሞክሮና ስኬቶች ይበልጥ እንዲጎለብቱ የለውጡ አመራር ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይብዛም ይነስም በስራው ላይ ይስተዋሉ የነበሩ የሀብት ብክነትም እንዳይቀጥል አመራሩ አሰራሮችንና መመሪያዎችን መፈተሽ አለበት፡፡ በአጠቃላይ በአዲሱ አደረጃጀት ልማቱ የበለጠ ውጤታማ፣ አሳታፊና ስኬታማ ለማድረግ የአደረጃጀቱን ተገቢነት ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡




*በ1989 የሮማንያው ሰምባገነን ኒኮላስ ካውሴስኩ በነጠላ ፊደላት ድርድር ቃላትን የመመስረት ሰንጠረዣዊ ጨዋታን/scrabble/ማንም እንዳይጫወት ሰግዷል፡፡ምክንያቱም ጥቂቶች ብቻ የሚችሉት አሰብዛኛዎቹ ዜጎች ንቃት በላይ ነው በሚል ነው፡፡*




ከእነዚህ አራት ገመዶች ውስጥ ሁለቱ በየራሳቸው ተጠላልፈዋል ሁለቱ ደግሞ አልተጠላለፉም፡፡ በየራሳቸው የተጠላለፉ የትኞቹ ናቸው ያልተጠላለፉትስ? awdelewt@gmail.com



የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች በመንግስታዊው የምርጫ ኮሌጅ አስቀድሞ የይሁንታ ድምፅ የአገኙ ናቸው ጆርጅ ወከር ቡሽ ግን በ2000 ዓ.ም የኮሌጁን የይሁንታ ድምፅ ቢያጡም ፕሬዚዳንትነቱን አሸንፈዋል - ወሳኙ ባለድምፁ ህዝቡ መራጩነዋ!

# የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂው የፖለቲካ ምህዳር




ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከመሪው ድርጅት ጋር ቁጭ ብለው የሚመክሩበት ዕድል ከፍቷል

በስልጣኔ ጫፍ ላይ የደረሱና አስተማማኝ ሰለም የሰፈነባቸው አገራት የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ባለቤቶችም ናቸው፡፡ እነዚህ አገራት በኢኮኖሚውም መስክ ቢሆን ቀጣይነት ያለው እድገትም ማስመዝገብ ከመቻላቸው ባሻገር የተለያዩ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የመፍጠርና ለሌላው አለም የማዳረስ አቅምም ያላቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ ምቹ መደላደል ሆኖ ያገለገላቸው ጠንካራ የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባት መቻላቸው ነው፡፡

የዳበረ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በመገንባታቸው መሪዎቻቸው በተለዋወጡ ቁጥር የሃገራቸውን ከፍታ ወደ ኋላ ሳይሆን ወደ ፊት እንዲያራምዱም አስችሏቸዋል፡፡ በሀገረ አሜሪካ ለረጅም አመታት በተፎካካሪነት የዘለቁትን የሪፐብሊካንና ዴሞክራት ፓርቲዎችን ለአብነት ወስደን ብንመለከት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ስልጣን የመምጣትና ህዝብን የመምራት እድል ያገኙት የዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ዕውን ማድረግ በመቻላቸው መሆኑን ከታሪኮቻቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ሪፐብሊካን ፓርቲ እ.ኤ.አ በ1854 በፀረ ባርነት ንቅናቄ ተሳታፊዎች የተመሰረተ ሲሆን ከ16ኛው የአብርሃም ሊንከን አስተዳደር አንስቶ እስካሁኑ 45ኛው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ጆን ትራምፕ ድረስ ለ19 ጊዜ



*ኤይር ፎርስ ዋን በህግ ዕውቅና የተሰጠው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ልዩ የመጓጓዣ አውሮፕላን ስም አይደለም፡፡ በቃ ፕሬዚዳንቱ የተሳፈሩበት የትኛውም አውሮፕላን የሚጠራበት እንጅ ! ጥያቄው ፕሬዚዳንት በየትኛውም አውሮፕላን ይጓጓዛሉ ወይ ነው? እንዳ!*

ሀገር የመምራት እድል አግኝቷል፡፡

በ1792 እ.ኤ.አ የተመሰረተው ዴሞክራቲክ ፓርቲ በበኩሉ በአለማችን ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ ፓርቲዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ሲሆን ህልውናውን አስጠብቆ በመቆየት የሚስተካከለው ፓርቲ እንደሌለ የታሪክ ድርሳናት ያመላክታሉ፡፡ በዚህም እንደ ቆይታው ከ7ኛው የአሜሪካ ፕሬዜዳንት አንድሪው ጃክሰን አንስቶ እስከ 44ኛው ባራክ ኦባማ ድረስ ከሪፐብሊካን ጋር እየተፈራረቀ ለ14 ጊዜ አሜሪካን የመምራት እድልን አግኝቷል፡፡

የአሜሪካ ፓርቲዎች ከቆሙለት አላማና ከህልውናቸው በላይ በሀገራቸውና በህዝባቸው ዙሪያ አንድ አይነት አቋም የሚያራምዱና በአሜሪካ ሃያልነት የማይደራደሩ ናቸው፡፡ ልዕለ ሃያሏ አሜሪካ በሁለቱ ፓርቲዎች እየተመራች ሀያልነቷን አስጠብቃ የቀጠለች ሲሆን ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት ያላቸው ግንዛቤም ሰፊ በመሆኑ በሀገር ጉዳይ ተግባብተውና ተቻችለው እንዲሰሩ አስችሏቸዋል፡፡

አሜሪካ በእነዚህ ሁለት ታላላቅ ፓርቲዎች እየተመራች ዛሬ ከደረሰችበት የእድገት ማማ ላይ ለመገኘት ከመቻሏም ባሻገር ሌሎች የአውሮፓ የኤስያ እንዲሁም የአፍሪካ ሀገራት ላይ እያሳረፈች ያለችው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ የዳበረ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ውጤት አንዱ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በአህጉረ አፍሪካ የምትገኘው ጋናም ከእንግሊዝ የ35 ዓመታት የቅኝ ግዛት አስተዳደር ነፃ ከወጣችበት ከ1949 ዓ.ም አንስቶ በበለጠ ቦታ የምትሰጠው የመጀመሪያውን መድብለ ፓርቲ ምርጫ ያካሄደችበትን ዕለት ሰኔ 20 ቀን 1984 ዓ.ም ነው፡፡ በአገሪቱ የመጀመሪያ የመድብለ ፓርቲ ብሄራዊ ምርጫ ውድድር በብሄራዊ የምርጫ ቦርድ እውቅና አግኝተው የተወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች 23 ሲሆኑ ከነዚያም ውስጥ በሂደት የጋራ ፖለቲካ መድረኩ ላይ ጎልተው የወጡትና የጋናን የምርጫ ፖለቲካ መቆጣጠር የቻሉት ግን ሁለት ፓርቲዎች መሆናቸውን ያገኘናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

የሊብራል ዴሞክራቲክ ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ ነው የሚባለው ኒው ፓትሪዮቲክ ፓርቲ (NPP) እና የግራ መሀል (Center Left) ርዕዮተ አለም የሚያራምደው የብሄራዊ ዴሞክራቲክ ኮንግረስ (NDP) ጎልተው በመውጣት ለረጅም ጊዜ ጋናን የማስተዳደር እድል አግኝተዋል፡፡ በዚህም ከ1984 ዓ.ም አንስቶ በጋና የተካሄዱትን ብሄራዊ ምርጫዎችን በማሸነፍ ጋናዊያንን እየተፈራረቁ አስተዳድረዋል፡፡ ሁለቱ ፓርቲዎች ለዚህ የበቁት የስልጣን መንበሩን ሲቆጣጠሩ ተፎካካሪዎችን በማዋከብ እያዳከሙ፣ ወይም መሪዎቻቸውን በሰበብ አስባቡ እስር ቤት በማጎር አይደለም፡፡ ይህንን ለማድረግም ቢፈልጉ እንኳ በጠንካራ መሰረት ላይ የተመሰረተው የጋናዊያን የፍትህ ስርዓትና የዴሞክራሲ ተቋማት እድልም ቀዳዳም የሚሰጡ አይደሉም፡፡

በጋናዊያን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ውስጥ ይህንን የመሰለ ተጽዕኖ መፍጠር የቻሉት ፓርቲዎቹ የጠራ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ከፍተኛ የመደራጀትና የማንቀሳቀስ ችሎታ ያላቸው የነቁ አመራር ባለቤት በመሆናቸው ነው፡፡ በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባው የጋናዊያን መድብለ ፓርቲ ስርዓት ጋናን አሁን ለደረሰችበት የተረጋጋ ፖለቲካ ስርዓትና የዳበረ ኢኮኖሚያዊ ባለቤት ከማድረጉም ባሻገር በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታም በአፍሪካ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ከበለጸጉት አገራት የአሜሪካንን ከአፍሪካ ደግሞ የጋናን የዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታንና የመድብለ ፓርቲን ተሞክሮ ለማንሳት የሞከርነው የሃገራችንን አጠቃላይ የፖለቲካ እንቅስቃሴና በአለፉት 28 ዓመታት በመሪው ድርጅት ኢህአዴግ ሲቀነቀን የቆየውን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታን ለመዳሰስ ስለፈለግን ነው፡፡

በ1987 ዓ.ም ፀድቆ ወደ ስራ በገባው የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 88 በፖለቲካ ነክ አላማዎቹ ላይ ማንኛውም ዜጋ በመሰለው የፖለቲካ ዓላማና መስመር መደራጀት እንደሚችልና መንግስትም በአግባቡ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ደንግጓል፡፡

በኢህአዴግ ፕሮግራም ላይም በሃገሪቷ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ መድብለ ፓርቲ ስርዓትን ዕውን ለማድረግ




*በአንዳንድ የአሜሪካ ስቴቶች በትዳር ላይ መሄድ መማገጥ የሚያስቀጣ ቢሆንም የቅጣት ልዩነቱ አጃኢብ ነው፡፡ ሚቺጋን ላይ እስከ እድሜ ልክ እስራት ሲያስቀጣ ሜሪላንድ ላይ ግን በ10 ዶላር ቅጣት መለቀቅም አለ፡፡*

ድርጅቱ መስራት የሚጠበቅበትን ሁሉ እንደሚሰራና በህጋዊ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለስልጣን የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲያብቡ፣ ህጉን ተከትለው ህዝቡን እንዲያደራጁ፣ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹና በፖለቲካ ስራ ላይ በነጻነት እንዲሳተፉ ማድረግን ቁልፍ የቤት ስራው አድርጎ እንደሚንቀሳቀስ ያትታል፡፡

በ1960ዎቹ ማቆጥቆጥ እንደጀመረ የሚነገርለት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩ ዴሞክራሲያዊ ውድድርን ሳይሆን ጉልበት መፈታተንን ስለመረጠ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለአብነትም በኢ.ህ.አ.ፓ፣ በደርግ እና በመ.ኢ.ሶ.ን ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር እየተባለ የረገፈው የኢትዮጵያውያን ውድ ህይወት ዜጎች ከፖለቲካ እንዲርቁ ከማድረጉ በተጨማሪ አምባገነኑ የደርግ ስርዓት ከኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ /ኢ.ሠ.ፓ/ ውጭ ያለ ፓርቲ ለአሳር በማለቱ ሰላማዊውን ውድድር በመቆለፍ ሌላ የትግል ስልት እንዲከፈት የአንበሳውን ድርሻ ተጫውቷል፡፡

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንዲሉ የተለያዩ አስተሳሰቦች እና አይዲዮሎጂዎች መኖር ለአገር የተሻለ አማራጭን ከማቅረብ በተጨማሪ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከልም ሰላማዊ ፉክክር በመፍጠር አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያስችላል፡፡ ነቀፌታን እንጅ መተባበርን ያልለመደው የፖለቲካ ባህላችን ግን ኢህአዴግ ስልጣኑን ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም ድረስ በተፎካካሪነት ሳይሆን በተቃዋሚነት ዘልቋል፡፡

"በውጭው አለም በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለው ግንኙነት በውድድር መንፈስ እንጅ በጠላትነት የሚተያይ አይደለም፡፡ በአገራችን የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ግን የውድድር ሳይሆን በጠላትነት የሚፈራረጁ ነበሩ፡፡" የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ግደይ ደገፉ በ1960ዎቹ ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረው የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴ በመጠላለፍ እና በመፈራረጅ ላይ ተመስርቶ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ ተጠላልፈው የወደቁትን ኢ.ህ.አ.ፓን እና መ.ኢ.ሶ.ንን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለአብነት የሚጠቅሱት ምሁሩ ካለፈው አመት ከለውጡ በኋላ

**"ሁለቱ ፓርቲዎች ለዚህ የበቁት የስልጣን መንበሩን ሲቆጣጠሩ ተፎካካሪዎችን በማዋከብ እያዳከሙ፣ ወይም መሪዎቻቸውን በሰበብ አስባቡ እስር ቤት በማጎር አይደለም፡፡ ይህንን ለማድረግም ቢፈልጉ እንኳ በጠንካራ መሰረት ላይ የተመሰረተው የጋናዊያን የፍትህ ስርዓትና የዴሞክራሲ ተቋማት እድልም ቀዳዳም የሚሰጡ አይደሉም፡፡"**



*በአሜሪካ በሲቪል መብቶች ንቅናቄዎች ታዋቂ አክቲቪስት በርኒ ሳንደርስ የጥቁሮችና የነጮች ትምህርት ቤት መለያየቱን በአደባባይ በመቃወሙ በ1963 ዓ/ም ታስሮ ነበር፡፡ ዛሬ አሜሪካ የዓለም ስደተኞች ሁሉ የገነት በር ልትሆን፡፡*

ግን ኢትዮጵያ መነቃቀፍን ሳይሆን ውድድርን በሚያስቀድመው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ምህዋር ውስጥ እየገባች መሆኑን ነግረውናል፡፡ ይሁን እንጅ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ተቋማዊ አካሄድ ሊይዝ እንደሚገባ እና ለሰላም ተገዥ መሆን እንዳለባቸው ምክራቸውን ይለግሳሉ፡፡

ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት መድብለ ፓርቲ ስርዓትን በኢትዮጵያ በመተግበር ደማቅ ታሪክ ለመፃፍ ቢያስብም በተግባር በእሱም ሆነ በተፎካካሪዎቹ ብዙ ጉድለቶች ስለነበሩ በተደጋጋሚ ራሱን ሲፈትሽ ቆይቷል፡፡ በባለፉት አመታት ቁጥራቸው ከ100 የሚያልፍ ብሔር ተኮር እና የዜግንት ፖለቲካ አራማጆች በአገሪቷ ውስጥ ቢንቀሳቀሱም ኢህአዴግ እንደ አንድ አገርን የማስተዳደር ልምድ ያካበተ አንጋፋ ፓርቲ ለተፎካካሪዎች ተጠናክሮ መውጣት የሚጠበቅበትን ተወጥቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡

በእርግጥ በፊት ከነበሩት ስርዓቶች አንፃር ሲመዘን ኢህአዴግ ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት መጠንሰስ ከ1983 ወደዚህ ጉልህ አሻራ ማሳረፉን ማንም አሌ የማይለው ሀቅ ነው፡፡ በ1997 ምርጫ ላይ ተፈጥሮ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች መነቃቃትም ኢህአዴግ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠረና መድብለ ፓርቲ ስርዓትን እውን ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን ያሳየበት ነበር፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን ኢህአዴግ ፖሊሲ እና ስትራቴጅዎቹን ሲተገብር በአፈፃፀም ላይ የሚያሳያቸውን ጉድለቶች እንደየራሳቸው ፖሊሲ እና ስትራቴጅ ቆጥረው በተለይም በምርጫ ዋዜማ ለህዝብ በማቅረብ አካሄዳቸውን ለትዝብት ሲዳርጉ መቆየታቸውም የቅርብ ጊዜ ትዝብት ነው፡፡ ኢህአዴግ ከህብረተሰቡ የሚቀበላቸውን እና አሉብኝ ብሎ የሚያምናቸውን ችግሮች በማስተጋባት ጉንጭ አልፋ የምርጫ ክርክር በማድረግ በአገራችን የፖለቲካ ዕድገት ላይ አንዳች እሴት ያልጨመሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡

ኢትዮጵያውያንም የምርጫ ሰዓት በደረሰ ቁጥር አንድ ሀሳብ ይመላለስባቸዋል፡፡ እሱም ከኢህአዴግ ውጭ አገር ለመምራት የሚያስችል ቁመና ያለው አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ አለ ወይ? የሚለው መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

በአንድ በኩል መሪው ድርጅት ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሟላ አቅም አጎልብተው ለአገራቸው አሻራቸውን እንዲያኖሩ በመደገፍ በኩል የነበረው ሰፊ ክፍተት እና አለፍ ሲልም ወጣ ያሉ አካሄድ ያላቸውን ከማስተማር ይልቅ በጅራፍ የመሸንቆጡ አባዜ ፖለቲካችን በሁለት እግሩ እንዲቆም አላደረገውም፡፡ በሌላ በኩልም ፓርቲዎች ተፎካካሪነታቸውን እረስተው ሁሉንም ነገር ከመንግስት እና ከመሪው ድርጅት የመጠበቁ ባህል የመድብለ ፓርቲ ስርዓታችን እንዳያብብ አድርጎት ቆይቷል፡፡ በዚህም በአገሪቷ ፓርላማ ላይ የተለያዩ አስተሳሰቦች የሚስተናገዱበት እድል እየጠበበ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ ይህም በራሱ ለመድብለ ፓርቲ ስርዓታችን አለመጠንከር አንዱ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

የተለያዩ አስተሳሰቦች በሚገባው ልክ አለመስተናገዳቸውም ከወጣቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ ጋር ተደምረው ከለውጡ በፊት በየአካባቢው ህዝባዊ ቁጣን እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ድርጅታችን ኢህአዴግም ራሱን ቆም ብሎ በማየት ከለውጡ በፊት ባደረጋቸው የ17 ቀን ውይይቶች መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በግልፅ በማስቀመጥ ህዝባዊ ወገንተኝነቱን አሳይቷል፡፡

የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢህአዴግ እና በመንግስት መሪነት ለ25 ዓመት የቀጠለ ቢሆንም የአስተሳሰብ ብዝሃነት በአግባቡ የሚስተናገድበት ተጨባጭ ሁኔታ እየተዳከመ መምጣቱን ኢህአዴግ በታህሳስ ወሩ የ17 ቀን ግምገማ ማመላከቱ አይዘነጋም፡፡ “ክፍተቶችን በጊዜና በአግባቡ ተገንዝቦ ማስተካከል የሚገባው ድርጅታችን ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ረገድ ያሳየው ዳተኝነት የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱን ችግር እንዲገጥመው አድርጓል፡፡” ያለው የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የዴሞክራሲ ምህዳሩን በማስፋት በኩል ድርጅቱ የሚጠበቅበትን ተወጥቷል ብሎ እንደማያምንም አመላክቷል፡፡

በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ከሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶችና ከህዝቡ ጋር



***የግሪን ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ሲባል ዴንማርክ በወተት አቅራቢ አርሶ አደሮች ላይ ልዩ ታክስ ዘርግታለች፡፡ ከብት አርቢዎች በአንዲት ላም በዓመት የ110 ዶላር ታክስ ይከፍላሉ፡፡***

በመሆን ለመቅረፍ በቁርጠኝነት እንደሚሰራም የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ17 ቀኑ ግምገማ በወሰነው መሰረት ባለፈው አንድ አመት አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ የለውጡ መንፈስም በኢህአዴግ ብቻም ሳይሆን በህዝቡ በተለይም በወጣቱ ተስተጋብቶ ስለነበር የድርጅቱን ተራማጅ ባህሪ የተላበሱ አመራሮች ወደ ፊት የሚወጡበትን እድልም ፈጥሯል፡፡ መጋቢት 23 ቀን 2010 ዓ.ም የኢህአዴግ ሊቀመንበር እና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ቀርበው ቃለ መሀላቸውን ሲፈፅሙ "ከኢህአዴግ ውጪ ያሉ ፓርቲዎችን የምናይበት መነፅር እንደተቃዋሚ ሳይሆን እንደ ተፎካካሪ፣ እንደ ጠላት ሳይሆን እንደ ወንድም አማራጭ ሀሳብ አለኝ ብሎ እንደመጣ ሀገሩን እንደሚወድ የዜጋ ስብስብ ነው፡፡" ሲሉ የነበረውን የተቃዋሚነት የፓለቲካ ባህልን በመጠቆም ወደ ተፎካካሪነት ለመለወጥ የራሳቸው እና የድርጅታቸው ፅኑ እምነት መሆኑን ለሁሉም አብስረዋል፡፡

ፓርቲዎች በፍትሀዊ የመወዳደርያ ሜዳ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ የየራሳቸው የፓለቲካ አስተሳሰብ ቢኖራቸውም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ ሊረባረቡ እንደሚገባና በተለይም አገራዊ ጥቅሞቻችንን ለድርድር ማቅረብ እንደማይገባም ዶክተር አብይ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡


በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው የለውጥ መንፈስ እና የጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አብይ ንግግር በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ብቻም ሳይሆን በውጭ አገር የሚኖሩና ቀደም ሲል በሽብርተኝነት በተፈረጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይም የተስፋ ብርሃን ፈንጥቋል፡፡ "ልብ ካዘነ እንባ አይገድም" ነውና ድርጅታችን ኢህአዴግ እና ሊቀመንበሩ ዶክተር አብይ ለኢትዮጵያውያን ያሳዩትን የተስፋ ብርሀን እውን ለማድረግ ከወራት የዘለለ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡

ከሀገር ውጭ የነበሩ የታጠቁም ያልታጠቁም የፖለቲካ ሀይሎች ወደ ሀገራቸው ገብተዋል፡፡ በሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ ለእስር እና ለእንግልት ተዳርገው የቆዩ በርካታ እስረኞችም ተለቅቀው የፈለጉትን የፖለቲካ አመለካከት እንዲያራምዱ ሲደረግ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው ለውጥ አለምን አስደምሟል፡፡

ከለውጡ በፊት በተወሰነ መልኩ ሻክሮ የነበረው የኢህአዴግ እና የዜጎች ግንኙነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መልካምነት ሊቀየር ችሏል፡፡ በተፎካካሪ ፓርቲነት ሳይሆን በተቃዋሚነት ጎራ ቆመው ኢህአዴግ ያመጣውን እድገት አይኔን ግንባር ያድርገው ሲሉ የነበሩት፣ የኢህአዴግ መልካምነት በጭራሽ የማይታያቸው የነበሩ ኃይሎች ጭምር የኢህአዴግን ለውጥ አለማድነቅ አልተቻላቸውም፡፡ በጋራ ለመስራትም አላመነቱም፡፡ "ፓለቲካ እና ኮረንቲን በሩቁ" ብለው ከቤታቸው ቁጭ ያሉ ዜጎች፣ በተለያዩ እስር ቤቶች የነበሩ የፓለቲካ አመራሮች፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው ወደሚወዷት ሀገራቸው መመለስ ያልቻሉ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና የፖለቲካ ፓርቲዎችም የተለኮሰውን የለውጥ ጉዞ አወድሰው ከለውጡ ጋር ተደመሩ፡፡ ለጎሪጥ ሲተያዩ የነበሩት መሪው ድርጅት ኢህአዴግ እና ተፎካካሪ ፓርቲዎችም በአንድ ማዕድ አብረው የሚቆርሱበት መልካም ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

በጋራ የመስራቱ እና በጋራ የመብላት የኢትዮጵያውያኑ መልካም እሴትም በፖለቲካ ፓርቲዎችም ዘንድ እንዲለመድ በመሪው ድርጅት ኢህአዴግ የተደረገው ሪፎርም አረጋገጠ፡፡ የፓርቲዎች የጥላቻ መንፈስ በደጋፊዎቻቸውም ተጋብቶ ሰውን በሰውነቱ ሳይሆን በፖለቲካ አመለካከቱ የመፈራረጅ መጥፎ ልማድም እየፈዘዘ የተሻለ መተሳሰብ ደምቋል፡፡ አሁን ላይ በፖለቲካ አመለካከቴ ተፅዕኖ ደረሰብኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ዜጋ የለም ማለት ይቻላል፡፡ አንድም የፖለቲካ እስረኛ አለመኖሩም በመሪው ድርጅት ኢህአዴግ እና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል የተሻለ መተማመንና መቀራረብ እንዲፈጠር አስችሏል፡፡ ማዶ ለማዶ ሆነው ዱላ ቀረሽ ስድብ ሲወራወሩ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሁን ላይ ወጉ ደርሷቸው በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብለው መምከር የዘወትር ተግባራቸው ሆኗል፡፡ በመጠላላት ላይ መሰረቱን የጣለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል እንዲለወጥ ኢህአዴግ በዓርአያነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ትናንት ኢህአዴግ በተነን፣ አፈራረሰን ወ.ዘ.ተ የሚሉ ኡኡታዎች ዛሬም እንዳይቀጥሉ ኢህአዴግ



*በ2000 ዓ.ም የዛሬው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ትራምፕ የሪፎርም ፓርቲን ወክለው ለፕሬዚዳንትነት ውድድር ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ እንዲያውም የካሊፎርኒያና ሚቺጋን የማሟሻ ድምፅን አሸንፈው ነበር፡፡ ፕለው ወጡ እንዴ!*

ፓርቲዎች ከተበታተነ ስልፍ ሰብስብ ብለው ጠንካራ ተፎካካሪ እንዲሆኑ በአስተሳሰብም በተግባርም የሚደግፍ ፓርቲ ሆኗል፡፡ በዚህም እነሆ አሁን ላይ በርካታ ፓርቲዎች ወደ ህብረት እየመጡ መሆኑን መታዘብ ይቻላል፡፡

ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለምና፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያላቸው ፓርቲዎች ወደ አንድነት እንዲመጡ ኢህአዴግ ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር ባሻገር ራሱም ከግንባር ወጥቶ ወደ አንድ አገራዊ ፓርቲነት በመሸጋገር ምሳሌ ለመሆን ከሶስት ዓመት በፊት ጀምሮ እንቅስቃሴ መጀመሩን በፖለቲካ ፓርቲዎች የውይይት መድረክ ላይ የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ብናልፍ አንዷለም ገልፀዋል፡፡ የኢህአዴግ የአንድ አገራዊ ፓርቲነት እሳቤ በአስረኛው የድርጅቱ ጉባኤ ላይ ተነስቶ ጥናት ቀርቦ ወደ ውሳኔ እንዲገባ ስምምነት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ቢሆንም በ11ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ሂደቱ አዝጋሚ እንደሆነና በፍጥነት ወደ ተግባር እንዲገባ መመላከቱን ሀላፊው ያስረዳሉ፡፡

የኢህአዴግ ወደ አንድ አገራዊ ፓርቲነት መምጣት በተለይም አጋር ፓርቲዎች በማዕከላዊ መንግስት ውስጥ ያላቸውን የውሳኔ ሰጭነት እንደሚያጎላው ዶክተር አብይ በተደጋጋሚ ጊዜ ሲናገሩ ይስተዋላል፡፡ ጊዜ የሚሰጠው እንዳልሆነም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ ሲገልፁ "ከጥቂት ወራት በኃላ ሶዴፓ፣ የአፋር፣ የቤኒሻንጉል፣ የኦሮሞ፣ የአማራ የሚባል ፓርቲ አይኖርም፡፡ አንድ አገራዊ ፓርቲ በመፍጠር ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል የሚነጋገርበት፣ ድምጹ የሚሰማበት፣ የሚወስንበት ስርዓት ለመፍጠር ለውጡ በፍጥነት እየተጓዘ ይገኛል፡፡" ማለታቸው ይታወሳል፡፡

በፓርቲዎች የውይይት መድረክ የድርጅታችን ሊቀመንበር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድም እየተገኙ ለፓርቲዎች መቀራረብ ጉልህ አስተዋፅዖ እያደረጉ ሲሆን በአንደኛው የውይይት መድረክ አሁን ላይ በአገሪቱ ለሚንቀሳቀሱ 108 የፖለቲካ ፓርቲዎች መንግስት ቢሮ እና መሰል ቁሳቁስ ማዳረስ አቅሙ ስለማይፈቅድ የሃሳብ ልዩነት ከሌላቸው ሶስት ወይም አራት ጠንካራ ፓርቲ ለመሆን ጥረት ቢያደርጉ እንደሚበጅ በማስገንዘባቸው ተቀራራቢ አስተሳሰብ ያላቸው ፓርቲዎችም ውህደታቸውን እያፋጠኑ ይገኛሉ፡፡


ከለውጡ በኋላ ኢህአዴግ ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታው የዴሞክራሲ ተቋማትን የማጠናከሩን ስራ በትኩረት አከናውኗል፡፡ ለአብነትም ምርጫ ቦርድ ፍፁም ገለልተኛ እንዲሆን በመፈለግ በተቋሙ ላይ ተስፋ ሰጪ ሪፎርም ተደርጓል፡፡ አሁን ላይ ስራ እና አሰራርን መፈተሽ እንጅ ፓርቲዎች ድክመቶቻቸውን በመሪው ድርጅት ላይ የሚያላክኩበት ፋሽን አልፏል፡፡ ቀደም ሲል ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቅሬታ ሲያቀርቡበት የቆየውና ለገዥው ፓርቲ ያደላል የሚለው ትችት ከአሁን በኋላ ሚዛን የሚደፋ አይሆንም፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው የተሾሙት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በአብዛኛው ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተቀባይነት ከማግኘታቸው በተጨማሪ ኢህአዴግን የሚቃወሙ እንደነበሩ ይታወሳል፡፡

ኢህአዴግ ምንም እንኳን በ2007 ዓ.ም በተደረገው አገራዊ ምርጫ አገሪቷን የማስተዳደሩን ሀላፊነት እና ይሁንታ ያገኘ ቢሆንም ድርጅቱ የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዲስተናገዱ ባለው ቁርጠኝነት አሁን ላይ በተለያዩ ተቋማት የኢህአዴግ አባል ያልሆኑ ግለሰቦችን ጭምር የተለያዩ ተቋማትን እንዲመሩ እያደረገ ይገኛል፡፡ ለአብነትም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን በቦርድ አመራርነት እና አባልነት እንዲመሩ የተደረጉ ግለሰቦች ከተፎካካሪ ፓርቲዎችም መኖራቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የአስተዳደራዊ ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ፣ብሄራዊ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን እና መሰል ከለውጡ በኋላ በተቋቋሙ ተቋማት የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዲስተናገዱ መሪው ድርጅት ብርቱ ጥረት አድርጓል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ በሆኑት በወ/ሮ መአዛ አሸናፊ እንዲመራ ከመደረጉም በላይ ተቋሙ ገለልተኛ እንዲሆን እየተሰሩ ያሉ ተግባራት አበረታች ናቸው፡፡

በሌሎችም መንግስታዊ ተቋማት የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዲወከሉ ወይም እንዲስተናገዱ መሪው ድርጅት ኢህአዴግ በሆደ ሰፊነት እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃወች የፖለቲካ ምህዳሩንም የሚያሰፉ ናቸው፡፡



*የሜክሲኮ መንግስት ከ1957 ዓ.ም አንስቶ ለዓሳዎችን ግብር አታስከፍልም፡፡ በምትኩ ከእያንዳንዱ ሰአል ሽያጭ እንደበገአድራጎት ለመንግስት ይሰጣሉ፡፡ አልሽሹም ዘወር አሉ መሆኑ ኮ ነው፡፡*

ከለውጡ በኋላ ኢህአዴግ በተጠናከረ መልኩ እየወሰዳቸው የሚገኙ እነዚህና መሰል እርምጃዎች በ17 ቀኑ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ግምገማም "ምሁራንና የሲቪክ ማህበረሰቦች ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የዴሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት ተገቢ ሚናቸውን የሚጫወቱበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ኢህአዴግ በትኩረት ይሰራል።" የሚል ውሳኔ ተደርሶባቸው የነበሩ ጉዳዮች መሆናቸው አይዘነጋም።

ከ23 የፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጣው ቡድን ለአገር የሚበጅ የፓርቲ አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን ልምድ ቀስሞ እንዲመጣ መደረጉም መሪው ድርጅት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ሰላማዊ ውድድር ለማድረግ እና አብሮ ለመስራት መዘጋጀቱን አመላካች ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነትና በተናጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች የሚገዛ የአሰራር ስርዓትና የቃል ኪዳን ሰነድ ረቂቅ በማዘጋጀትም ፓርቲዎችን በጠረጴዛ ዙሪያ የማወያየት ተግባር እያከናወነ ይገኛል።

የፖለቲካ ምህዳሩን ከተቃዋሚነት አመለካከት ወደ ተፎካካሪ እሳቤ ለመቀየር በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል እየተደረገ ያለው ውይይትም የፖለቲካ ምህዳሩን እንደሚያሰፋው ኢትዮጵያውያን ሰፊ ተስፋ ሰንቀውበታል። ይህ የተፎካካሪ ፓርቲዎች የጋራ ውይይት በሁለት ምዕራፍ የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ፓርቲዎች የጋራ መቀራረብ እንዲኖራቸው ማስቻልን ዓላማ ያደረገ ነው። ለዚህም የአገሪቷ አንገብጋቢ አጀንዳዎች ላይ ጥናታዊ ፅሁፎች እየቀረቡ ወይይት እየተደረገባቸው ይገኛል። ተቀራራቢ የጋራ አቋም በመያዝም በቀጣይ በጋራ በሚሰሯቸው ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እየያዙ መጥተዋል። የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ብናልፍ አንዱአለም እንዳሉትም "በሃሳብ መለያየት ለአገር በጋራ መስራትን አይከለክልም" የሚለው እምነት እንዲጎለብት የመጀመሪያው ምዕራፍ ወሳኝ ነው።

ሁለተኛው እና ቀጣዩ ምዕራፍ ደግሞ ፓርቲዎች በጋራ በመረጧቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ራሳቸውን ለህዝብ የሚያስተዋውቁበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ፓርቲዎች እንደ ምርጫ ክርክር የየራሳቸውን አቋም ለህዝቡ ግልፅ በማድረግ ከህዝቡ ጋር የበለጠ እንዲተዋወቁ የሚያስችላቸው ይሆናል።

በፓርቲዎች መካከል እየተደረጉ ያሉት ውይይቶች በአገሪቱ የተጀመረው ለውጥ ዳር እንዲደርስ እና የዴሞክራሲ ምህዳሩ እንዲሰፋ የጎላ ሚና እንዳላቸው አቶ ብናልፍ ያስረዳሉ።

የፓርቲዎችን ውይይት እና በሂደትም ወደ ውህደት ማምራት አሁን ላይ ከሞላ ጎደል የሚነቅፍ ፖለቲከኛ የለም ማለት ይቻላል። በየአካባቢው እየተፈጠሩ ላሉ ግጭቶች መቀረፍ ውህደቱ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ምሁራኑና የፖለቲካ አመራሩ እየገለጹ ይገኛል። ውይይቶችም ፍሬያማ እንዲሆኑ ፓርቲዎች የመሰላቸውን ሀሳብ እየሰነዘሩ እንዳሉም መገንዘብ ይቻላል።

ፓርቲዎች በሀሳብ ደረጃ መዋሀድ እንዳለባቸው ቢያምኑም ወደ ተግባር የቀየሩት ግን ውሱን ናቸው። የመላ ኢትዮጵያ ድርጅት (መኢአድ)፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ (ኢብአፓ)፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት (ኢዴህ) የአፋር ህዝቦች ፍትህዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የአፋር ህዝቦች ነፃነት ፓርቲ፣ የኦሮሞ ህዝቦች ፍትህዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ውህደት ከፈፀሙት ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። የኢትዮጵያ ዜጎች ማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ን የመሰረቱት ስምንቱ ፓርቲዎችም ውህደት መፍጠራቸው ይታወቃል።

የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ኢህአዴግ ወደአንድ ፓርቲነት ከመምጣቱ አስቀድሞ ቀደም ሲል ተቃዋሚ ከነበሩ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ስምምነትን በኦዴፓና በአዴፓ ብሄራዊ ድርጅቶች በኩል ጅምር እንቅስቃሴ አሳይቷል። የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የኢህአዴግ ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ መለስ ዓለሙ ሰብሰብ ብሎ ከመታገል አኳያም ኢህአዴግ በሩን ክፍት በማድረግ ተመሳሳይ ዓላማና ፕሮግራም ካላቸው ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ይህንንም ለማድረግ የሚያስገድደው የተራማጅነቱ ባህሪና የፖለቲካ አስተሳሰቡ ከህዝቡ



*የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ኬንያን ከጎበኙ በኋላ በስማቸው የሚጠራ ቢራ ተጠምቆ የኬንያውያንን ጉሮሮ አርሷል። በነገራችን ላይ ፕሬዚዳንቱ ራሳቸው እንደ ለስላሳ መጠጦች አነቃቂ ግን መጠነኛ አልኮል የለሰው አልፎ አልፎ ከመጎንጨት ያለፈ ጠጪ አይደሉም።*

የአስተሳሰብ እድገት ጋር አብሮ የሚጓዝ በመሆኑ ነው ይላሉ።

ኢህአዴግ በአገሪቷ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ቁርጠኛ ከሆኑ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆኑን በተለያየ መድረኮች እየገለጸ ይገኛል። ይህ ሲባል ግን በመስመር ከማይመስሉት ጋር ይዋሀዳል ማለት አይደለም። የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ሀላፊ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ "ኢህአዴግ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ስለሰላም አብሮ ለመስራት፣ ለዴሞክራስ ስርዓት ግንባታ፣ ለፖለቲካ ባህላችን መዳበር፣ ለአገር ብልጽግናና በመሳሰሉት አገራዊ ጉዳዮች ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ተደምሮ ይሰራል። ነገር ግን ከአፍራሽ አካላትና ከጸረ ሰላም ሀይሎች ጋር አይደመርም።" በማለት አብራርተዋል።


ኢህአዴግ ለውጡን ዳር ለማድረስ የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት የተለያዩ አበረታች እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። በተለይም የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር አብሮ ለመስራት ቁርጠኝነቱን እያሳየ መጥቷል። ድርጅቱ እኔ ብቻ ሳይል ተፎካካሪዎችም ለሀገር ግንባታውና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈን የጎላ ድርሻ እንደሚያበረክቱ በማሰብ ውጭ ሀገር ድረስ ፓርቲዎችን ይዞ በመሄድ የሌሎች ሀገራትን ልምድ እንዲቀስሙ አድርጓል። በዚህም ፓርቲዎች በተለያዩ ሚዲያዎች እና የህዝብ መድረኮች በነፃ ሀሳባቸውን የሚያሰርፁበት ዕድል ተፈጥሯል። አደረጃጀቶቻቸውን ለማጠናከርም ህዋሳትንና ሌሎች አደረጃጀቶችን እየፈጠሩ ነው። የአባል ቁጥራቸውን ለመጨመርም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል።

ይሁን እንጅ አንዳንድ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በቃል ኪዳን ሰነዱ ላይ የፈረሙትን ወደ ጎን በመተው ከሀገርና ከህዝብ ጥቅም የራሳቸው በማስቀደም ለብጥብጥና ለሰላም እጦት ምክንያት መሆናቸው ኢትዮጵያዊያንን አሳስቧል። እንደዚህ አይነት አካሄድ ለውጡ ያስገኘውንና በጅምር ያለውን የፖለቲካ ውድድር እንዳያደናቅፈው መላ ሊበጅለት እንደሚገባ ብዙዎች እያሳሰቡ ነው። አሁን ላይ ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ጫፍ፣ ከምዕራብ ጫፍ እስከ ምስራቅ ጫፍ የተለያዩ አለመረጋጋቶችንና ግጭቶችን በመፍጠር ለውጡ ያስገኘላቸውን ነፃነት በመጠቀም በዜጎች ላይ ስጋትን ጨምሮ የተለያዩ ጫናዎችን እያሳረፉ ይገኛሉ። በተለይም የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት "አዛኝ ቅቤ አንጓች" በመሆን ህብረተሰቡን ያለሁህ እኔ ብቻ ነኝ በማለት እንደ ጅራፍ እራሳቸው ገርፈው እራሳቸው ሲጮሁ ማየት የተለመደ ሆኗል።

ይዋል ይደር እንጅ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በተለያየ መልኩ አፍራሽ ተግባራትን የሚያከናውኑ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ህብረተሰቡ አበጥሮ ማውጣቱ ባይቀርም ማንኛውም ዜጋ ለውጡ ያመጣለትን ነፃነት መጠቀም ስላለበት ህግን በሚተላለፉ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ የህግ የበላይነቱን የማረጋገጡን ጉዳይ መንግስት ችላ ሊለው አይገባም።

አሁን ላይም እንደ አዲስ የሚፈጠሩ ፓርቲዎች መኖራቸው ሳይዘነጋ የፓርቲዎች ቁጥር እጅግ በመብዛቱ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታችን እና ለመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ መጎልበት ውህደቱም በተሻለ ፍጥነት መደረግ ስላለበት ኢህአዴግ የጀመረውን አበረታች እንቅስቃሴም አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ውህደቱም ብቻ ሳይሆን በአገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ለመያዝም የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድርና ውይይት ሰፊ ጊዜ እየወሰደ በመሆኑ ሁሉም ፖለቲከኞች ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት ሰጥተው በመንቀሳቀስ የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂውን የፖለቲካ ምህዳር ይበልጥ እንዲሰፋ ርብርብ ማድረግ አለባቸው።



*በ1983 ዓ.ም በአሜሪካ ህገ መንግስት ላይ ከቀረቡት ማሻሻያዎች አንዱ ዘዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የሚለው እንዲቀየር ነበር-ዘዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አርዝ በሚል፡፡ ተቀባይነት አጣ እንጅ፡፡*



*የ2008ቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ የምርጫ ውድድርን ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች ሁለቱም ተወዳዳሪዎች ኦባማም ሆኑ ኬያን የተወለዱት ከአሜሪካን ግዛት ዉጪ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአሜሪካ ታሪክ የመጀመሪያዎቹ አድርጓቸዋል፡፡*

# ዓለማዊ፣ አከባቢያዊና አገራዊ ሁኔታችን

በፀጋዬ በየነ

የእስራኤል እና ፍልስጥዔም መቆሳሰል ዓይነት ዓለማችን የለመደችው ሌላ ዓይነተኛ ትዕይንት የሃያላኑ አገራት ገመድ መጓተት ነው፡፡ ረቺና ተረቺ የሌለው፣ ግን ደግሞ ለአፍታም ቢሆን ፋታ የለሽ መጓተት፣ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ሩሲያ..... አዙሪቶች!

እ.አ.አ.ከ 1980ዎቹ ጀምሮ በአለም ደረጃ ሃያልነቱንና ተቆጣጣሪነቱን እያሳየ የቆየው አሜሪካ መራሹ ኒዮሊበራሊዝም ዓለምን ባለአንድ ዋልታ አድርጓት ከርሟል፡፡ አገራት ወደውም ይሁን ተገድደው ኒዮሊበራሊዝም ብቸኛው አማራጭ እንደሆነና እሱን እንዲከተሉ ጫናና ርብርብ ሲደረግባቸው መቆየቱ ይታወቃል፡፡

አሁን ያለው የአለማችንን ሁኔታ ስናጤን የኒዮ ሊበራል ሃይሉ ጫና በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም ቀደም ሲል ከነበረበት በመጠኑም ቢሆን የወረደ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የራሳቸውን ቅያስ የሚከተሉ አገራት እየተበራከቱ መምጣታቸው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ወደ ልዕለ ሃያልነት እየተሸጋገሩ ከሚገኙ አገራት ከፊት የምትታይ ቻይና ስትሆን ከአሜሪካ በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀስ ግዙፍ፣ ፈጣን፣ ያለማቋረጥ የሚያድግ ኢኮኖሚ እመቤት ሆናለች፡፡ ይህንን ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚመጥን ወታደራዊ አቅምም እየገነባች ነው፡፡ የምዕራባዊያኑ መገናኛ ብዙሃን ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ‹‹ቁመህ ጠብቀኝ ጠመንጃ የተሸከሙ ሚሊዮን ሚሊሻዎች ስብስብ!›› ሲሉ የሚያብጠለጥሉት የቻይና ጦርሃይል አይደለም አሁን የአለው፤ ከየትኛውም ልዕለ ሃያል ጋር መሳ ለመሳ የሚታይ እንጂ፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም በዓለም ያላትን ቦታ ለማሻሻል ቻይና የራስዋን ተፅእኖ ማሳደር ጀምራለች፡፡

አሜሪካ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ስጋት አድሮባታል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የአሁኑ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ በቻይና እና በአጋሮቿ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በርከት ያሉ የኤስያ አገሮችም ቀልጣፋ ኢኮኖሚያዊ እድገት በማረጋገጥ ወደ አደጉ አገራት ሰልፍ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ እንደ ሕንድ፣ ብራዚል የመሳሰሉ አገራትም ግዙፍ ሊባል የሚችል ኢኮኖሚያዊ አቅም በመገንባት ላይ ናቸው፡፡ ይህ አቅም ደግሞ በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ጨዋታ ላይ ተፅዕኖ ለማሳረፍና ደረጃቸውን ለማሻሻል እየተረባረቡ ያሉበት ዓለማዊ ሁኔታን አስከትሏል፡፡

በሌላ በኩልም በተለምዶ የምዕራባውያን ሃይሎች ተብለው የሚጠሩ የአውሮፓ አገራት እና አሜሪካን የያዘው ክንፍ ከፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ ወደ ስልጣን መምጣት በኋላ አሜሪካ እየተከተለችው ባለችው የመከላከል (protectionist) ፖሊሲ ቀደም ሲል ለረዥም ግዜያት የቆየውን ስትራቴጂካዊ ወዳጅነታቸውን ወደ አደጋ የሚያስገባ መሳሳብ መፈጠሩን እናያለን፣ በሚወስዷቸውም አቋሞች ግልፅ ልዩነታቸውን እንመለከታለን፡፡ በነዚህ አገራት እየታየ ያለው የአቋም ልዩነት ምን ያስከትላል? የሚለውን ወደ ፊት የምናየው ቢሆንም ይህ ወዳጅነት በውስጡ የመሰነጣጠቅ ምልክቶች እየታዩበት ነው፡፡

የአውሮፓ አገራት ትስስራቸውን በማጎልበት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የጀመሩት ጉዞም የተለያዩ እንቅፋቶች እያጋጠሙት ይገኛል፡፡ በተለይም የዩናይትድ ኪንግደም ከአውሮፓ ህብረት ለመውጣት ህዝበ ውሳኔ ማካሄዷን ተከትሎ እስከ አሁን በሂደቱ ያሉ እንቅፋቶች በቀላሉ የሚታለፉ አልሆኑም፡፡ ውሳኔው በክፍለ አህጉሩ ከፍተኛ ቀውስ የፈጠረ ከመሆኑም በላይ የአውሮፓ ህብረት እንዳይጠናከር ከጥንቱ ከጠዋቱ ሲቃወሙ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በዚሁ አጋጣሚ በየሃገራቸው ተሰሚነታቸው ከፍ እያለ በመምጣቱ

**“ጠቅለል ብሎ ሲታይ ዓለማችን ከአሃዳዊ ሃያል ተላቅቃ ወደ መድብለ ሃያላን፣ ከአንድ ዋልታ ወደ ባለብዙ ዋልታ ሽግግር ላይ ነች፡፡”**

የአገራቱ የህብረት ጉዞ ትላልቅ መሰናክሎችን እንዲያልፍ ተገድዷል፡፡

ጠቅለል ብሎ ሲታይ ዓለማችን ከአሃዳዊ ሃያል ተላቅቃ ወደ መድብለ ሃያላን፣ ከአንድ ዋልታ ወደ ባለብዙ ዋልታ ሽግግር ላይ ነች፡፡ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የትኞቹ አገሮች ጠንካራ ሁነው ሊወጡ እንደ ሚችሉ የተለያዩ ግምቶች ቢኖሩም የሽግግሩ ሁኔታ ከጅምር አልፎ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻል አይደለም፡፡ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው ግን ቀደም ሲል በአንድ ልዕለ ሃያል አገር ትመራ የነበረች አለም እየተቀየረች መሆኗን ነው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው አሁን በአለማችን እየታየ ያለው ሽግግር እንደኛ የመሳሰሉ ከድህነት ለመውጣት እየታገሉ ላሉ ህዝቦች በአንድ በኩል ከፍተኛ እድል የሚፈጥር ሲሆን ፣በሌላ በኩል ደግሞ ለተጨማሪ ፈተናዎች እየተዳረጉ እንዳሉ ማየት ይቻላል፡፡

የዓለማችን ልዕለ ሃያል ለመሆን እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሃይሎች በዓለም ዙሪያ ያላቸውን ደረጃ ለማሻሻል በሚወዳደሩበት ጊዜ ከድህነት ለመውጣት በመታገል ላይ ያሉ አገሮች ይደርስባቸው የነበረው ጫና እንዲቀንሥና የየአገሮቻቸውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የራሳቸውን ፖሊሲ ለማውጣትና የህዝቦቻቸውን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል እድል ሊያሥገኝላቸው ይችላል፡፡ ከኛ አገር ነባራዊ ሁኔታም የጀመርነውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ጉዞ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያስችለን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንድንፈጥር እድል የሚሰጠን ይሆናል፡፡ በርከት ያሉ የኤዥያ አገሮችም ቀደም ሲል ከነበራቸው መካከለኛ የእድገት ደረጃ ወደ ላቀ እየተሸጋገሩ በመሆናቸው ከፍተኛውን የሰው ጉልበት ከሚጠቀሙ የተራቀቀው ቴክኖሎጂ ወደ መጠቀም እየተሸጋገሩ ስለሆኑ በነዚሁ አገሮች የነበሩ በርከት ያሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ረከስ ያለ የሰው ጉልበት ወደ ሚያገኙባቸው አካባቢዎች ተነቅለው የሚወጡበት ሁኔታ አለ፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም ይህንን ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ከሌሎች ተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ከሚገኙ አገሮች በተሻለ ሁኔታ ተመራጭ የመሆን እድል እንዳላት የዘርፉ ሊቃውንት ይገልፃሉ፡፡

አሁን የተፈጠረውን እድል የመጠቀምና ያለመጠቀም ሁኔታ የሚወሰነው ግን ከላይ እስከ ታች ያለው አመራራችን የዚህች አገር ሰላምና ፀጥታ፣ ደህንነት ከመላው የአገሪቱ ህዝቦች ጋር ተቀናጅቶ ማረጋገጥ ሲችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በንቃትና በብስለት የሚረዳና እድሉን በሥፋት ለመጠቀም የሚታትር አመራርና ህዝብ ወሳኝ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ይኸው በልዕለ ሃያላን አገሮች እየተደረገ ያለው የሽግግር ሁኔታ እድል ብቻ ሳይሆን ፈተናዎችም ያሉበት ነው፡፡ በአገራቱ መካከል ጠንካራ ፉክክርና ውድድር የሚደረግበት ሂደት በመሆኑ አንዳንዶቹ ሃያላን የራሳቸውን ጥቅም የሚቃረን እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን በሚረዱበት ጉዳይ ላይ የማያወላዳ እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታ በመኖሩ የዚህ ሰለባ ላለመሆን መጠንቀቅ የግድ የሚልበት ዓለም ላይ እንገኛለን፡፡ በዓለም ዙሪያ ተቀናቃኝ ሃይል እንዳይፈጠር፣ የኒዮሊበራሊዝም ሃይሉን የሚፃረሩ ትናንሽ አካባቢያዊ ሃይሎች እንዳይፈጠሩ ሾተላይ በመሆን ማስጨንገፉን ጨምሮ ከተፈጠሩም በለጋነታቸው ለማክሰም የሚደረግ እንቅስቃሴ ሠፊ ነው፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ ያሥገባ ብቁ፣ የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት ያለው አመራር ከላይ እሥከ ታች መፍጠር የግድ ይላል፡፡

በአሁኑ ግዜ አሀዳዊ ልዕለ ሀያል ወደ ባለብዙ ልዕለ ሃያላን ዋልታዎች ሽግግር ላይ እንገኛለን ስንል ኒዮሊበራሊዝም የሚያበቃበት የተለያዩ አለማዊ ሁኔታዎች ተከስቷል ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አሁንም ቢሆን ልእልናውን አረጋግጦ የሚገኘውም የኒዮሊበራል አስተሳሰብ ነው፡፡ ያም ሆኖ ካገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር መሰረት አድርገው የወጡ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች አሁንም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ ላይ ወሳኝ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አሁን ያለንበት አለማዊ ሁኔታ ሌሎች ትላልቅ ፈተናዎች ፊት ለፊታችን እንዲደቀኑ አድርጓል፡፡ አገሮች በተለይም ደግሞ እንደ አሜሪካ የመሳሰሉ በጣም ያደጉ አገሮች የህዝበኝነትና ፅንፈኛ የቀኝ አስተሳሰብ በግልፅ እያራገቡና እያናፈሱ ህዝቡን ወደ አልሆነ አቅጣጫ

"የዘር፣ የፆታ፣ የሀይማኖት ወዘተ... ልዩነቶች የሚሰብኩበት፣ ስደተኛ ጠል አስተሳሰቦች እየጎለበቱ የሚሄዱበት፣ ጉርብትና በግንብ የሚታገድበት፣ የፋሽስቶች ዘረኛ መፈክሮችና ቀስቃሽ ንግግሮች አሳፋሪ እና አስፈሪነታቸው ተዘንግቶ በጭብጨባና ሆታ የሚታጀቡበት እንደ አቋም የሚራመዱበት ሁኔታ በስፋት እየታየ ነው፡፡"

እያነሳሱ ወደ ስልጣን የሚመጡበት ሁኔታ በስፋት እየታየ ነው። ግልፅ በሆነ መንገድ የዘር፣ የፆታ፣ የሀይማኖት ወዘተ... ልዩነቶች የሚሰብኩበት፣ ስደተኛ ጠል አስተሳሰቦች እየጎለበቱ የሚሄዱበት፣ ጉርብትና በግንብ የሚታገድበት፣ የፋሽስቶች ዘረኛ መፈክሮችና ቀስቃሽ ንግግሮች አሳፋሪ እና አስፈሪነታቸው ተዘንግቶ በጭብጨባና ሆታ የሚታጀቡበት እንደ አቋም የሚራመዱበት ሁኔታ በስፋት እየታየ ነው።

አንዳንድ አገሮች በሚያራምዱት መጥፎ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ምክንያት ተነጥለው ጥጋቸውን ይዘው የቆዩ የቀኝ ብሄርተኛ ፅንፈኛ ፓርቲዎች ድምፅ አግኝተው ወደ ፓርላማ ገብተዋል። ይህ እየሆነ ያለው ለመቶዎች አመታት ዴሞክራሲን መገንባታቸው፣ የዴሞክራሲ ማለፊያ እሴቶችን ኑሮዋቸው ስለማድረጋቸው በሚነገርላቸው አገራት መሆኑ ደግሞ እንቆቅልሽ ነው። ይህ ደግሞ የቀኝ ክንፍ ፖለቲካ አስተሳሰብ የደረሰበት ደረጃም በጣም የሚያሳስብ እንዲሆን አድርጎታል።

ዓለማችን ካጋጠማት የተፈጥሮ መዛባት ለመውጣትና የከፋ አደጋን መከላከል የሚያስችል ስምምነት ላይ ከብዙ ድካምና ውጣ ውረድ በኋላ መደረሱ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።

ሆኖም ግን አለምን በአሳዘነና ኃላፊነት በጎደለው መንፈስ ስምምነቱ በነዚሁ የተፈጥሮ መዛባት እንዲከሰት የአንበሳውን ድርሻ በወሰዱ ሃያላን አገሮች ሲጣስ እየተመለከትን ነው። ትላልቅ የኢኮኖሚ አቅም በገነቡ አገሮች መካከል የተከሰተው የንግድ ውጥረትም ሌላ የስጋት ምንጭ እየሆነ ነው። በአሜሪካ ተነሳሽነት በገቢ ሸቀጦች ዙሪያ ላይ ታሪፍ የመጫን እንቅስቃሴ ሌሎች አገሮችም ተመሳሳይ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል እርምጃ ለመውሰድ በመገደዳቸው ዓለም ዓቀፍ ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል እንዳይከሰት ስጋቱ አይሏል።

በአጠቃላይ በየጊዜው አዳዲስና የሰውልጅን ወደ ከፋ አደጋ ሊያስገቡ የሚችሉ ዝንባሌዎች እየታዩ ይገኛሉ። የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለመደው ስርዓትና አካሄድ ችግሮቻቸው ሊፈታላቸው ባለመቻሉ ተማርረው ፅንፈኛ ሃሳብ የሚያራምዱ ቡድኖችን የሚደግፉበት ሁኔታ እየታየ ነው። ይህ ደግሞ ችግሩን የሚያባብስ እንጂ የሚፈታው ባለመሆኑ ወደ ሌላ ግርግርና አመፅ ሊያመራ የሚችል ነው።

## የመካከለኛው ምስራቅ እድሎችና ፈተናዎች

የመካከለኛው ምስራቅ ሁኔታ ከአገራችን አንፃር ሲታይ በብዙ መንገዶች ትስስር ያለው ነው። በተለይም በዚሁ አካባቢ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ያለው ውጥረት ፋይዳ ለአገራችን ምን እንደሆነ አሳጥሮ መመልከት ይቻላል። የመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ወትሮም ቢሆን ሁከትና ግርግር የማይለየው ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለረዥም ጊዜያት የዓለማችን ፖሊስ ሁና የቆየችው አሜሪካ የብሄራዊ ደህንነትዋ ዋነኛው ስጋት ከቻይና ጋር ያላት ወድድር እንደሆነና በደቡብ ቻይና በሚገኙ ውሃማ አካላትና የፓስፊክ ውቅያኖስን ዋነኛው የትኩረት ቀጠናዋ ማድረግዋ ተከትሎ አካባቢው የደህንነት ስጋት ቀጠና መሆን ችሏል። ከሰሞኑ ደግሞ ለታይዋን የሁለት ቢሊዮን ዶላር መሳሪያ በሽያጭ ለማቅረብ መወሰንዋ ቤይጂንግን አበሳጭቷል።

ሰሞኑን አሜሪካ በፋርስና በኦማን ባህረ ሰላጤዎች መካከል ያለውን ሰርጥ ፣ እንዲሁም የመን፣ ጅቡቲና ኤርትራን የሚያዋስነው ባብ ኤል-ማንዳብ ሰርጥን በወታደራዊ ጥምረት ለመቆጣጠር ቅድመዝግጅት እያደረገች መሆንዋንም ይፋ አድርጋለች ። እነዚህን የንግድ መርከቦች ቁልፍ መተላለፊያና ባሕረ ሰላጤ እንዲሁም ቀይ ባሕርን የሚያገናኙ ስትራቴጂዊ አካባቢዎች ላይ አሜሪካ የበላይነትዋን የምታረጋግጠው ተጣማሪ አገራትን መርከቦች አጃቢ ብቻ አድርጋ እስዋ በምታስማራቸው ወታደራዊ መርከቦች አማካይነት አዛዥና ተቆጣጣሪ በመሆን ነው።

የፀደይ አብዮት (Arab spring) አመፅ ከተከሰተ ወዲህ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች የሃይል አሠላለፍ የተለዋወጠበት ሁኔታ ይስተዋላል። በአካባቢው ከፍተኛ ተደማጭነትና ሃይል የነበራቸው ኢራቅንና ሶሪያን የመሳሰሉ አገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ተዳክመዋል። ኢራቅ አሜሪካ በአካሄደችበት ወረራ ምክንያት ክፉኛ ደክማና ተጎሳቅላ ትገኛለች። ሶሪያም ብትሆን በተለያዩ የአረብ አገሮች በተፈጠረው አመፅና ረብሻ እንዲሁም

"እስማዊ ሁኔታው የሚፈጥራቸው መልካም አጋጣሚዎችና ፈተናዎች በትክክል በመረዳት እድሎችን ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ፈተናዎቹ ደግሞ ሲያደርሱት የሚችሉትን አደጋ ለመመከትና በብቃት ለመዝጋት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ከላይ እስከ ታች ያለው መዋቅራችን ሊገነዘበው ይገባል።"

በውስጧም በጣም አስከፊ በሆነ ሁኔታ ተቀጣጥሎ ወደ እርስ በርስ ጦርነት ገብታ ወደማያባራ የእርስ በእርስ ዕልቂትና ውድቀት ማጥ ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡ ከአገር ውስጥ የየጎበዝ አለቆች ታጣቂዎች ከርስ በእርስ ከሚተናነቁበት እና ከሚሞሻለቁበት ሁኔታ በተጨማሪ የአካባቢው አንበስ ለመሆን የሚፈልጉ እንደ ኢራን፣ ሳውዲ አረቢያ እና ሌሎችም በከፍተኛ ፉክክር ውስጥ ገብተው ይገኛሉ፡፡

የመካከለኛው ምስራቅ ሲነሳ የየመን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚስብ ነው፡፡ የመን በተለያዩ የአረብ አገሮች በተከሰተው አመፅና ግርግር ሰለባ ከመሆኗ በላይ ኢራንና ሳውዲ አረቢያ የሃይል የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ሃይላቸውን የሚያሳዩባት የእልቂትና ውድቀት አውድማ ሆናለች፡፡ ከሁለት አመት በፊት በሳዑዲ አረቢያ የሚመራው ሃይል በአስር ቀን ግዜ ውስጥ የየመን አማፂዎችን እንደመስሳቸዋለን በሚል የተጀመረው ወታደራዊ ጥቃት እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ጦርነቱ እስከ አሁን አላባራም፡፡ የዚሁ አካባቢ ችግርም ወደ ምስራቅ አፍሪካ የተሸጋገረበት ሁኔታ አለ፡፡

የገልፍ አገሮች በአካባቢያቸው በሚከተሉት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ልዩነት ምክንያት የኳታር እና ሌሎች የአካባቢው አገሮች ልዩነታቸው ተካርሮ በተለይም በኳታር እና በሣዑዲ አረቢያ መካከል የቆየው የተደበቀ መሳሳብ ግልፅ መሆን ችሏል፡፡ ሳዑዲና ደጋፊዎቿ በኳታር ላይ ማዕቀብ ጥለዋል፡፡ በዚሁም ምክንያት በአካባቢው ሁለት አሰላለፍ ተፈጥሯል፡፡ አንዱ በሳዑዲ አረቢያ የሚመራ ሆኖ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ (UAE) እና ግብፅን በዋናነት የያዘ ፣ ሌላው ደግሞ ኢራንና ቱርክ ከኳታር ጎን የቆሙበት ሁኔታ አለ፡፡ አሁን ከተፈጠረው አሰላለፍ ጀርባ በመሆን ደግሞ አካባቢውን ለመቆጣጠር አሜሪካንና ሩሲያ የራሳቸውን ደባ እየፈፀሙ ነው፡፡ በሣዑዲ አረቢያ የሚመራውን ኃይል አሜሪካ ደጀን በመሆን ስትደግፈው፣ በአንፃሩ ሩሲያም ኢራን፣ ቱርክና ኳታርን እየደገፈች ትገኛለች፡፡

ይህ ሁኔታ በመካከለኛው ምሥራቅ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያችን ሠላም ላይም ተፅእኖ እያሣደረ ነው፡፡ በምስራቅ አፍሪካ ስትራቴጂክ የሆነ ቦታ የሆነውን ቀይ ባህርን ለመቆጣጠር የቻሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች (UAE) የአሰብን ወደብ በመከራየት የአየር እና የባህር ሃይል በማስፈር ቦታውን ወታደራዊ ቤዝ/ቀጠና/ ማዘዣ አድርጋዋለች፡፡

በቀይ ባህር ዳርቻዎች የወታደራዊ ቤዝ መገንባት የመን ላይ ለሚካሄደው ጦርነት ከማገልገሉ በላይ ከዚህም ለአለፈ ፍላጎት ማስፈፀሚያ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በሶማሊያ ላይ ቀጥተኛ ተፅእኖ ለመፍጠርም ሁለቱም ወገኖች እየተፎካከሩ ይገኛሉ፡፡ የተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ ቀደም ሲል ከሶማሌ ላንድ የበርበራን ወደብ፣ ከፑንት ላንድ ደግሞ የቦሰሳ ወደብን መከራየታቸው ይታወቃል፡፡ ቱርክም በአካባቢው ቦታ ለመያዝ እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች፡፡ ሳዑዲ በበኩሏ በጅቡቲ ወታደራዊ ማዘዣ እየገነባች ትገኛለች፡፡ በሌላ በኩል ቱርክ የሱዳንን ሉአኪን ደሴትና ወደብ ለማልማት ከሱዳን ጋር የጋራ ስምምነት አድርጋ ወደ እንቅስቃሴ ገብታለች፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ ሳዑዲንና ሱዳንን ውጥረት ውስጥ ገብተው በቅርቡ የሆነውን ነገር ለመመልከት ችለናል፡፡ በሱዳን ውስጥ ያለውን አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ እና እንቅስቃሴም በቅርበት መመልከት የግድ ይላል፡፡

በአጠቃላይ የመካከለኛው ምስራቅ ውጥረት ከግዜ ወደ ግዜ እየተጠናከረ እየሄደ በመሆኑ በአካባቢያችን እየደረሰ ያለው ተፅእኖም በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ መንግስትና ህዝብ በቅርበት ሊከታተሉት እና አቅጣጫ ሊያስቀምጡለት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ የየራሱን መልክ እያየዘ እየሄደ ያለው የሃይሎች አሰላለፍ ባህሪውን በሚገባ በመረዳት አገራዊ ጥቅማችንን ሊያስከብር በሚያስችል መልኩ አቅጣጫ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ የየአካባቢው አንበሶች ሆነው ለመውጣት እነዚህ አገሮች እያደረጉት ያሉት ውድድር እና የሚዘረጉትን ወጥመድ በማስተዋል ጥንቃቄ ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ዲሲፕሊን ነው፡፡ አገራዊ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ግንኙነት በመፍጠር አገራችን ለደህንነትዋና ለልማትዋ የሚያስፈልጋትን ድጋፍ ከሁሉም ወገኖች ለማግኘት የሚደረገው ርብርብ ግን ትክክለኛ አቅጣጫ ነው፡፡

*"አሁን የተፈጠረውን እድል የመጠቀምና ያለመጠቀም ሁኔታ የሚወስነው ከላይ እስከ ታች ያለው አመራራችን የዚህች አገር ሰላምና ፀጥታ፣ ደህንነት ከመላው የአገሪቱ ህዝቦች ጋር ተቀናጅቶ ማረጋገጥ ሲችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡"*

# የአፍሪካ ቀንድ እድሎች፣ ፈተናዎች እና ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ

የአገሮች ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የራሱ ጥቅምና ጉዳት አለው፡፡ በአንድ ወቅት በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥዋ ምክንያት ምንም አይነት ጥቅም የማታገኝ የነበረች አገር ከቁጥጥርዋ ውጭ በሆነ ምክንያት ያላሰበችው እና ያልገመተችው ጥቅም ልታገኝ ትችላለች፡፡ ቀደም ሲል ዋነኛ ተጠቃሚ የነበረችም ስታገኘው የነበረችውን ጥቅም ልታጣ ትችላለች፡፡ ለዚሁ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የአፍሪካ ቀንድ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ ነው፡፡ ቀደም ሲል ዓለማችን በሁለት ልዕለ ሃያላን ማለትም በምስራቁና በምዕራቡ ጎራ ተከፍላ በነበረችበት ወቅት የአፍሪካን ቀንድ ለመቆጣጠር የሚፎካከሩበት ነበር፡፡ ከምስራቁ ጎራ መፍረስ በኋላ ግን ዓለም በምእራቡ ሃይል ልዕለ ሃያል አሜሪካ ቁጥጥር ስር ልትውል ቻለች፡፡ በዚህም የአፍሪካ ቀንድ ጂኦፖለቲካዊ አስፈላጊነት ከነበረበት ደረጃ የወረደበት ሁኔታ ተከስቶ ነበር፡፡ ለአብነት ኤርትራ አብዛኛው የቀይ ባህርን የሚያዋስን ቢሆንም እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ከውጭ ሃይሎች ትርጉም ያለው ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች፡፡ ካለፉት ሁለትና ሶስት አመታት ወዲህ ግን በልዕለ ሃያላን አገሮች ያለው ሽግግር ተያይዞ የአካባቢው ተፈላጊነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የዓለማችን ልዕለ ሃያል ለመሆን በሚደረገው ሁለተናዊ ትግል እነዚህ ተቀናቃኝ ሃይሎች ስትራቴጂክ የሆኑ ባህሮችና ውቅያኖሶችን ለመቆጣጠር እና የባህር ሃይላቸውን ለማጠናከር ያላሰለሰ ጥረት እና ፍትግያ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከፍተኛ ጂኦስትራቴጂካዊ ጥቅም እንዲያገኝ ካደረጉት ምክንያቶችም ቀይ ባህር የሚገኝበት አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡

ቀይ ባህር አውሮፓና ኤስያ በዋናነት የሚያገናኝ ፣ እንዲሁም አፍሪካን ከመካከለኛው ምስራቅ የሚያገናኝ የነዳጅ ንግድ ዋነኛው ማስተላለፊያ መስመር ነው፡፡ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሃያላን አገሮች ሊያረጋግጡት ከሚፈልጉት ጥቅሞች አንፃር ትኩረት ሰጥተን በደንብ ልንመዝነው ይገባል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያም ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች የምትፈጥረው የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ከዚሁ አየተነሳች በጥንቃቄ ልትመለከተው ይገባል፡፡ አገሮች የሚያደርጉት ትስስር ጠቀሜታቸው የላቀ ሊሆን የሚችለው ነፃነታቸውን ጠብቀው የህዝቦቻቸውን ዘላቂ ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉና ይህንን አላማ እውን የሚያደርጉ ሲሆን ነው፡፡ አገራችን ከሌሎች አገሮች የምትዋዋላቸው፣ የምትፈራረማቸው ነገሮች ሁሉ ከውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን፣ ህገ-መንግስታችንና ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ በመነሳት የሚፈጸሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡

በአሁኑ ግዜ በአለማችን እየታየ ያለው ፅንፈኛ አስተሳሰብ እኛ አገርም የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ባለው ፈጣን የቴክኖሎጂ ግንኙነት በየትኛውም የአለማችን አካባቢ የተከሠተ ጉዳይ ሠከንድ በማይሞላ ግዜ ውስጥ ሁሉም ጋር ስለሚዳረስ ተፅእኖው በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በተለይም ደግሞ ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል በሌሎች አገሮች ሲፈፀም ያየውን ተግባር ጥቅሙና ጉዳቱን በአግባቡ ሳያመዛዝን በስሜት አገራችን ላይም ሲከውነው ይስተዋላል፡፡ የሚካሄዱ ፖለቲካዊ ሁነቶች ህዝበኝነትና ፅንፈኛ አስተሳሰቦች በወጣቱ እና ሙሁሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፖለቲካዊ ሁኔታው የራሱ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ የአለማችን የንግድ ትስስር እና በተፈጥሮ መዛባት ዙሪያ ላይ እየታዩ ያሉ ለውጦችም በአገራችን አጠቃላይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ አሉታዊ ተፅእኖ እያሣደረ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

በማጠቃለል አገራችን ውስጥ የተፈጠረውንና እየተፈጠረ ያለው ችግር ዋነኛው ምንጩ የራሳችን አመራር ቢሆንም አሁን በዓለማችን ያለውን ሁኔታ የፈጠራቸው ችግሮችና ፈተናዎች የሚያደርሱት አሉታዊ ክስተት ተረድተን በአንድነትና በመቻቻል መርህ የምንመክትበትን ስልት መንደፍ ይገባናል፡፡ ሁኔታው በአዎንታ ይሁን በአሉታ እኛ ላይ የሚያደርሠው ተፅእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም አለማዊ ሁኔታው የሚፈጥራቸው መልካም አጋጣሚዎችና ፈተናዎች በትክክል በመረዳት እድሎችን ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ፈተናዎቹ ደግሞ ሊያደርሱት የሚችሉትን አደጋ ለመመከትና በብቃት ለመዝጋት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ከላይ እስከ ታች ያለው መዋቅራችን ሊገነዘበው ይገባል፡፡

*" አገራችን ውስጥ የተፈጠረውንና እየተፈጠረ ያለው ችግር ዋነኛው ምንጩ የራሳችን አመራር ቢሆንም አሁን በዓለማችን ያለው ሁኔታ የፈጠራቸው ችግሮችና ፈተናዎች የሚያደርሱት አሉታዊ ክስተት ተረድተን በአንድነትና በመቻቻል መርህ የምንመክትበትን ስልት መንደፍ ይገባናል፡፡ "*